# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

እሁድ 82ኛ ዓመት ቁጥር 092 ታኅሣሥ 2 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




ፎቶ - ፎቶ ሳሙኤል ተስፋዬ

ሼህ አብዱልሐሚድ አሕመድ

መምህር አዳነ ደቻሳ

# በቤተ ዕምነቶች አካባቢ ያለው የሙስና ችግር መፍትሔ ያስፈልገዋል

ጌትነት ተስፋማርያም

አዲስ አበባ፡- በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ ቤተ ዕምነቶች አሳሳቢ ደረጃ ላይ የሚገኘውን የሙስና ችግር የዕምነት ተቋማቱ አፋጣኝ መፍትሔ መስጠት እንዳለባቸው የሃይማኖት አባቶች አስታወቁ።

ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ቃለ ምልልስ ያደረጉት የኢትዮጵያ እስልምና ጠቅላይ ምክር ቤት ሥራ አስፈጻሚ አባልና የኢትዮጵያ የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ ምክትል ቦርድ ሰብሳቢ ሼህ አብዱልሐሚድ አሕመድ እንደገለጹት፤ የኃይማኖት ተቋማት በሙስና ጉዳይ ጣታቸውን ወደሌላ ከመቀሰራቸው በፊት ወደ እራሳቸው መመልከት ይገባቸዋል። በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ ቤተ ዕምነቶች አሳሳቢ ደረጃ ላይ የሚገኘውን የሙስና ችግር የዕምነት ተቋማቱ አፋጣኝ መፍትሔ መስጠት አለባቸው፡፡

እንደ ሃገር ያጋጠመውን የሙስና ችግር ለመቀነስ የሃይማኖት አባቶች ጉልህ ሚና አላቸው፤ በዚህ ረገድ ምሳሌ ሆነው በንጽሕና የሚሠሩ እንዳሉ ሁሉ በተቃራኒው ደግሞ በሙስና የተጠመዱ የሃይማኖት ሰዎችም አሉ ሲሉ ተናግረዋል።

በእስልምና ሃይማኖት ተቋማት ውስጥ ሰው በሙያውና በዕውቀቱ ሳይሆን በዝምድናና በሙስና

በቤተ ዕምነቶች አካባቢ ... ወደ ገጽ 5 ዞሯል



## ‹‹በእንስሳት ዝርያ ማሻሻል ላይ ብዙ ሥራ ይጠብቀናል››

- አቶ ዑመር ሁሴን
የግብርና ሚኒስትር

አስቴር ኤልያስ

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ውስጥ ላለፉት 68 ዓመታት እና ከዚያ በላይ የእንስሳት ዝርያ ማሻሻል ላይ ቢሠራም ካለን እንስሳት ሀብት አኳያ ዝቅተኛ በመሆኑ አሁንም ብዙ ሥራ ይጠብቀናል ሲሉ የኢፌዴሪ ግብርና ሚኒስትር አቶ ዑመር ሁሴን አስታወቁ፡፡ ዝርያ ለማሻሻል ሲታሰብ

‹‹በእንስሳት ዝርያ ... ወደ ገጽ 5 ዞሯል

## በተቋማት ቅንጅት መጓደል የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ከግማሽ ቢሊዮን ብር በላይ ኪሳራ አስተናግዷል

### - ኢትዮ-ቴሌኮምም በወር 12 ሚሊዮን ብር የሚጠጋ ኪሳራ ያስተናግዳል


ሶሎሞን በየነ

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ በመሠረተ ልማት ላይ በተሠማሩ ተቋማት መካከል ባለ የቅንጅት መጓደል ሳቢያ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት በአራት ዓመት ውስጥ 534,321,438 ብር ኪሳራ እንዳስተናገደ ጥናት አመላከተ። ኢትዮ ቴሌኮም በወር 11,651,000 ብር እንደሚያጣም ተመላክቷል፡፡

ከዚህም ባሻገር የተቋማት ቅንጅት ማነስ በሚያስከትለው የፕሮጀክት መዘግየት ምክንያት የኢትዮጵያ የመንገድ ፕሮጀክቶች ከአብዛኞቹ የምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት ጋር ሲነጻጸር ለተጨማሪ ወጪ መዳረጉን ጥናቱ አመላክቷል።

የኢትዮጵያ ፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት በሀገሪቱ የመሠረተ ልማት ተቋማት(ማለትም መንገድ፣ ቴሌኮም፣ ውሃ፣ የኤሌክትሪክ አገልግሎት...) መካከል ያለውን የቅንጅት ችግሮች እና የፕሮጀክት መጓተት በመመርመር መፍትሔዎችን ለማመላከት የሚያስችል ጥናት አከናውኗል።

ኢንስቲትዩቱ "የመሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች ቅንጅት



ተግዳሮቶች እና የመፍትሔ አማራጮች በኢትዮጵያ" በሚል ርዕስ ባከናወነው ጥናት በመሠረተ ልማት ላይ በተሠማሩ ተቋማት መካከል ባለ የቅንጅት መጓደል ምክንያት የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት በአራት ዓመት ውስጥ 534,321,438 ብር ኪሳራ እንዳስተናገደ እና ኢትዮ ቴሌኮምም በወር 11,651,000 ብር እንደሚያጣ ተመላክቷል።

የጥናቱ ግኝትም ሃገር አቀፍ የመሠረተ ልማት ማስተር

በተቋማት ቅንጅት ... ወደ ገጽ 5 ዞሯል


ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር

በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ

ፀደይ ባንክ (አ.ማ)
TSEDEY BANK (S.C)
የሁሉም ባንክ
Bank for all !
የብዙዎችን ተስፋ ያለመለመ!
በፋይናንስ አቅርቦት በተግባር የተፈተነ እንዲሁም ሰፊና ጽኑ መሰረት ያለው ባንክ በአነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ዘርፍ በአገለገለባቸው 25 ዓመታት አለም አቀፍ ዕውቅናዎችን ሲያገኝ የቆየው አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ወደ ፀደይ ባንክ ተሸጋግሮ የተሟላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡
Tel: +251 115 58 12 70/011 551 73 48/011 558 99 98
P.O.Box: 9630
E-mail: mekonnenyelewemwessen@tsedeybank-sc.com
Web: www.tsedeybank.org.et
Addis Ababa, Ethiopia

eccs
የኢትዮጵያ የግንባታ ግብዓቶች አቅራቢ ኃ/የተ/የግል ኩባንያ
ETHIOPIAN CONSTRUCTION COMMODITIES SUPPLY PLC.
የአርማታ ብረት እና ሌሎች ብረታብረቶች አከፋፋይ
Mob. 0911 225057/ 0989 343434
አድራሻ፡ ከሜክሲኮ አደባባይ ወደ መርካቶ በሚወስደው መንገድ ከዲ-አፍሪክ ሆቴል ፊት ለፊት




## "መንግሥት በሸብር፣ በጽንፈኞችና በሌቦች ላይ የጀመረውን እርምጃ አጠናክሮ ይቀጥላል"

- ዶክተር ለገሰ ቱሉ
የመንግስት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር

ገጽ 5


አዳማ ቆርቆሮ ፋብሪካ
ADAMA STEEL FACTORY
ሚስማር ከ3 ቁጥር -15 ቁጥር
የበረንዳ ታይልስ ኤጋ መደበኛ ኮሊሞ
0940 505050/0940 606060/0940 909090/0940 808080/0920 656565




## ብልሹ አሠራሮችንና ሙስናን ለመከላከል ተቋማት የኤሌክትሮኒክስ ግዥ ሥርዓትን መተግበር አለባቸው

ገጽ 2

# ፍርድ ቤቱ ቀልጣፋና ጥራት ያለው የፍትሕ አገልግሎትን ተደራሽ ለማድረግ እየሠራ ነው

**ገመቹ ከድር**

አዲስ አበባ፡- ቀልጣፋና ጥራት ያለው የፍትሕ አገልግሎትን ለኅብረተሰቡ ተደራሽ ለማድረግ ነባራዊ ሁኔታዎችን ለመቀየር የሚያስችል ሪፎርም ነድፎ በመንቀሳቀስ ላይ እንደሚገኝ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አስታወቀ ።

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ብርሃነመስቀል ዋጋሪ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት ፤ ኅብረተሰቡ ቀልጣፋና ጥራት ያለው የፍትሕ አገልግሎት እንዲያገኝ ፍርድ ቤቱ ካለበት ነባራዊ ሁኔታዎች ጫና ስር ለመውጣት ሪፎርም ነድፎ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል።

ነባራዊ ሁኔታዎች ከመሠረተ ልማት መሟላት፣ አሠራሮችን ከማዘመን፣ የሰው ኃይልና መሰል ጉዳዮችን ከሚሟላት ጋር ጭምር የተያያዙ እንደሆኑ ገልጸው ይህንን ለመቀየር ለአለፉት ሦስት ዓመታት ሪፎርም ተነድፎ ወደ ሥራ ተገብቶ እየተሠራበት ነው ብለዋል ።

የዳኝነት አስተዳደር ጉባዔ ፣ ጉዳይ ፍሰት መመሪያ፣ ፍርድ ቤት መር አስማሚነት አገልግሎት ፣ለፍርድ ቤት አገልግሎት አሰጣጥ አጋዥ የሆኑ አሠራሮች ተጠንተው ሥራ ላይ እየዋሉ ነው ያሉት አቶ ብርሃነመስቀል፤ውጤቱ በኅብረተሰቡ ዘንድ በሚሰጠው እርካታ እየታየ እየተሻሻለ እንደሚሄድ ገልጸዋል።

እንደ ፕሬዚዳንቱ ገለጻ ፤ ፍርድ ቤቱ በአዋጅ 3/22/1995 መሠረት በአምስት ክልሎች እንደሚቋቋም ቢደነገግም በአሁኑ ወቅት በቂ ችሎት ማስቻያ ቦታ ሳይኖረው የፍትሕ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል ።

የፍርድ ቤቱን ችሎት ማስቻያ ሕንጻ መገንባት ነባራዊ ሁኔታዎችን በፍጥነት ለመቀየር እንደሚያግዝ ገልጸው ጥር 2015 ዓ.ም የመሠረት ድንጋይ እንደሚቀመጥም ተናግረዋል።



ፎቶ - በሃዲሽ አብርሃ

የተከበሩ አቶ ብርሃነመስቀል ዋጋሪ

ከለውጡ በኋላ ኅብረተሰቡ ፈጣንና ቀልጣፋ የፍትሕ አገልግሎት እንደሚፈልግ ገልጸው የባለሙያ ሥነምግባርና ብቃት ችግሮችን በአሠራርና በስልጠና ምላሽ ለመስጠት እየተሠራ መሆኑንም ጠቁመዋል።

ዳኞች ነጻ ሆነው የዳኝነት ሥራ እንዲሠሩ የዳኞችን ነጻነት ሊያረጋግጡ የሚችሉ ሥራዎች መሠራታቸውን የገለጹት ፕሬዚዳንቱ፤ የሚዘገዩ መዝገቦች እልባት እንዲያገኙ ፍርድ ቤቱ ሰፊ ሥራዎችን መሥራቱን አያይዘው ገልጸዋል ።

ከሙስና፣ከሽብር፣ ከባድ ግድያ እና መሰል ወንጀል ነክ ጉዳዮች ውስብስብ በመሆናቸው ከሚመለከታቸው ፍትሕ ተቋማት ጋር በቅንጅት ስለሚሠራ ሊዘገይ እንደሚችል አብራርተዋል ።

መዝገቦች የሚዘገዩበት የራሳቸው ባሕሪ አላቸው ያሉት ፕሬዚዳንቱ ምስክሮች አለመቅረብ ፣ ተከሳሾች አለመገኘት፣ እክሎች መዛግብቶችን እንደሚያጓትቱ እንደምሳሌ አንስተዋል። መሰል ተግዳሮቶችን ለመቅረፍ በ2014 ዓ.ም ክረምት በተሰራው የተቀናጀ ሥራ 700 ውዝፍ መዛግብት እልባት ማግኘት መቻሉንም ችለዋል ።

እንደፕሬዚዳንቱ ገለጻ፤ ፍትሕ አገልግሎቱን በፍጥነት ተደራሽ ለማድረግ ተመራጭ የግጭት መፍቻ መንገዶች ከሆኑት ፍርድ ቤት መር አስማሚነት አገልግሎት ተግባራዊ እየተደረገ ነው ።

ይህ አሠራር በተከራካሪ ቡድኖች ተሳትፎ የሚሰጥ የዳኝነት ሥርዓት በቅርብ ጊዜ በሕግ እውቅና አግኝቶ ወደ ሥራ መግባቱን ጠቅሰው አሠራሩ የኅብረተሰቡን ወጪና ጊዜ በመቆጠብ ዘላቂ ሰላም ለማስፈን ትልቅ አስተዋፅዖ አለው ብለዋል ።

የፍትሕ አገልግሎቱ ልዩ ትኩረት ለሚሹ ኅብረተሰብ ክፍሎች ተደራሽ ለማድረግ በተለይ አዛውንቶች፣ሴቶች፣ሕጻናት ፣ አካል ጉዳተኞች ቅድሚያ አገልግሎት እንዲሰጣቸው በማድረግ ተደራሽነቱን በማስፋት እየተሠራ ነው ብለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ "ቀይ መስመር ያልነውን ወደ ቀይ ምንጣፍ ቀየሩ" ያሉት ጉዳይም የችግሩን ግዝፈት የሚያሳይ ነው ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ ይህንን ችግር ለመፍታትም የፍርድ ቤቶችን አቅም ማጠናከርና አገልግሎትን ማሻሻል ተገቢ መሆኑን ጠቁመዋል።

# ቁንዝላን የቱሪስት መዳረሻ ለማድረግ እየተሠራ ነው

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- ቁንዝላንና አካባቢዋን በማልማት የቱሪስት መዳረሻ ለማድረግ እየሠራ መሆኑን የከተማዋ መሪ ማዘጋጃ ቤት አስታወቀ። በአካባቢው አራት ሺህ 50 ሄክታር መሬት እየለማ መሆኑም ተመላክቷል።

የቁንዝላ ከተማ መሪ ማዘጋጃ ቤት ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ እጅጉ አየለ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ ከተማዋ በተፈጥሮ ሀብት የታደለች ጥንታዊ ከተማ እንዲሁም ለሰው ልጅ መኖሪያና ለኢንቨስትመንት ሁለንተናዊ ክንዋኔ አመቺ ስትሆን፤የቱሪስት መዳረሻ እንድትሆን በርካታ የልማት ፕሮጀክቶች እየተተገበሩባት ይገኛሉ። ጥያቄ ካቀረቡ ባለሀብቶች የተወሰኑት ፕሮጀክታቸው ተገምግሞ ጸድቆላቸዋል።

የጣና ሐይቅ፣ የጣና ገዳማት፣ የእቴጌ ምንትዋብ ጅምር ሕንጻና በርካታ ጥንታዊ ገዳማት በቁንዝላና አካባቢው መኖራቸውን የገለጹት ኃላፊው፤ አካባቢውን የቱሪዝም መስህብ ለማድረግ በአሁን ወቅት ጥሩ መነቃቃት እንዳለ ጠቅሰዋል። የማደግ ዕጣ ፋንታዋም ከጊዜ ወደጊዜ እየተሻሻለ የመጣ ነው ብለዋል።

ቁንዝላና አካባቢው የጣና በለስ ኤሌክትሪክ ማመንጫው የውሃ መግቢያ፤ በርካታ ሀብት ያለበት፣ ጥንታዊ ገዳማትና ቅርሶች ያሉበት በመሆኑ ለቱሪስት መዳረሻነት መልካም አጋጣሚ እንደሆነ ተናግረዋል።

በተፈጥሮ የታደለውን አካባቢ ለቱሪዝም መስህብነት ማዋል ሀገራዊ ፋይዳው ከፍ ያለ ነው ያሉት ኃላፊው፤ ከሚዳሰሱ ቅርሶች በተጨማሪ እንደ መስቀልና ጥምቀት ያሉ ክብረ በዓላት በልዩ ሁኔታ እንደሚከበሩ ገልጸው፤ቱሪስቶችም በአካባቢው ጉብኝት እንዲያደርጉና ለቱሪዝሙ መስፋፋት የበኩላቸውን እንዲያበረክቱ ጠይቀዋል።



ኃላፊው፣ ከሆቴልና ቱሪዝም ኢንቨስትመንት አንጻር በርካታ ባለሀብቶች ጥያቄዎችን እያቀረቡ እንዳለ ጠቅሰዋል። ፕሮጀክት አስገብተው ጸድቆላቸው ውሳኔ እየጠበቁ መሆናቸውንም አንስተዋል።

የአካባቢው ማኅበረሰብ ባለው የመልማት ፍላጎት በተለይ ቱሪዝም ላይ ለሚሠሩ ሥራዎች አስተዳደሩ ዝግጁ ሆኖ እንደሚጠበቅ አስታውቀዋል።

ከፀጥታ ጋር ተያይዞ ያለው ነገር አስተማማኝ እንደሆነ በመጠቆም፤ እያንዳንዱ የቱሪዝም ልማት እንቅስቃሴ ለሕዝቡ የኢኮኖሚ አቅም እንደሚፈጥር በመታሰቡ ቅድሚያ ተሰጥቶት እየተሠራ እንዳለ አመላክተዋል።

በአካባቢው የአገር ውስጥም ሆኑ የውጭ አልሚ ባለሀብቶች ኢንቨስት እንዲያደርጉም ጥሪ አቅርበዋል።

አካባቢው ከያዛቸው ታሪካዊ ሥፍራዎች ባሻገር የትኛውንም ዓይነት የኢንቨስትመንት አማራጭ የማስተናገድ አቅም ያለው መሆኑን በመጥቀስ፤ በተሠራው የከተማው "ስትራክቸራል ፕላን" አራት ሺህ 50 ሄክታር መሬት በኔዘርላንድ መንግሥት በኩል የተለያዩ ተሞክሮዎች ተወስዶ የኢንቨስትመንት ሥራዎች እየተሠሩበት እንደሆነም ገልጸዋል።

እንደ ኃላፊው ገለጻ፤ ከከተማ ጽዳትና ውበት ጋር ተያይዞ እየተሠሩ ያሉ ተግባራት ለከተማዋ ማደግ ተስፋ የሚሰጡ ናቸው።

አካባቢውን እንደጎርጎራ ለማድረግ የሚያስችል የተፈጥሮ ሀብትም ይገኛል።

"መንግሥት ከያዘው የበጋ መስኖ ጋር ተያይዞ ጣናን መጠቀም ቢቻል በኢኮኖሚው ዘርፍ ለአገር የሚጠቅም ትልቅ ሥራን በመሥራት ውጤቶችን ማስመዝገብ ይቻላል።

ከውጭ የሚገዛውን ስንዴ ለማስቀረት ትልቅ አበርክቶ አለው" ሲሉም ተናግረዋል።

ቁንዝላ ከአማራ ክልል ዋና ከተማ ከባሕርዳር ቅርብ ርቀት በደቡብ ምዕራብ ጣና ሐይቅ ላይ የምትገኝ ትንሽ የወደብ ከተማ ስትሆን፤ ለረዥም ዘመናት የቆየ ታሪክ ያላትም ናት።



ሐጂ ኢብሳ

# ብልሹ አሠራሮችንና ሙስናን ለመከላከል ተቋማት የኤሌክትሮኒክስ ግዥ ሥርዓትን መተግበር አለባቸው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በመንግሥት ተቋማት የሚስተዋለውን የሙስና እና ብልሹ አሠራር ችግር ለመከላከል የኤሌክትሮኒክስ ግዥ ሥርዓትን በሁሉም ተቋማት መተግበር እንደሚገባ የመንግሥት ግዥና ንብረት ባለስልጣን አስታወቀ።

የኤሌክትሮኒክስ የመንግሥት ግዢ ሥርዓት (eGP) የተባለ መተግበሪያ ከንክኪ የጸዳ፣ ወጪ ቆጣቢ፣ ቀልጣፋ፣ ግልጽ እና ዘርፉ ለሙስና ያለውን ተጋላጭነት የሚቀንስ መሆኑም ተገልጿል።

የመንግሥት ግዥና ንብረት ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ሐጂ ኢብሳ እንደገለጹት፤ የኤሌክትሮኒክስ ግዢ ሥርዓት የመንግሥት ተቋማት የግዢ ፍላጎታቸውን በቀላሉ የሚጠይቁበት ዲጂታላይዝድ አሠራር ነው። በአጭር ጊዜ በሁሉም ተቋማት ተደራሽ መሆን የሚያስችል ሲሆን ምርትና አገልግሎት አቅራቢዎችም ያለ ውጣ ውረድ ተወዳድረው መሸጥ የሚያስችላቸው ነው።

ከ70 በመቶ በላይ የመንግሥት በጀት ለግዢ የሚመደብ መሆኑን ጠቁመው፤ ከግዥና ጨረታ ጋር ተያይዞ ሙስና እና ብልሹ አሠራሮችን ለመከላከል አዲሱ የግዥ ሥርዓት አይተኬ ሚና አለው ብለዋል።

ከዚህ ቀደም የነበረው የጨረታ ሂደት አሰልቺ፣ ለብልሹ አሠራር የተጋለጠ እንደነበር አስታውሰው፤ የመንግሥት የኤሌክትሮኒክስ ግዢ ሥርዓት ይህን በማስተካከል የመንግሥትና ሕዝብን ሃብት ከሙሰኞች የሚታደግ መሆኑንም ጠቁመዋል።

በኤሌክትሮኒክስ የግዥ ሥርዓትን በመጠቀም በኩል አሁን ላይ 73 የፌደራል ተቋማት እየተጠቀሙ መሆኑን ጠቁመው፤ የቀሪዎቹም በቅርብ ጊዜ ወደ አዲሱ የግዥ ሥርዓት ይገባሉ ነው ያሉት።

የዓለም አገራት ሙስናን ለመከላከል ይህን ሥርዓት ቀድመው ተግባራዊ በማድረግ ላይ መሆናቸውን አውስተው፤ በኢትዮጵያም በመተግበር ላይ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

በቀጣይ ሁሉም የመንግሥት ተቋማት ወደ እዚህ የግዢ ሥርዓት በመቀላቀል ዘመናዊ አሠራር እንዲከተሉ አሳስበዋል።

በተያዘው እቅድ መሠረት በቀጣይ በአዲስ አበባ ከተማ፣ በክልሎች እና በሌሎች ተቋማትም የሚተገበር መሆኑን ኢዜአ ዘግቧል።

በቀጣይ በአዲሱ የግዥ ሥርዓት ውስጥ ያልተመዘገበ የንግድ ተቋም በመንግሥት የግዥ ጨረታ ውስጥ መሳተፍ የማይችል በመሆኑ እንዲመዘገቡ ጥሪ አቅርበዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ኢትዮጵያ ትፈተናለች እንጂ አትሸነፍም!

ኢትዮጵያ የረጅም ዘመን ታሪክ ባለቤት እንደመሆኗ ለበርካታ ጊዜያት ከውስጥም ከውጪም ፈተናዎች ገጥመዋታል። የእርስ በርስ ግጭቶች፣ የውጪ ጠላትና ወራሪዎችን ሁሉ አሳልፋለች። ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ችግሮችንም ተጋፍጣ አልፋለች። አሁንም ድረስ ከውስጥም ከውጪም የሚፈታተኗት፤ እድገትና ሰላሟን የሚገዳደሯት ችግሮች በርካታ ናቸው። ነገር ግን ሁሉንም እንደየአመጣጡ በጥበብ ፣ በብልሀት፣ በእውቀት እና በጀግንነት እየመከተች ዛሬ ለደረስንበት ደረጃ ደርሳለች። ፈተናዎች ቢፈትኗትም እየተሸነፈች ሳይሆን እያሸነፈች ቀጥላለች።

የኢትዮጵያ የመከራዋ ማብቂያ ደረሰ፣ ሰላም ወረደ፣ ሁሉም ነገር ወደልማት ወደ ብልጽግና ሲባል ከውስጥም ችግር ጠንሳሽ አይጠፋምና ሰላምን ለማደፍረስ፤ ሁከት ከዚህም ከዚያም እንዲቀሰቀስ ተግተው የሚሰሩ ይቀጥላሉ ። ሀገሪቱ በሰላም ውላ እንዳታድር ጸረ ሰላም የሆኑት ሁሉ ጸብ ሲጠነስሱና ሲጠምቁ ይከርማሉ። ይሄንኑ የጸብ ድግስ ከሀገር ውስጥ እስከ ውጪው ዓለም የሚያራግቡ አጀንዳውን ተቀብለው ሲያሟሙቁ ይከርማሉ። ይሄ በኢትዮጵያና በሕዝቧ ላይ የሚደረገው አንድነትን የማናጋት አንዱን ብሄርና ሃይማኖት በሌላው ብሄርና ሃይማኖት ላይ ለማነሳሳት የሚጫረው እሳት እንዲሁም እሱን ለማቀጣጠል የሚርከፈከፈው ነዳጅ ዛሬ አዲስ አይደለም። ቀደም ባሉት ዘመናት ሁሉ ታሪካዊ ጠላቶች ሀገሪቱን በቀኝ ለመግዛት ፣ተፈጥሯዊ ሀብቷን ለመጠቀም ፣ህዝቧን የበይ ተመልካች ለማድረግ ብዙ ሙከራዎችን አድርገዋል። ይሄንን ሁሉ ሙከራ ሕዝቡ ያሸነፈውና ተቋቁሞ አሁን ለደረስንበት ደረጃ የደረሰው በአንድነት ፣ በጥንካሬ፣ በሀገር ፍቅር ስሜት ችግር መከራውን ሁሉ መመከትና መቋቋም በመቻሉ ነው።

ጣሊያን ሀገራችንን የወረረው ሕዝቡን በቅኝ ለመግዛት ዳር ድንበር ተሻግሮ፣ አገር አቋርጦ የመጣው ከኢትዮጵያ በተሰነዘረበት ትንኮሳ አይደለም፤ በነበረው የአቻ ስሜት ትከሻ እንለካካ ፉክክር ውስጥ ገብቶ አልነበረም። በወቅቱ አውሮፓውያን አፍሪካን ለመቀራመት በነበራቸው ፍላጎት ኢትዮጵያንም በቅኝ ለመግዛት አስቦ ነው። ሆኖም ግን ኩሩው ኢትዮጵያዊ ሀገሩን የሚወደው፣ ለሀገሩ ሉአላዊነት የሚዋደቀው ፣ የሀገሬን ዳር ድንበር አላስደፍርም፣ ነጻነቴን አሳልፌ አልሰጥም ብሎ ህይወቱን ገብሮ፣ ደሙን አፍስሶና አጥንቱን ከስክሶ ዘመናዊ ጦር ታጥቆ የመጣን ወራሪ አሳፍሮ መልሷል።

ይሄ የሆነው ሁሉም ነገር አልጋ በአልጋ ስለሆነለት አይደለም። በእጁ ላይ ዘመናዊ መሳሪያ የተሟላ ስንቅና ትጥቅ ይዞም አልነበረም። ይዞ የተነሳው አንድ ነገር ብቻ ነው እሱም ኢትዮጵያዊነት! የሀገር ፍቅርና አንድነት ነው። ይሄን ሲያደርግም እርስ በርስ ሳይጋጭ፣ ቅሬታ ሳይገባው ፤ ከመሪዎች ጋር የሃሳብ ልዩነት ወይም ቅራኔ ሳይኖረው ቀርቶም አይደለም። ሁሉም ነገር የተደላደለ ቀይ ምንጣፍ ሆኖለትም አይደለም። ችግሮች ቢኖሩ እንኳን በሀገር ላይ አይኮረፍም። በውስጥ ጉዳይ ተነጋግሮ፣ ተግባብቶና በይቅርታ ተላልፎ መቀጠል የሚቻል በመሆኑ ነው። ቂምና ቁርሾን ከራሱ አርቆ እንደ አንድ ሃሳቢ እንደ አንድ ተናገሪ ሆኖ በጋራ በመነሳቱ ነው ውጤታማ መሆን የተቻለው። አሁንም በሀገራችን ላይ የሚያጋጥሙንን ውስጣዊም ሆነ ውጫዊ ችግር ማሸነፍ እና መወጣት የምንችለው ተለያይተን ፣ ተከፋፍለን ፣አንዱ በሌላው ላይ ጣት ቀስሮ መሆን የለበትም። በተቻለ መጠን ችግሮችን ተነጋግሮ በመፍታት ነው። ቁጭ ብሎ በመወያየት እና በመተሳሰብም ጭምር ነው።

በውስጥ የምንከፍተው በር ለጠላቶች መግቢያ ይሆናል። ስለዚህ የሰላም እጦታችንን ለሚፈልጉ ማስገቢያ መስኮት መሆን የለብንም። በመሃላችን ንፋስ እንዳይገባን ጭላንጭሉን ሁሉ መዝጋት ይጠበቅብናል። የሀገራችን ፈተናዎች አሁን ያጋጠሙን ክስተቶች ብቻ አይደሉም በፊትም ነበር፤ አሁንም አለ ወደፊትም ማጋጠሙ ሊቀጥል ይችላል። ሆኖም ግን የሚያጋጥሙንን ፈተናዎች የምናልፍበት መንገድ ነው ጥበብ መሆን ያለበት።

ኢትዮጵያ ሁሌም ትፈተናለች ነገር ግን አትወድቅም። አሁንም እየተፈተነች ነው ነገር ግን አትሸነፍም። ሁሌም ፈተናዎችን አሸንፋ ትቀጥላለች። ይሄንን ደግሞ ባሳለፍናቸው የመከራ ጊዜያቶች ሁሉ አይተነዋል። አሁንም እየሆነ ያለው ይሄ ነው።

ይሄ የሚሆነውም የሆነውም በአንድነታችንና በጥንካሬያችን ምክንያት ነው። አሁንም ሆነ በቀጣይ የሚያጋጥሙንን ፈተናዎች ማሸነፍ የሚቻለው አንድነትን በማጠናከር ብቻ ነው። ለሁላችንም የምትሆን ሀገር መገንባት የምንችለው የዛሬውን እያሰብን ሳይሆን ነገአችንን ትኩረት አድርገን በመስራት መሆን አለበት።

አሁንም ኢትዮጵያ ፈተናዎች ቢበዙባትም ቢደራረቡባትም ትፈተናለች እንጂ አትሸነፍም። ሁሌም አሸናፊ ሆና ትቀጥላለች። ለዚህ ግን ሁሉም ብሄር ብሄረሰብ ልዩነቱን ውበት፤አንድነቱን ጥንካሬ አድርጎ ሊቀጥል ይገባል። ከሚወረወሩ ወቅታዊ፣ አሳሳች እና አደናቃፊ አጀንዳዎች ራስን ማራቅ፣ አርቆ ነገን ማሰብም ይገባል!


ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


ነፃ ሃሳብ

**ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::**

# የእግር ኳሳችን ጉዳይ

ግርማ መንግሥቴ

በአለማችን "ሁሉንም" ከሆኑት አንዱ ስፖርት ነው። በአምስቱ ቀለበቶች ይታጠር እንጂ ስፖርት የማይነካካው ጉዳይ እስከ ዛሬ አልታየም። በመሆኑም የሕዝብ ስለሆነው ስፖርት ሀሳብ መለዋወጥ፣ የሁሉም ይሆናል ማለት ነውና በርእሳችን ዙሪያ እንቀጥል።

እርግጥ ነው፣ ዘመናዊ ሥልጣኔ ካፈራቸው ስፖርቶች አንዱ፤ በ19ኛው ምዕተ አመት መጀመሪያ አካባቢ ወደ አገራችን የገባውና የመጀመሪያውን ውድድር በ1919 ዓ.ም በት/ቤቶች ያደረገው የእግር ኳስ (ቡድናችን) ጉዳይ እማይነጠው ሰው ማግኘት ይከብዳል። ይህ እስከ ዛሬ ድረስ በነበረው የስፖርት ቤተሰቦች ዘንድ ሲታይ የነበረ ሲሆን፣ ዝቅ ብለን እንደ ምናየው ዛሬ ነገር አለሙ ሁሉ ተለዋውጧል።

ምንም ጥያቄ የለም፣ ያለንበት ዘመን ስለስፖርት የሚዘግቡ ሚዲያዎች እንደ አሸን የፈሉበት ነው። በመሆኑም የብዙዎችን ልብና አእምሮ ከመማርክ አልፈው አይንና ጆሮን ቀስፈው ለመያዝ ችለዋል። ግን፣ ግን እየዘገቡ ያሉት ስለስፖርት፣ ኳስ ጥበቡ፣ ቴክኒክና ታክቲኩ ነው? አይደለም።

ስለ እውነት እንነጋገር ከተባለ ስለስፖርት በሚቀርቡት ትረካዎች (በሙሉ ሊባል በሚችል ደረጃ) ስለ ተጫዋቾች የሽያጭ ሁኔታ፣ የገዥዎች የመግዛት አቅም፣ የተገዥው የመሸጥ አለመሸጥ እድል ወዘተ እንጂ ስለ ኳስ ጥበብ፣ ሳይንስ፣ ፊዚክስና የመሳሰሉት አይደለም። እግር ኳስንና ተጫዋቾችን ከስነልቦና አኳያ የሚያስተነትን የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ ይህ ጸሐፊ አላጋጠመውም።

ከላይ እንዳልነው በተደጋጋሚ የሚያጋጥመው ትንፋሾች ሁሉ የሚያጥኑት ስለ ግዥና ሽያጭ፤ ፌደሬሽኖች አካባቢ ስለሚታይ ሽኩቻ እንጂ እግር ኳሱ እንዴት ወደፊት መሄድ እንዳለበት፤ ፕሮግራሞቹ ከማስታወቂያ ጋር ተስማምተው እንዲሄዱ ሲደረጉ እንጂ እግር ኳሱን ታሳቢ ያደረጉ፤ እግር ኳሱ ያለበትን አጠቃላይ ሁኔታ የሚያጠይቁ አይደለም። ያለው ሁኔታ ያው ያለው ሁኔታ ብቻ ነው። በመሆኑም ያሳስባል።

እዚህ ላይ ከስነልቦናም እንበለው ሙያዊ ዲሲፕሊን አኳያ ተጫዋቹ(ቾቹ) የት ጋ ነው ያለው/ሉት? ብለን ስንጠይቅ ለራሳችን የምናገኘው መልስ አስደንጋጭ ነው ፤ አስደንጋጭነቱም የሚጀምረው "ቤቲንግ ሲፍቅ የተገኘው የቡና ተጫዋች 'ቡና ይሸነፋል'" ብሎ መወራረዱ፤ በዚህም ምክንያት "ቦርዱ ላይመለስ ያሰናበተው" መሆኑን በፕራይም ዜና ስንሰማ ነው። በዚህ ሁኔታ ስለአለም ዋንጫ ማሰብ ይቻላል? ይህን ማሰብ እራሱ ስለ አለም ዋንጫ ምንነት ካለማወቅ የመነጨ እንጂ ሌላ ምን ሊሆን ይችላል?።

ይህንን ሁሉ ስንል አቅም ሲጠፋ፣ ውጤት "ሲሄድ"፣ ባለጋራ የበላይነቱን ሲይዝ ... "ጫማው ይዞኝ ... ነው"፤ "ቁንጣው አጥሮኝ ... ነው"፤ "ገምባሌው ጠቦኝ ..."፤ "ዳኛው ቂሙን በፊሽካው ስር ቋጥሮ ...፣ ለባለጋራ ወግኖ... ነው" ወዘተርፈን ሳናካትት መሆኑን አንባቢ ልብ ሊልልን ይገባል።

የመሀል ዳኛውን በማራገቢያ እንጨት ሲያሳድድ (የአዲግራቱን ጨዋታ ያስታውሷል) የታየ ብቸኛ ቡድን ኢትዮጵያ ውስጥ መታዩትን ረስተን አለመሆኑንም ከግምት ውስጥ ያስገባልን ዘንድ፤ እየተካሄደ ስላለው የአለም ዋንጫ ስንል መሆኑን እንዲያውቅልን አደራ እንላለን።

ግራዚያቶ የተባሉና "የተበሉ" አሰልጣኝ "የኢትዮጵያ ቡድን ብላ ያልከውን ትቶ ጥብስና ቅቅሉን ሲወርድበት ታየዋለህ" ያሉትም ከግምት የማይገባ እንዳልሆነም እንዲሁ።

ሌላው አስደንጋጭ "ነገ ለውድድር ወደ ውጭ አገር ሊሄድ የተዘጋጀ ቡድን አባል የሆነ ተጫዋች ማታ ከእጮኛው ጋር ምሽት ቤት ታየ። 'ምነው?' ሲባል፣ ሽኝት እያደረገችልኝ ነው" የሚለውም ለዘፈንና ግጥሙ አወራረድ ሲባል የተደረደረ አለመሆኑን ያልዘለልነው ለአለም ዋንጫ ለመድረስ መንገዱ ይህ አለመሆኑን ለመጥቀስ በመፈለግ እንጂ ሌላ አይደለምና "አፉ" እንደምንባል ተስፋ አለን።

"የድሮ ናፋቂዎች" ሲናገሩ እንደሚሰማው መንግስቱ ወርቁ ቀን፣ በልምምድ ወቅት ያሳየውን ድክመትና በአሰልጣኙ የተሰጠውን ምክር ጠዋት አርሞና ልቆ ይገኝ ነበር፤ "እንዴት?" ሲባል ከተያዘለት መኝታ ቤት ጠፍቶ በመውጣት ለሊቱን ልምምድ በማድረግና ስህተቱን በማረም ጠዋት ብቁ ሆኖ መገኘት በመቻሉ እንደ ሆነ ይነገራል። በመሆኑ መንግሥቱ ወርቁ ያው መንግሥቱ ወርቁን ሆኖ ሊያልፍ ቻለ።

"የድሮ ናፋቂዎች" ሲያማርሩና ሲያዝኑም እንደሚታየው በ1943 (እ.ኤ.አ.) ከተመሰረተው (በ1953 የፊፋ፣ በ1957 የካፍ አባል ከሆነው) እግር ኳስ ፌደሬሽን አካባቢ "አልፎ አልፎ" የሚሰማው ተኩስ የሚረብሽና ለእግር ኳሱም እንደ በሬ ሽንት ወደ ኋላ መሄድ ምክንያት ነው፤ ከእነ ይድነቃቸው ተሰማ የፀጥታ ዘመን ጋር ሲወዳደር ከደረጃ በታች ነው። የአሁኑ ዘመን የፌደሬሽኑ ባለ ስልጣናት "ደረት የማያስነፋ፤ አንገት የሚያስደፋ ሥራ እንጂ ሌላ የተሰራ ስራ የለም"። ይህ ሌላው ለ138ኛነታችን ምክንያት ነው።

እነዚሁ "የድሮ ናፋቂዎች" እንደሚሉት የድሮው ብሔራዊ ቡድን በአየር ንብረትና የተለያዩ ምክንያቶች የልምምድ ስፍራ ሲያጣ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመነጋገር ልደት አዳራሽ ውስጥ ልምምድ ያደርግ ነበር። ዛሬ ግን አገር ሙሉ ስታዲየም ለምንም ሳይሆን ምንም ሆኖ እየቀረ ይገኛልና የዛሬም ሆነ የወደፊቱ የአለም ዋንጫ ለኢትዮጵያ፣ የመድረኩ ንጉስ እንዳለው "ርቆ የተሰቀለ ዳቦ ..." እንዳይሆን ያሰጋል።

የድሮዎቹ ተጫዋቾች ምርጥ ምርጥ ጨዋታዎችን በቪዲዮ አስቀርተው እቤታቸው ቁጭ ብለው የሚያዩ ሲሆን፤ ይህ በአሁነኞቹ ዘንድ "የማይረባ" አስተሳሰብ ሆኖ ነው የሚለውም በቀላሉ ሊዘለል የሚገባው ጉዳይ አይደለም።

እንደ "የድሮ ናፋቂዎቹ" አባባልም ሆነ ነፃ አስተያየት ተመልካችም እንበለው ቲፎዞ ጋ የከፋ ችግር አለ። ኳስን እሚመለከተው ከኳስ ፍቅር ወይም ጥበብ አንፃር ሳይሆን ከተወራረደበትና አገኛለሁ (አሸንፋለሁ) ብሎ በእቅድ ከያዘው ገንዘብ (ብሄራዊ ባንክ "መንፈሳዊ ገንዘብ" ይለዋል) አኳያ ነውና ችግሩ የአንድ ወገን ብቻ አይደለም ማለት ነው። ኳስ አደጋ ላይ ነች (ለነገሩ በስፖንሰር አድራጊነት ምክንያት የአንደኛው ስያሜ "ቤቲኪንግ የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ" አይደል እንዴ)። ዝርዝሩ ብዙ ነው።

### ያለንበት ይዞታ

በ2018 በተደረገ ጥናት የ"አደረጃጀት እና አወቃቀር፣ የተዝረከረከ ልማዳዊ አሰራር ... ችግር" እንዳለበት የተረጋገጠው፤ በአሁኑ ሰአት ለአፍሪካ ዋንጫ እየተዘጋጀ ያለው ብሄራዊ እግር ኳሳ ቡድናችን (ሉሲም ሆነ ዋሊያ) በአሁኑ ሰአት ከዓለም 138ኛ ደረጃ ላይ ይገኛል። እንደ ፊፋ ደረጃ አሰጣጥ ከ2019 ጀምሮ ቡድናችን ምንም አይነት መሻሻል ሳያሳይ በዚሁ ደረጃ ላይ ጮቤ እየረገጠ ነው።

እንደ "የድሮ ናፋቂዎች" ከሆነ፣ በዚሁ ከገፋን የአለም ዋንጫ እንዳማረን የሚቀጥለው ሚሌኒየም እንዳይመጣ ያሰጋል። የሕዝቡም ወሽመጥ መበጠሱም እንደዛው። (በነገራችን ላይ፣ ቡድናችን የመጀመሪያው ኢንተርናሽናል ውድድር የተደረገው ጂቡቲ ከነበረው የፈረንሳዊያን መርከበኞች ቡድን ጋር በ1940 ዓ.ም ነበር፡፡)

### የአለም እግር ኳስ ይዞታ

ወቅቱ የዓለም ዋንጫ እየተካሄደ ያለበት ነው። ያልተጠበቁት ሴኔጋልና ሞሮኮ 16 ውስጥ ሲገቡ (ሞሮኮ 8 ውስጥም ገብታለች) እነጀርመን፣ ቤልጂየም (ቡድኑ በመሸነፉ ምክንያት ሕዝባዊ ተቃውሞ ገጥሞታል) ... የተሰናበቱበት ሁኔታ ነው ያለው። ይህ የሚያሳየን እግር ኳስ እንኳን ተቀልዶበት እንዲሁም ከባድ ነውና "የእኛዎቹ ከዚህ ምን ይማሩ ይሆን?" የሚለውን ለማንሳት ያህል ነውና መልካም የዓለም ዋንጫ!!!

በነገራችን ላይ፣ በአሁኑ ሰአት የስፖርቱ ባለቤት ግን ማን ነው? ፌዴሬሽኖች፣ ወይስ ...

# “መንግሥት በሸብር ፣ በጽንፈኞችና በሌቦች ላይ የጀመረውን እርምጃ አጠናክሮ ይቀጥላል”

*- ዶክተር ለገሰ ቱሉ*
*የመንግስት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር*

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- መንግሥት በሽብር፣ በጽንፈኞች፣ በሌብነትና የጥቅም ትስስሮች ላይ የጀመረውን ዘመቻ እና እርምጃ ኅብረተሰቡን ባሳተፈ አግባብ አጠናክሮ ይቀጥላል ሲሉ መንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ዶክተር ለገሰ ቱሉ ገለጹ።

ጥያቄዎቻቸውን በውይይት፣ በድርድር እና ሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ለሚፈልጉ ኃይሎችም በሩ ክፍት መሆኑን አመልክተዋል።

መንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ዶክተር ለገሰ ቱሉ በማኅበራዊ ገጻቸው ላይ ባሰፈሩት መልዕክት፤መንግሥት በሽብር፣ በጽንፈኞች፣ በሌብነትና የጥቅም ትስስሮች ላይ የጀመረውን ዘመቻ እና እርምጃ ኅብረተሰቡን ባሳተፈ አግባብ አጠናክሮ ይቀጥላል። እስከአሁን የተገኙ ውጤቶችም አበረታች ናቸው።

የሰሞኑ ሁከትና ብጥብጥ ዋና ዓላማ መንግሥት በሌብነት ላይ የከፈተው ዘመቻና በሰሜኑ የተጀመረው የሰላም ጥረት ከዳር እንዳይደርስ ለማድረግ ያለመ መሆኑን አመልክተው፤የሽብር፣ የጽንፈኛ እና ለሌብነት ዓላማ የተሳሰሩ ቡድኖች በተናጠል እና በቅንጅት በአክራሪ ሚዲያዎች ታግዘው በሀገራችን በተለያዩ አካባቢዎች በተለይም በወለጋ አንዳንድ ቦታዎች ሁከትና ብጥብጥ በመፍጠር ንጹሓን ዜጎችን ገድለዋል፣ አፈናቅለዋል፤ በፀጥታ ኃይሎቻችን ላይ ጉዳት አድርሰዋል፤ የግለሰቦችንና የመንግሥት ንብረት አውድመዋል ብለዋል።

ይህን እኩይ ድርጊታቸውን የትምህርት ተቋማትን ማዕከል ባደረገ አግባብ ወደ አዲስ አበባም ለማስፋፋት ከሰሞኑ አልመው እየሠሩ እንደሚገኙ ጠቁመው፤ የእነዚህ የሽብርና የጽንፈኝነት ኃይሎች ዋና ዓላማ መንግሥት በሌብነት ላይ የከፈተው ዘመቻና በሰሜኑ የተጀመረው የሰላም ጥረት ከዳር እንዳይደርስ ለማድረግ ያለመ ነው ብለዋል ሚኒስትሩ።



የመላ ሕዝባችን ተጠቃሚነት የሚረጋገጠው ከዘላቂ ሰላም ፣ኅብረ ብሔራዊ አንድነት፣ ጥቅሞችን በማጣጣም፣ ከእኩልነትና ከጋራ ልማት ጋር ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ ለዚህ መርሕ ሁሉም የድርሻውን መወጣት አለበት። ከዋልታ ረገጥ ፖለቲካ መጠቀም የሚችሉት በጥቅም ትስስር ውስጥ ያሉ ጥቂት ግለሰቦች መሆናቸውን ገልጸዋል።

ኅብረተሰቡ በተለይም ወጣቶች ከልዩ ልዩ አሉባልታዎችና ሐሰተኛ መረጃዎች ስርጭት ራስን በመጠበቅ፣ አንድነቱን በማጠናከር በሽብርና ጽንፈኛ ቡድኖች እንዲሁም በሌብነት ላይ መንግሥት የጀመረውን ዘመቻ መደገፍ እና ማገዝ እንደሚኖርበት ገልጸው፤ የትኞቹም ሚዲያዎች ኅብረተሰቡን ጥላቻ ላይ ወደተመሠረተ ግጭት ከሚያስገቡ ቅስቀሳዎች መቆጠብ ይኖርባቸዋል። ከዚህ አልፈው የሚሄዱትን ለመላው ሕዝብ ደህንነት ሲባል ሕጋዊ እርምጃ ይወስዳል ብለዋል።

ጥያቄዎቻቸውን በውይይት፣ በድርድር እና ሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ለሚፈልጉ ኃይሎችም በሩ ክፍት መሆኑንም ጠቁመዋል።

# በቤተ ዕምነቶች አካባቢ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ይቀጠራል ያሉት ሼህ አብዱልሐሚድ፤ አንድ ሰው ያለችሎታው ሲቀመጥ የሚጎዳው ሕዝብና ሃገርን ነው ብለዋል።

እንደ ሼህ አብዱልሐሚድ ገለጻ፤ ሙስናን በመከላከል ረገድ የሃይማኖት አባቶች ሀገራዊና ሃይማኖታዊ ኃላፊነታቸውን እስካሁን በአግባቡ ተወጥተዋል ተብሎ አይታሰብም። በቤተ ዕምነቶች ሙሰኛውን ከማጋለጥና ባለፈ፣ አማኞቻቸውን ስለሙስና የተወገዘ ተግባር መሆኑን በማስተማር ረገድ ክፍተት አለባቸው።

የሙስና ፈጻሚዎች ማለትም ገንዘብ ሰጪ ፣ ተቀባይና በመሐል ያሉትን ደላሎች አሊያም አቀባዮች በማጋለጥና በመታገል ረገድም ሰፊ ሥራ ይጠይቃል ሲሉ ገልጸዋል።

ሙስናን በተግባርም ሆነ በአስተሳሰብ ደረጃ መከላከል ረገድ ደግሞ የሃይማኖት አባቶች ኃላፊነት የጎላ ነው ነው ያሉት ሼህ አብዱልሃሚድ፤ ይህን ኃላፊነታቸውንም በአግባቡ ሊወጡ እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

የኢትዮጵያ የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ የሰላም ግንባታ መምሪያ ምክትል ኃላፊና የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት መምህር አዳነ ደቻሳ በበኩላቸው፤ ከሙስና ነፃ የሆነ የእምነት ተቋም በኢትዮጵያ አለ ብዬ አላስብም፤ ችግሩ በእኛም የዕምነት ተቋማት ውስጥ አለ ብለዋል።

በተለይ አዳዲስ የማምለኪያ ቤቶች አሊያም “ቸርች” የሚከፍቱ ሰዎች የቸርች ባለሃብት እስከመባል ደርሰዋል። እነዚህ ሰዎች በሃይማኖት ምክንያት የደሃውን ገንዘብ በመሰብሰብ ያለአግባብ የሚበለጽጉ ናቸው ብለዋል።

አንዳንዶቹ ደግሞ ገንዘቡንም ብቻ ሳይሆን መገናኛ ብዙኃንንም በመቆጣጠር የማጭበርበር ተግባራቸውን ማጠናከራቸውን መምህር አዳነ ደቻሳ ተናግረዋል።

የእምነት ተቋማትም ሙስናን መታገልና ማውገዝ ሲገባቸው ራሳቸው በሙስና ውስጥ ሲዘፈቁና ምሳሌነት የጎደለው ተግባር ሲፈጽሙ ተስተውሏል። በመሆኑም የአገሪቷን የሙስና ችግር ለመፍታት የሃይማኖት ተቋማት ቀዳሚ ሆነው ሊሰሩ እንደሚገባ ምክር ሰጥተዋል።

ለእኛ ሳይሆን ለእኔ ብቻ የሚሉ በመብዛታቸውና ስግብግብነቱ በማየሉ በሙስና ምክንያት ሕዝቡ ችግር ላይ ወድቋል ያሉት መምህሩ፤ በእምነት ተቋምትና ግለሰቦች ዘንድ የተንሰራፋውን ሙስና ለመቀነስ ንጹህ ሆነው የሚሰሩ የኃይማኖት አባቶች ሰፊ ጥረት ሊያደርጉ ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

በእስልምናውም ሆነ በክርስትናው ዕምነቶች ሙስና የተወገዘና ከበጎ ስነምግባር ያፈነገጠ ተግባር ነው ያሉት የሃይማኖት አባቶቹ፤ መንግስት ከሚያደርገው ጥረት ባሻገር የእምነት ተቋማትም አስተምሯቸውን በተከተለ መንገድ አጥፊዎችን ማጋለጥና ችግሩን መከላከል እንዳለባቸው ገልጸዋል።

# በተቋማት ቅንጅት...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ፕላን አለመኖር እና ይህን ተከትሎ በሁሉም የፕሮጀክት የሕይወት ዑደት ደረጃዎች (አነሳስ/ጽንሰት፣ እቅድ፣ ዲዛይን እና ትግበራ) ውስጥ በተለያዩ የመሠረተ ልማት ግንባታ ፕሮጀክቶች ባለድርሻ አካላት መካከል ያለውን ቅንጅት አነስተኛነት፣ የሕግ ማዕቀፍ ክፍተት፣ የዳበረ የመሠረተ ልማት መረጃ አለመኖር እና በሴክተሮች መካከል የተፈጠሩ ግንኙነቶች ተቋማዊ አለመደረግ እና ውጤታማ አለመሆን ዋና የቅንጅት መጓደል ምክንያት መሆናቸውን አሳይቷል።

ይህ ገንዘብ ለአዲስ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ማስፋፊያ ሥራ ላይ ሊውል ቢችል 1100 መካከለኛ መስመር መዘርጋት የሚያስችል ምሰሶዎችን መግዛት ያስችላል ያለው ጥናቱ፤ በሌላ መንገድ ከሰብስቴሽን 40 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ለሚገኙ አምስት ከተሞች በየአምስት ኪሎ ሜትር ርቀት የ23 ኪሎ ሜትር የዝቅተኛ መስመር ማዘርጋት የሚችል እንደሆነም ጥናቱ ይጠቁማል።

ሌላው የቅንጅት ማነስ ከሚያስከትላቸው ጉዳቶች አንዱ የፕሮጀክት መዘግየት እና በዚህም ሳቢያ ወጪ እና ጊዜ መናር እንደሆነ በጥናቱ ተጠቁሞ፤ ለአብነት በጥናቱ ከተዳሰሱ 242 የመንገድ ፕሮጀክቶች በእቅድ ከተያዘላቸው የፕሮጀክት ወጪ ባሻገር ከ7 እስከ 205 በመቶ ጨምረው መገኘታቸውን ጠቁሟል።

የመንገድ ፕሮጀክቶቹ በአማካይ 140 በመቶ ከበጀት በላይ (cost overrun) የተጠቀሙ ሲሆን፤ እጅግ የተጋነነ ወጪ የታየባቸውን ፕሮጀክቶች በማስወገድ ሲሰላ ደግሞ 102 በመቶ እንደሆነ ጥናቱ ያሳያል ተብሏል።

እነዚህ የመንገድ ፕሮጀክቶች በአማካይ ከታቀደላቸው ጊዜ በ2 ነጥብ 44 ዓመታት ዘግይተው እንደተጠናቀቁ በጥናቱ ተጠቅሶ፤ ከአብዛኞቹ የምስራቅ አፍሪካ ሀገራት የመንገድ መሠረተ ልማት ጋር ሲነፃፀር ደግሞ "ኢትዮጵያ የመንገድ ፕሮጀክቶቿ ለተጨማሪ ወጪ የተዳረጉ ናቸው" ብሎ መደምደም እንደሚያስችል የጥናቱ ግኝት ያሳያል።

ፕሮጀክቶች የሚዘገዩት እና ከተያዘው በጀት በላይ ወጪ እንዲወጣ የሚያደርጉበት ምክንያት ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ሲሆኑ ጥናቱ የለያቸው ዋና ዋናዎቹ፤ ተገቢ ያልሆነ እና ደካማ የፕሮጀክት አዋጭ ጥናት፣ ከእውነታው የራቀ እና ተገቢ ያልሆነ እቅድ ማውጣት፣ ደካማ ክትትል፣ ግምገማ እና የኮንትራት አስተዳደር እንዲሁም የተዘበራረቀ ተጠያቂነት መሆናቸውን ጠቁሟል።

ከዚህም ጎን ለጎን የፋይናንስ አቅም እና የምርታማነት ውስንነት፣ የባለድርሻ አካላት ቅንጅታዊ አሠራር እና ግንኙነት ደካማ መሆን፣ የዋጋ ግሸበት እና የግዥ ማጭበርበር ድርጊቶች ተጨማሪ ምክንያቶች እንደሆኑም አብራርቷል።

እነዚህን ችግሮች ለመፍታት ሁሉን አቀፍ የፖሊሲ ጣልቃገብነትን እንደሚጠይቅም ጥናቱ የመፍትሔ አቅጣጫ አስቀምጧል።

# ‹‹በእንስሳት ዝርያ ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

የአንዲትን ላም ምርታማነቷን ለመጨመር የሚያስችል ግብዓት ከውጪ በዶላር የሚመጣ በመሆኑ ተግዳሮት መሆኑን አመልክተዋል።

የግብርና ሚኒስትሩ አቶ ዑመር ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ባደረጉት ቆይታ እንዳስታወቁት፤ ኢትዮጵያ ካላት የእንስሳት ቁጥር ብዛት አንጻር ሲታይ ተጠቃሚ እየሆነች አይደለም።

ዝርያው ያልተሻሻለና ምርታማነቱ አነስተኛ የሆነ እንስሳ ቁጥር መያዝ በራሱ መጥፎ ባይሆንም ቁጥር ብቻ ግን ተጠቃሚ አያደርገንም።

ላለፉት 68 ዓመት እና ከዚያ በላይ የእንስሳት ዝርያ ማሻሻል ላይ የተሠራ ቢሆንም ካለን የእንስሳት ሀብት አኳያ እስካሁን የተሻሻለው ዝርያ ያለበት ደረጃ አምስት በመቶ መሙላት አልቻለም።

ከዚህ አንጻር የእንስሳት ሀብቱ አለን ከማለት ያለፈ ከውጭ የሚገባውን ወተት ከመተካት አንጻር እንዲሁም ለምግብና ሥርዓተ ምግብ ደህንነት በቂ ነገር ማግኘት ባለመቻሉ ከዓመት በፊት የሴክተሩን ባለሙያ ያሳተፈ ሥራ መጀመሩን ገልጸዋል።

የእንስሳትን ምርታማነት ለማሳደግም የዝርያ ማሻሻል ሥራ ማስፋት ላይ መሥራት ይጠበቃል ብለዋል።

ይህንን ሥራ ውጤታማ የሚያደርገው ደግሞ የአስተሳሰብ ለውጥ ማምጣት ሲቻል መሆኑን ተናግረዋል።

አቶ ዑመር፣ አብዛኛው የወተት ምርት ስናይ በጣም ብዙ ቁጥር ያለውን የቀንድ ከብት እንደያዘ ዓይነት አይደለንም።

በቀንድ ከብት ቁጥር ከአፍሪካ አንደኛ፣ከዓለም ደግሞ ሰባትና ስምንተኛ አካባቢ ተቀምጠናል፤ ይህን የከብት ብዛት ይዘን በቀን በአንዲት ላም አንድ ነጥብ 5 ሊትር ወተት እያመረትን ከብት አለን እያልን እያወራን መኖር አንችልም ብለዋል።

ዝርያውን በማሻሻል ሌሎቹ እንዳደረጉት ከ15 እስከ ሃያ ሊትር ወተት በቀን ወደማግኘት መምጣት መቻል አለብን ሲሉ ጠቅሰው፤ ይህ ካልሆነ ከውጭ የሚመጣውን የወተት ዱቄት ዶላር እያወጣን እንድንገዛ እንገደዳለን ብለዋል።

እርሳቸው እንደተናገሩት፤ ወተት ልማት ላይ በዓለም አቀፍ ስታንዳርድ በዓለም የምግብ ድርጅት የተቀመጠው አንድ ሰው በዓመት በአማካይ በነፍስ ወከፍ ሊያገኝ የሚገባው 200 ሊትር ነው።

ኢትዮጵያውያን ያለንበት በዓመት በአማካይ ሲታይ ገና 60 እና 70 ሊትር አካባቢ ያላለፈ ነው።

ይህ ማለት ደግሞ የተሻለ ሊያስቡ የሚገባቸው ታዳጊ ሕጻናት በምግብና ሥርዓተ ምግብ ደህንነት በበቂ ሁኔታ ተደግፈው አለመምጣታቸውን የሚያመላክት ነው።

በመሆኑም ሌሎች የምግብና ሥርዓተ ምግብ ደህንነት የሚያረጋግጡ ፓኬጆች እንደተጠበቁ ሆነው የወተት ልማት ላይ ውጤት ለማምጣት ግን በሚቀጥሉት አራት ዓመታት አሁን ካለንበት 6 ነጥብ 9 ቢሊዮን ሊትር ዓመታዊ ምርት አካባቢ ወደ 11 ነጥብ 7 ቢሊዮን ለማምጣት እየተሠራ ነው።

እንዲህ ሲባል ግን ዝርያ ላይ፣ የእንስሳት ጤና ላይ እንዲሁም መኖ ላይ ሠርተን ነው ያሉት አቶ ዑመር፣ እንደእሱ ካልሆነ ዝም ብሎ የአንድን ላም ምርታማነት በአማካይ ከምትሰጠው 1 ነጥብ 5 ሊትር በአንዴ ወደ አምስትና ስድስት ማምጣት አይቻልም ብለዋል።

ይህ ሥራ በአግባቡ እየተሠራ ሲሆን፣ በአሁኑ ሰዓት ወደ ሕዝብ ዘንድም መውረዱን አስረድተዋል።

ሚኒስትሩ እንደገለጹት፤ ስራው በአሁኑ ወቅት ብዙ ፈተና አለው። ለአብነትም አንዱ የግብዓት ፈተና ነው።

ዝርያ ለማሻሻል ሲታሰብ ልክ እንደ ማዳበሪያ የሚፈትን ነገር አለ፤ ዝርያ ለማሻሻል ሲፈለግ በሀገር ቤት እንደ የቦረና አይነት ዝርያ መኖሩ የሚታወቅ ቢሆንም ነገር ግን የራሳችንን ላም ምርታማነቷን ለመጨመር የሚያስችል ግብዓት ከውጪ በዶላር የሚመጣ በመሆኑ ተግዳሮት ነው።

ይህንን ግን መንግሥት ተረድቶ በጀት በመመደብም እየፈታው ከሄደ ተስፋ የሚጣልበት ነው።

ምክንያቱም የሥራ እድል ፈጠራውም የገቢ ምርት መተካቱ ላይም እየተሻሻለ የሚሄድበት ነገር ይፈጠራልና።

በአሁኑ ሰዓት እየሠራን ያለነው ይህንን ቢሆንም ገና በጅምር ያለና ያልከፈለን ሥራ መሆኑ የሚታወቅ ነው ብለዋል።

በዘርፉ ያሉ የእንስሳት ሀብት ባለሙያዎች ለዓመታት ብዙ ሳይንቀሳቀሱ መቆየታቸውን አስታውሰው፤ አሁን ግን ጊዜው መምጣቱን ተናግረዋል።


በየሚዲያውና በየስብሰባው የምናሰማው ጥሪ ቢኖር ጊዜው ከመጣ ዳር ቆሞ ሌላውን ተወቃሽ ማድረግ አለመጥቀሙ ነው፤ ስለሆነም ወደዘርፉ መሠማራት መልካም መሆኑን ገልጸዋል።

ይህን ማድረግ ከተቻለ የዛሬ ሦስትና አራት ዓመት ገደማ ምንም እንኳ ድካም የሚጠይቅ ቢሆንም ስለስኬታቸው የሚወራበት ጊዜ እንደሚሆን ሚኒስትሩ አቶ ዑመር አስረድተው፤ ሁሉም ባለድርሻ ግን የየበኩሉን ቁርጠኝነት እንዲያሳይ ጥሪ አቅርበዋል።

ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠትም ውጤት እስኪመጣ ድረስ መታገል እንጂ ያዝ ለቀቅ ማድረግ እንደማይገባ ተናግረዋል።

# ከሱስ የተረፈች ነፍስ

እፀገነት አክሲሉ



ከእንቁላል ፋብሪካ ወደ ሩፋኤል ቤተክርስቲያን የሚያስኬደውን ቀጭን አስፋልት ይዘን እየወጣን ነው፤ ትንሽ እንደተጓዝንም የምንፈልገውን ቦታ ወይም ቤት ያገኘን መሰለንና መኪናችንን አቆምን። በእርግጥ የምንፈልገውን ቤት አግኝተናል። ይህ ቤት ምናልባትም በተለያየ ምክንያት የህይወት መንገዳቸውን ስተው በደባል ሱስ ውስጥ ገብተው ብዙ ነገራቸው የተበላሸ፤ ከመኖር ወዳለመኖር ሊሸጋገሩ የነበሩ የህብረተሰብ ክፍሎች እያገገሙበት ያለ ቤት ነው። ቤቱ ለሰዎቹ ተስፋ ሆኗቸው ከገቡበት ሱስ ሊያላቅቃቸው ግብ ግብ ላይ ያለም ነው።

ቤቱ የውጭ በሩ ግጥም ብሎ ተዘግቷል። ለመዘጋቱ ደግሞ ምክንያት አለው። በውስጡ ያሉት ሰዎች ጥበቃና እንክብካቤ የሚሹ ምስጢራቸው ከዛ ግቢ መውጣት የሌለበት ስለሆኑም ጭምር ነው።

እኛ ደግሞ እዚህ ቤት የተገኘነው ቀድመን ፈቃድ አግኝተን ነውና በሩን ለማንኳኳት አልፈራንም። አዲስ ህይወት የአልኮል መጠጥና የአደንዛዥ እፅ የቅድመ መከላከልና የተጠቂዎች የማገገሚያ ማዕከል ስሙ ነው። በርካቶች እያገገሙበት፣ ከተሳሳተው መንገዳቸው ተመልሰው ቀናውን መንገድ እያዩበት፣ ያለፉትን ህይወት እየኮነኑ የነጋቸውን ብሩህነት አሻግረው እያዩበት ነው።

የተዘጋውን በር አንኳኩተን ተከፈተልን፤ ለከፈቱልን ጎልማሳ ሰውም የመጣንበነትን ምክንያት ብሎም ቀጠሮ የተያዘልን መሆኑን ነግረን እንድንገባ ፈቅዱልን። አመስግነን ወደውስጥ ዘለቅን። በድንጋይ የታነጸው ቤት ከውጭ ሲታይ ያምራል፤ ወደውስጥ እንድንዘልቅ ጥበቃው ፊት ፊታችን ይመሩናል፤ እኛም ወደመሩን እየሄድን ዙሪያ ገባውን እንቃኛለን፤ ቤቱ የጋራ የሚባል ሳሎን አለው፤ ሳሎኑ የትኛውም ቤት ሊኖር በሚችል እቃ ተሟልቶለታል። ከዛ ቀጥሎ የነርሶች ክፍል የዋና ዳይሬክተርና የፋይናንስ ቢሮዎችም አሉ።

በሱስ የተጠቁ አሁን በማገገም ላይ ያሉ ሰዎችም ግማሾቹ የመኝታ ክፍሎቻቸውን ያጸዳሉ፤ ሌሎቹ ደግሞ የጠዋቷን ጸሀይ እየሞቁ እርስ በእርሳቸው ይጨዋወታሉ። እኛም ጠጋ ብለን ሰላምታ ከሰጠናቸአው በኋላ ከየት እንደመጣን በመግለጽ ትውውቅ አደረግን። ከመካከላቸውም ያለፉበትን የሱስ መንገድ አንስተው ከእኛ ሌሎች እህት ወንድሞቻችን ይማሩ ማንም በሱስ ውስጥ መግባት የለበትም የሚለውን መልዕክት ሊያስተላልፉልን ዝግጁ መሆናቸውን ጠየቅን። ወጣት አሉላ በላይ ሙሉ ፈቃደኛ መሆኑን ገልጾልን ተያይዘን ለመጨዋወት በሚያመቸን ቦታ ላይ ቁጭ አልን።

አሉላ በላይ የ36 ዓመት ወጣት ነው። ተወልዶ ያደገው አዳማ ከተማ ነው። ቤተሰቦቹ እሱን ጨምሮ ስድስት ልጆችን ወልደዋል። እርሱ ደግሞ የመጨረሻ ልጅ ነው። አሉላ የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን እዛው አዳማ ከተማ በሆተ ጥበብና በአዳማ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተከታትሏል። በትምህትርት ሰነፍም ጎበዝም ሳይሆን በመካከለኛ ደረጃ ትምህርቱን ተምሯል።

“......በወቅቱ የትምህርት ጥቅም ባይገባኝም ለቤተሰቦቼ ስል መማር እንዳለብኝ አስብ ነበር። ከዚህ የተነሳም አነባለሁ የቤት ስራ ሰርቼ እሄዳለሁ በጠቅላላው የተጣለብኝን የተማሪነት ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት የምችለውን ሁሉ በማደረግ በትምህርቴም ጥሩ የምባል ነበርኩ” ይላል።

ነገር ግን በ1996 ዓ.ም የ10ኛ ክፍል ማጠናቀቂያ ፈተና ወስዶ ወደ መሰናዶ ትምህርት የሚያስገባ ውጤት ባለማግኘቱ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ቤት ይገባል። በዚህ ሁኔታ እምብዛም ደስተኛ ባይሆንም የነበረው አማራጭ ግን መማር ብቻ ሆነ።

አሉላ አባቱን በ1994 ዓ.ም ነው በሞት ያጣው። ከዛን በኋላ ያለውን ጊዜ ልጆችን የማሳደግ የማስተማር ኃላፊነቱ የወደቀውም በእናቱ ላይ ነበር፤ ይህም ቢሆን ግን እናቱ በጣም ታታሪና በጣም ጎበዝ ስለነበሩ የባለቤታቸውን ሀዘን ችለው ልጆቻቸው ከትምህርት እንዳይቀሩ እንዳይጎልባቸው የቻሉትን ሁሉ ያደርጉም ነበር። አሉላ እናቱ ልጆቻቸውን ለማሳደግ የሄዱበትን መንገድና ያሳለፉትን ነገር ሲያስብ እጅግ ይገረማል የእኔ እናት የጀግኖች ጀግና ናትም ይላል።

“.....እናቴ ለእኔ ጀግናዬ ናት። እንደውም እሷን መግለጫ ቃላት ያጥረኛል፤ አባታችን ከሞተ በኋላ እኛን ለማኖር የሄደችበት መንገድ እጅግ የሚገርም ምናልባትም በጣም ጥበብና የፈጣሪ እርዳታ የታከለበት ሆኖ ይሰማኛል “ ይላል።

አሉላ የቴክኒክና ሙያ ትምህርቱን ቢያጠናቅቅም በ1998 ዓ.ም በግሉ ፈተናውን የ10ኛ ክፍል ማጠናቀቂያ ፈተናን ዳግም ተፈትኖ ወደመሰናዶ ትምህርት የሚያስገባውን ውጤት አመጣ።

እዚህ ላይ ግን አሉላን ከመንገድ የሚያወጣ ምናልባትም አሁን ላለበት ደረጃ ያበቃውና ከፍ ያለ ስነ ልቦናዊ ኢኮኖሚያዊ እንዲሁም ማህበራዊ ቀውሶችን ይዞበት ወደመጣው ሱስ ገባ። አሉላ ለጥናት ብሎ የጀመረው ጫት እንደቀልድ ጣፈጠው፤ ከመጣፈጥም አልፎ በቁጥጥሩ ስር አዋለው። ይህ የጫት ሱስ ደግሞ ሌሎች ደባል ነገሮችንም ጎተተበት፤ ቀኑን በመቃም ምሽቱን ደግሞ እሱን ለመስበር በሚል በመጠጣት ማሳለፍ የቀን ተቀን የኑሮው ሂደቱ ሆነ። በጣም የሚገርመው ግን በዚህ ሁሉ ሱሶች ውስጥ ሆኖ አንድም ቀን ትምህርቱን ስለማቋረጥ አስቦ አለማወቁ ነው። የመሰናዶ ትምህርቱን በአግባቡ ይማራል፤ ክፍል ይገባል፤ ከትምህርት ጓደኞቹም በእውቀት አይተናነስም። ነገር ግን ከትምህርት ቤት ሲወጣ እነሱ ወደ ቤታቸው እሱ ደግሞ ሱሶቹን ሊያስተናግድባቸው ወደሚችሉት ቦታዎች መሄዱ ልዩነት ፈጠረ።

“.......በወቅቱ ገንዘብ እንኳን ባይገኝ በቀላሉ ጫት ይገኝ ነበር። አንዱ ጓደኛም ገንዘብ ካለው ለሁሉም ይተርፋል፤ በጠቅላላው ለሱስ ሲሆን ምንም አይጠፋም” በማለት ይገልጸዋል።

“ውሃ ሲወስድ አሳስቆ” እንደሚባለው አሉላም እንደ ቀልድ ለጥናት ብሎ የገባበት የጫት ሱስ በቀላሉ የሚተወው አልሆነም። እንደውም ከቀን ቀን ፍጆታው እየጨመረ ከጫትና ከጫት ቃሚዎች ጋር አብሮ የሚያሳልፈው ሰዓት እየረዘመ መጣ። አሁን የመሰናዶ ትምህርቱን አጠናቆ የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተናንም ወስዶ አልፏል። ምድቡም ሃዋሳ ዩኒቨርሲቲ መሆኑ ታውቋል። ሊማር የተመደበበት የትምህርት ዘርፍ ደግሞ ሲቪል ኤንድ አርባን ኢንጂነሪንግ ነው። በውጤቱም በተመደበበት የትምህርት ዘርፍም ደስተኛ ነበር።

“ .....በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የጀመርኩትን የጫትና የሌሎችም ነገሮች ሱስ ዩኒቨርሲቲ ስገባ አጠናከርኩት። እረ እንደውም በራሴ መንገድ ህጋዊ ሁሉ አደረኩት። ማንንም ሳልፈራ በልበ ሙሉነት መቃም መጠጣት ስራዬ ነበር። ገንዘብ እንደሆነ ለሱስ አይጠፋም፤ከእኔ ቀድመው ዩኒቨርሲቲ ገብተው የወጡ ጓደኞቼ ይሰጡኛል። እናቴም እህት ወንድሞቼም በሚችሉት አቅም ይልኩልኛል። በተለይ አንዷ እህቴ ዱባይ ስለነበረች በተወሰኑ ጊዜያት ልዩነት ገንዘብ ትልክልኝ ነበር፤ በወቅቱም በትንሽ ገንዘብ በአራት ብር ብዙ ጫት መግዛት ይቻላል፤ ብቻ ገንዘብ አይጠፋም፤ ከጠፋም ደግሞ ሌላ መንገድ ይፈጠራል። በቃ ለሱስ እና ለቀብር ገንዘብ አይጠፋም” በማለት ያለፈበትን መንገድ ይገልጻል።

ወጣት አሉላ ይህንን መሰል ህይወት ውስጥ ይኑር እንጂ በዩኒቨርሲቲ ቆይታው ለትምህርቱ ላቅ ያለ ትኩረትን ነበር የሚሰጠው። ጓደኞቹ ከተመረቁበት ጊዜም አንዲት ሴሚስተር እንኳን ሳይጨምር 2 ነጥብ 9 ውጤት ይዞ ስለመውጣቱ ይናገራል።

“በትምህርትማ ቀልድ አላውቅም። ጠዋት ክፍል እገባለሁ እማራለሁ፤ ከሰዓት በኋላ ምሳዬን እንደበላሁ የማጠናውን ወረቀት ይዤ ጫት ቤት እሄዳለሁ፤ እዛ እያጠናሁ እቅማለሁ። ግን ከወጣሁ በኋላ ያ ሁሉ ጥንካሬዬ ጠፍቶ ከባድ የሱስ ወጥመድ ውስጥ ወደኩ፤ እሱም ለአሁኑ ለተበላሸው ህይወቴ አበቃኝ” ይላል።

ከሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ በሲቪል ኤንድ አርባን ኢንጂነሪንግ እንደተመረቀ በቀጥታ ከሰም ስኳር ፋብሪካ ነበር ስራ የጀመረው። በወቅቱም ይከፈለው የነበረው ደመወዝ በጣም ትልቅ ስለነበር ይዞት የገባውን ሱስ አጠናክሮ ለመቀጠሉ መደላድሉን ፈጠረለት።

“ .....አሁን እያነበብኩት ያለሁት መጽሀፍ አለ በእውነት ከእኔ ህይወት ጋር የሚመሳሰል ነው። የመጽሀፉ ርዕስ “ሪች ዳድ ፖር ዳድ” ነው የሚለው፤ይህ መጽሀፍ ሰዎች በውል የማያውቁት “ዲዛየር” የሚባል በሽታ እንዳለ ይገልጻል፤ ይህ በሽታ ደግሞ ገንዘብ ችግርን የሚፈታ እንዲመስለን የሚያደርግ ነው። ነገር ግን ገንዘብ ሲመጣ ችግሮቹም ቀዳዳዎቹም ይበዛሉ፤ አንድ ሰው ቮልስ ቫገን ይነዳ ከነበረ ልክ ገንዘቡን ሲያገኝ የተሻለ መኪና ያምረዋል እንደማለት ነው፤ እኔም በፊት በማገኘው ገንዘብ እጠቀማቸው የነበሩ አደንዛዥ ነገሮች አቅሜን ያገናዘቡና መጠናቸው ትንሽ ነበር፤ ነገር ግን ገንዘብ ከተገኘ በኋላ ጥፋቱም የዛኑ ያህል ጨመረ” ይላል።

ወጣት አሉላ እንደ ቀልድ ብዙ ብዙ ጊዜዎቹ ባከኑበት “.... በጣም የሚገርመው ደግሞ ሱስ ውስጥ ያለን ሰዎች የሚያዘናጋን የራሳችን ጭንቅላት ነው። ሰውዬው በቃሲል ጭንቅላቱ ደግሞ እረ ዛሬ አይደለም ጊዜው አንተ እኮ በማንኛውም ሰዓት ከወሰንክ ማቆም ተችላለህ፤ ዛሬ ግን አታድርገው የሚል የተሳሳተ መረጃን ያቀብላል። በእንደዚህ አይነት ሁኔታ መሄዱ ደግሞ መመለስ ወደማይቻልበት መንገድ ያስገባል”።

ዛሬ ላይ አሉላ ያለፉትን ጊዜያት ሲያስባቸው ይገረማል በመባከናቸው ቢያዝንም ዛሬን ያሳየውን ከሱስ ወጥቶ ጥሩ ጭንቅላት ላይ ቆሞ እያመዛዘነ፤ ነገን እያቀደ፤ እያወጣ፤ እያወረደ መሆኑን ሲያስብ ደግሞ ተመስገን ይላል።

“.....ሱስ እንደዋዛ እያሳሳቀ ረጅም ርቀት ይዞ ይጓዛል፤ እኔም በዚህ ሁኔታ ረጅም ርቀት ከሄድኩ በኋላ ነቃ ብዬ ዞር ስል የመጣሁበት ርቀት በጣም ረጅም ነው። ረጅም ብቻም ሳይሆን በጣም አስፈሪ ከዛ ሁሉ በላይ ደግሞ በዚህ በተሳሳተ መንገድ ስጓዝ ተው ጥሩ መንገድ ላይ አይደለህም ሲሉኝ በመንገዴ ውሃ ሲያቀብሉኝ የነበሩ ሁሉ ተሰላችተው ደክሟቸው ትተውኛል። በቃ ልመለስ ስል እነዛ ሰዎች ከጎኔ የሉም። ይህ ደግሞ የሰሃራ በረሃ ላይ ብቻ እንደመጣል አይነት ስሜት እንዲሰማ ያደርጋል። በዚህ አጋጣሚ ደግሞ ሱሱ በግላጭ አግኝቶ ይጫወትብናል” በማለት ስለ አስፈሪው ጊዜው ይናገራል።

አሉላ በተለይም በዚህ ሱስ ውስጥ ሆኖ መውጣት ሲያቅተው ታላቅ ወንድሙ ቴዎድሮስ በላይ ያደረገለትን

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

ብሎም የለፋውን ልፋት መርሳት ይከብደዋል። ነገር ግን ብዙ ቢታገልም እሱ ዝግጁ ስላልነበር ውጤታማ ሳይሆን ቀረ።

አሉላ በከፋ የሱስ መንገድ ራሱን ጥሎ ከቤተሰቡ ተነጥሎ ቆይቷል። ሰው ቢታመም፣ ቢወልድ፣ አይጠይቀም። ቢሞት ለቅሶ አይደርስም።ሰርግ፣ ምርቃት፣ ክርስትና የመሳሰሉት ነገሮች እሱ ጋር ቦታ የላቸውም። የእሱ ቤተሰብ የቅርብ ጓደኛ ብቻ ከጎኑ ሆኖ በርታ ግፋበት የሚለው ሱሱ ነበር። አሉላም እጅ ሰጥቶ ስለነበር ከሱስ ለመውጣት ቢያስብ እንኳን መንገዱን ስለማያውቀው ከመኖር ወዳለመኖር የሚሸጋገርበት መንገድ ላይ ደርሶም ማቆም አልቻለም ነበር። እሱ እንደሚለው የፈጣሪ እጅ ገብቶበት አትሙት ጠፍተህ አትቅር ሲለው ግን አንድ አጋጣሚ ወደህይወቱ መጣ። አሉላ አጋጣሚውን ዛሬ ላይ ቆሞ ሲያስበው እውነት ሁሉ አይመስለውም።ህልም ከህልምም የማይጨበጠው ቅዠት ይመስለዋል። ግን ሁሉም ነገር እውነት ነበር።

### የልጅነት ጓደኛ ውለታ

አለም ፈርሳ ድጋሚ ብትሰራ ሁሉ ለእኔ እንደ ልጅነት ጓደኛዬ አብሮ አደጌ ክብሮም ሃጎስ የሚያስገርመኝ ይፈጠራል ብዬ አላስብም። ክብሮም የልጅነት ጓደኛዬ ነው። እሱ ያደረገልኝን በአንደበቴ መግለጽ ይከብደኛል።በቀላሉ ከሞት ወደህይወት መልሶኛል። እኔ ክብሮምን ቀሪ ዘመኔን እንኳን የእሱ አገልጋይ ሆኜ ብቀር ውለታውን የምከፍለው አይመስለኝም።

ክብሮም ሀጎስን ሁለት ዓመት እበልጠዋለሁ ታላቁ ነኝ፤ ግን ደግሞ ሁሉም ሰው ስለእኔ ሰልችቶት በምክርም በድጋፍም ፊቱን ባዞረብኝ ወቅት የደረሰልኝ ነው። ሳይታክት ፈልጎ አግኝቶኝ ያለሁበትን ሁኔታ አይቶ ሳይጠየፍ እንደውም ሁለመናዬን ቀይሮ አንደኛ ሚዜው አድርጎኝ ሰው ፊት አቀረበኝ።

በወቅቱ እኔ የነበርኩበት ሁኔታ እንኳን ሰው የተሰበሰበበት ቦታ ሚዜ ሆኜ ልቆም ቦታ ጠፍቶሽ አቅጣጫ ለመጠየቅ የምትመርጪኝ ሰው አልነበርኩም። እሱ ግን ይህንን ሳያይ የልጅነት ጓደኛዬ ሚዜዬ ሆኖ ካላጀበኝ ማን ሊያጅበኝ ብሎ መርጦኝ ሚዜ አደረገኝ። እሱ አይደለም የሚገርመው፤ አንድ ወር ከአንድ ሳምንት ቤቱ አስቀምጦኝ እራሴን እንድመለከት ከነበርኩበት ሁኔታ እንዳገግም ሰውነቴ እንዲመለስ ብዙ አደረገልኝ።

ክብሮም ኑሮው ከአገር ውጪ በመሆኑ ሊሄድ ሲል አንተን ሱስ ላይ ጥዬ ወይም ገንዘብ ሰጥቼ ሙት ብዬህ አልሄድም፤ ከዛ ይልቅ በደንብ የምትለወጥበት ቦታ አስገብቼህ ወደራስህ እንድትመለስ ሰርተህ መብላት የምትችልበት ቁመና ላይ እንድትደርስ አደርጋለሁ፤ብሎ መጀመሪያ ጳውሎስ ሆስፒታል ወሰደኝ፤ ከዛ ግን ወደ አዲስ ህይወት የሱስ ማገገሚያ ማዕከል ይዞኝ መጣ በማለት ጓደኛው ለእሱ የሆነውን ይናገራል።

አንዳንድ ጊዜ ሱሱ ሙሉ በሙሉ ወስዶሽ መተው በማትችይበት ወቅት ሰዎች ብዙ ጥረት ያደርጋሉ፤ነገር ግን ስኬታማ አይሆኑም።እኔ ደግሞ የነበርኩበት ሁኔታ ሰዎች ጥረት አድርገው ሰልችቷቸው የተውኝ ሰዓት ላይ ነበር በተቃራኒው ግን እኔ ደግሞ ከሱስ ጋር መኖሬ እጅግ ያንገፈገፈኝና የመረረኝ፤ማነው ከዚህ መከራ የሚያወጣኝ ብዬ ያልኩበት ወቅት ነበር ጓደኛዬ ወደእኔ የመጣው።

"…..ማንም ሰው በተለያዩ ሁኔታዎችና አጋጣሚዎች ሱስ ውስጥ ሊገባ ይችላል፤ በዛ ሂደትም የነበረውን ነገር ሁሉ ቀስ በቀስ እያጣ ይሄዳል። ከሁሉም በላይ ግን አጥቶ አጥቶ ከነበረው ነገር ቀንሶ መሬት ላይ ሲደርስ ቆም ብሎ ማሰብ ይገባዋል። እኔ መሬት ደርሼ ነበር ስራዬንም ትቼ እነሱ እንኳን ጊዜ ሰጥተው ና ሲሉኝ እበሳጭ ነበር። ብቻ ለመጥፊያ አይጠፋምና ባልሰራም መጥፊያዬ በዝቶ ጠፍቼም ነበር" ይላል።

አሉላ በዛ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ አብረውት አፈር ፈጭተው ያደጉትን ልጆች ሲያይ የተሰማውን ስሜት መግለጽ ይከብደዋል። አብዛኞቹ በጣም ጥሩ ስራና የገቢ አቅም ላይ ናቸው፤ቤተሰብ መስርተዋል፤ ኑሯቸውን በሰላም ይኖራሉ፤ ከሱስ ነጻ ናቸው፤ መልካቸው፣ አለባበሳቸው በጣም ያምራል፤ እሱ ግን

…..እኔ እድለኛ ነኝ ዛሬን ለማየት በቅቻለሁ። የነበርኩበትን ዞር ብዬ ሳስበው ከሞቱት በላይ ካሉት በታች ነበርኩ፤ በሱስ ምክንያት ራሴን ያልሆነ ነገር ውስጥ አስገብቼ ነበር፤ አሁን ሳስበው ሱስ ምንም ጥሩ ነገር የሌለው ገዳይ ከሰው በታች የሚያደርግ አዋራጅ መንገድ መሆኑ ይሰማኛል

ከነሱ በተቃራኒው ነው፤ ስጋ ርቆት በአጥንቱ እየሄደ ነው፤ገንዘብ የለውም፤ እናቱን እህት ወንድሞቹን አስቀይሟል፤ ትዳር አልመሰረተም በጠቅላላው የእኔ የሚለው ነገር የለውም። ይህንን ሁሉ ዞር ብሎ እንዲያይ ያደረገው ደግሞ የክብሮም ሰርግ ነው።

ብዙ ሰው በገንዘብ አቅም ጓደኛ ሲበልጠው እኔስ ሊል ይችላል አሉላ ግን የእነሱ ገንዘብ አይደለም ያማረው ወይም እኔስ እንዲል ያደረገው ገንዘብን ጤናማ ሆኖም ጤናማ ሳይሆንም አገኝቶት ጤናማ አካባቢ ባለመዋሉ ያጣው ነገር ነው። አሉላ በዚህ አልተበሳጨም፤ ከዛ ሁሉ በላይ እኔስ እንዲል ያደረገው ጓደኞቹ በሙሉ ሰው ፊት ሊቀርብ የሚችል ቁመና ባለቤት መሆናቸው ነው። ይህ ሁኔታ ደግሞ በውሳኔው እንዲጸና ዳግም ወደሱስ እንዳይመለስ ከራሱ ጋር ቃል እንዲገባ አደረገው።

"…..እኔ እድለኛ ነኝ ዛሬን ለማየት በቅቻለሁ። የነበርኩበትን ዞር ብዬ ሳስበው ከሞቱት በላይ ካሉት በታች ነበርኩ፤ በሱስ ምክንያት ራሴን ያልሆነ ነገር ውስጥ አስገብቼ ነበር፤ አሁን ሳስበው ሱስ ምንም ጥሩ ነገር የሌለው ገዳይ ከሰው በታች የሚያደርግ አዋራጅ መንገድ መሆኑ ይሰማኛል" በማለት ይገልጸዋል።

### ሱስ ውስጥ ሳሉ

ማንኛውም ሰው መኖር ነው የሚፈልገው፤ መኖር የሚፈልግ ሰው ደግሞ በፍጹም ሱስ ውስጥ አይገባም። እኔ በወቅቱ ሱስ ገዳይ ነው ከሰው ያሳንሳል ተብዬ ብዙ ተለምኛለሁ፤ ተመክሬያለሁ፤ ነገር ግን አልሰማሁም። እኔ አሁን ለሌሎች የምናገረው ሱስ ሊያጠፋ ሲል ምልክት ያሳያል፤ ከማህበራዊ ህይወት ይነጥላል፤ ለቅሶ አያስደርስም ፣ ለሰው ግድ ማጣት ይፈጥራል፣ ራስን ያስጥላል ፣ ንጽህናን ለመጠበቅ ጊዜ አይሰጥም፤ እነዚህ ነገሮች ሲመጡ በሱስ ውስጥ ያለ ሁሉ ቆም ብሎ ሊያስቡ ይገባል።

"…ሌላው ጥያቄ መኖር ትፈልጋለህ፤ አትፈልግም የሚል ነው" መኖር የፈለገ ሰው ዛሬ ነገ ሳይል ከገባበት ሱስ ሊወጣ ይገባል። ምክንያቱም ሱስን እያስተናገዱ መኖር ስለማይቻል። አንዳንድ ሰዎች መከርን ይሉና አጉለው ይናገራሉ "ጫት ብቻ እኮ ችግር የለውም፣ መጠጥም ሳይበዛ ጥሩ ነው" ይላሉ ግን ልክ አይደለም፤ ምናልባት በደንብ እስኪይዝና ጉልበት እስኪያሳጣ ድረስ ማዘዝ ይቻል ይሆናል። ቀስ ብሎ ወደመሃል ካስገባ በኋላ ግን ማንኛውም ሱስ አዛዥ ይሆናል።

እኔ በከንቱ አስራ ምናምን አመቶቼ ጠፍተውብኛል። መሆን በሌለበት መንገድ ስራዬን ቤተሰቤን በጠቅላላው ማህበራዊ ግንኙነቴን አጥቻለሁ። ሌሎችም እኔን አይታችሁ ተማሩ ሱስ እያስተናገዱ መኖርን መምረጥ ስህተት ነው።

### ቤተሰብ ሲረዳው የሚገባው ነገር

ማንም ወላጅ ልጁን አሳደኩ ሊል የሚችለው ከ14 ዓመት እድሜው በኋላ ነው። ከ14 ዓመት በታች ያሉ ህጻናት በቁጥጥር ስር ስለሆኑ ማንም አያሳድጋቸውም ፈጣሪም ይጠብቃቸዋል። 14 ዓመት ሲሆን ግን የወላጅ የአስተዳደግ ጥበብ መገለጥ ይጀምራል። ከዛ በኋላ በወላጅ ፍላጎት መዝናናት ቀርቶ በልጁ ፍላጎት መሄድን ያስፈልጋል። ከልጆች ጋር መግባባት እንጂ ተቆጪ መሆን ዋጋ ያስከፍላል። ሌላው ወላጆች ልጆቻቸው ምንም ነገር ውስጥ ቢገቡ መውጣት እንደሚችሉ ከወዲሁ መንገር ማስተማር መቻል አለባቸው።

ከቤትሽ ጀርባ አንድ ትልቅ ተራራ አለ። ተራራውን መውጣት እየፈራሽ አልወጣሽም፤ ነገር ግን አንድ ቀን በሰዎች አደፋፋሪነት ወጣሽና ስታይው ውብ የመዝናኛ ቦታ ያለው ስፍራ ሆኖ አገኘሽው፤ከዛ በኋላ ማንም ሳትጠብቂ መመላለስ ጀመርሽ፤ ሱስም እንደዚሁ ነው። ወላጆች ለልጆቻቸው ጫትንም ሆነ ሲጋራን አግዝፈው ይነግሯቸዋል፤ ተጠቃሚውንም ሰው እንደሌላ ፍጡር ይስሉላቸዋል። በሆነ አጋጣሚ ልጆቹ ሲያዩት ግን ጭንቅላታቸው ውስጥ ትልቅ ቦታ ይሰጡታል፤ ከዛ መመለሱ ከባድ ይሆናል።

በመሆኑም ማንም ወላጅ ለልጁ መናገር ያለበት ሲወለድ ሲጋራ ጫት ወይም የአረቄ መለኪያ ይዞ የተወለደ አለመኖሩን ነው፤ ነገር ግን እድሜው ሲደርስ በአቻ ግፊትም ይሁን በሌላ ምክንያት ሊገባበት ይችላል፤ እንደ ወላጅ ቀደም ብለን ልንል የሚገባን ነገር "ልጄ ከእለታት አንድ ቀን ተሰናክለሽ ብትደፈሪ ተመልሰሽ ትቆሚያለሽ፤ ወንዱንም አንድ ቀን ተሳስተህ ሱስ ውስጥ ብትገኝ ነገ ትመለሳለህ" ማለት መቻል ያስፈልጋል። በመሆኑም ወላጆች ለልጆቻቸው ሊናገሩ የሚገባው ነገር ምንም ነገር ከቁጥጥራቸው ውጪ እንዳልሆነ የተበላሸ ነገር መስተካከል እንደሚችል ነው።

### ስለ አዲስ ህይወት የአጽና አልኮል ሱሰኞች ማገገሚያ ማዕከል

ብዙ ሰዎች ይህንን ተቋም አያውቁትም፤ እዚህ ማዕከል ውስጥ ለመምጣት ፍቃደኛ የሆነ ሱስ ውስጥ ያለ ሰው ሁሉ መዳን፤ ማገገም፤ ወደቀድሞ ስብዕናው መመለስ የሚያስችል ህክምናን ያገኛል። ስህተትን ማረሚያ መንገዶች አሉ። በሀይልና በጉልበት ከሱስ ለማስወጣት ከመሞከርም ወደዚህ ያሉ ተቋማት ማምጣት ጥሩ ነው። ከእኔ ተሞክሮ ልናገር በሱስ ውስጥ ካሉ ሰዎች መካከል 20 በመቶው በሚያደርጉት ነገር ደስተኞች አይደሉም። ምናልባት መርሳት የሚፈልጉት ነገር ይኖራል፤ አልያም መውጣት እንደማይቻል ሆኖ አእምሯቸው ውስጥ ቀርቷል። በመሆኑም ምንም ነገር ሳታከብዱ እኔ አለሁልህ ልጄ በማለት ከባለሙያ በመማከር ወደደዚህ አይነት ተቋም ማምጣት ያስፈልጋል።

በሌላ በኩል ሰዎች ወደዚህ አይነት ተቋም ሲመጡ ከ 90 በመቶ በላይ ስራው የራሳቸው በመሆኑ አእምሮን ማሳመን ወደቀደመው መንገድ መመለስ የሚያመጣውን ነገር ማወቅና መረዳት ወደኋላ ላለመመለስ መወሰን፤ እነዛን አስቀያሚ ጊዜያትን ማሰብ፤ ወደፊት ለመራመድ ደግሞ ራዕይ ማስቀመጥ ያስፈልጋል። መልካም ነገሮችን የሚያስቡና በስብዕናቸው ምሉዕ ከሆኑ ሰዎች ጋር መዋልና እነሱን ሞዴል ማድረግ ያስፈልጋል።

ማዕከሉም የማንበብ፤ ራስን የማዳመጫ ጊዜ ይሰጣል የስነ ልቦና አማካሪዎች አሉ፤ ስምንት ሰዓቱን የስራ ሰዓት ለማስለመድ ጥረት ይደረጋል። በጠቅላላው ማዕከሉ ከዚህ በበለጠ ቢጠናከር ብዙ ሰዎችን ማገልገል እና መመለስ ይችላል።

### መልዕክት

አገርን መለወጥ አቅም ያላቸው ሰዎች ሱስ ውስጥ አሉ፤ አገርንም እያጠፉ ያሉት ሰዎች በተመሳሳይ በሱስ ውስጥ ናቸው። ትልልቅ ፋርማሲስቶች ታማሚው እየተሰቃየ እነሱ በጎን መድሃኒት አውጥተው የሚሸጡት ለሱሳቸው ነው። የባንክ ማናጀሩ ለሚገባው ትቶ ለማይገባው ሰው ብድር የሚፈቅደው ለራሱ ሱስ ማስተናገጃ ስለሚያገኝበት ነው። ይህንን የምናገረው ዝም ብዬ አይደለም ከልምዴ ከአዋዋሌ ተነስቼ ነው።

በመሆኑም ይህ የሱስ ነገር ሁሉንም የሚነካ እንደ አገርም ብዙ ዋጋ እያስከፈለ ያለ ወደፊትም የሚያስከፍለን ነው። ይህም ቢሆን ግን እንደ አዲስ ህይወት አይነት ማዕከላት ብዙ የሉም። ጳውሎስ ሆስፒታል አገልግሎት ለመስጠት ቢሞክርም የሚመጡትን ታካሚዎች ባህርይ ያገናዘበ መስተንግዶ የለም። በሱስ የተጠቁ ሰዎች አሰልቺ ጊዜያትን ለማሳለፍ ይገደዳሉ፤ ይህ ደግሞ በሱስ ውስጥ ላለ ሰው ከባድ ነው። በመሆኑም ይህንን ሴክተር ማጠናከር ተነሳሽነቱን ወስደው የሚሰሩ ግለሰቦችን ማበረታታትና እነሱን መደገፍ ነገ አገር ተረካቢ ትውልድ እንዳናጣ ያደርጋል።

ሰው ወደሱስ እንዳይገባ ሰፈሩ ቁጭ ብሎ ድንጋይ እንዳያሞቅ ማድረግ ያስፈልጋል። በትምህርት ቤቶች ዙሪያ ያሉ ጫት ቤቶች መላ ሊመታላቸው ይገባል። ዛሬ አገር እየገነባን መንግስትም ብዙ ስራ እየሰራ ነው። ነገር ግን ስራው ውጤት የሚያመጣው ጤናማ ትውልድ መቀጠል ሲችል ብቻ ነው።

### የወደፊት እቅድ

ከዚህ በፊት በነበረኝ ህይወት ምንም አላፍርም፤ ብዙ ጥፋቶችንም አጥፍቻለሁ፤ ትናንት ከሞት ያልተናነሰ ህይወት ኖሬያለሁ፤ ማህበረሰቡም ላብድ ስል ቆሞ እያየኝ ነበር፤አሁን በአዲስ ህይወት የሚኖረኝን ቆይታ አጠናቅቄ ስወጣ ግን የራሴን ስራ መጀመር፤ በምችለው አቅም በሱስ ውስጥ ያሉ ጓደኞቼን መንገድ ማሳየት እቅዴ ነው።

# ኢትዮጵያዊ አንድነትን የሚያጎሉ እሴቶች

**ዳግም ከበደ**

ኢትዮጵያ የሺህ ዘመናት የአገረ መንግስት ታሪክ፣ ውብ ባህልና ማንነት ያላቸው ብሄሮች፣ብሄረሰቦችና ህዝቦች በጋራ ተዋደውና በአንድነት ሆነው የሚኖሩባት አገር ናት። ህዝቦቿ ለአይን ማራኪ፣ ጆሮ ገብና ተወዳጅ የሆኑ ለባዳ የሚያስቀኑ፣ ለወዳጅ ሁሌም ሃሴትን የሚያጭሩ በርካታ የባህል እሴቶች አሏት። ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦቿ ለሉአላዊነታቸው መከበር በጋራ ዘብ የሚቆሙ፣ ጠላትን በአንድነት መክተው ድባቅ የሚመቱም ናቸው።

ሁሉም ዜጎች ኢትዮጵያዊነትን ሳይለቁና የመጡበትን ማህበረሰብ ባህልና ማንነት ሳይሸራርፉ አብረው የመኖር የሺህ ዓመታት ታሪክ ባለቤትም ናቸው። የነዚህን ህዝቦች አንድነት የተፈታተኑ አያሌ አጋጣሚዎች በተለያዩ ጊዜያት ተከስተዋል፤ ይሁንና በጠንካራው አብሮነትና የተጋድሎ ወኔያቸው ችግሮቹን በጣጥሰው በማለፍ ዛሬ ላይ ደርሰዋል። የጋራ ማንነት ያላቸው ህዝቦች ንፋስ ያመጣውን ወጀብ ሁሉ ለዘመናት በገነቡት የአብሮነት ባህላዊ እሴት መክተው ውድማማችነታቸውንና አንድ መሆናቸውን አጽንተዋል።

ይህ ወንድማማችነት ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች በልዩነት ብቻ ሳይሆን በአንድነት ውስጥ ያሉ መሆናቸውን በሚገባ ያመለክታል። ይህ ወንድማማችነትና አንድነት ይበልጥ እንዲጠናከርም ነው በመንግስት በኩል እየተሰራበት ያለው። የብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች ቀን በአል መከበርም ከዚሁ አኳያም የሚታይ ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐብይ አሕመድ ሰሞኑን ለ17ተኛ ጊዜ የተከበረውን የብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ቀን በዓል አስመልክተው ባስተላለፉት መልእክት "የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች በዓል የኢትዮጵያዊነት በዓል ነው፤ ኢትዮጵያዊነት የብሔር ብሔረሰቦች የጋራና የአንድነት መገለጫ ነውና» ሲሉ አስገንዝበዋል። ኢትዮጵያዊነት ማለት የብሔሮች ብሔረሰቦች ዕሴቶች፣ ባህሎች፣ ታሪኮች፣ ቅርሶች፣ ቋንቋዎችና ጥበቦች በአንድነት የሚገለጡበት የጋራ ማንነት መሆኑን ጠቅሰው፣ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት በዓለም መድረክ አሸናፊ ሆነው እንዲወጡ ከፈለግን ሁላችንም አሸናፊ የምንሆንበትን መንገድ መፍጠር አለብን" ብለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ኢትዮጵያውያን ከልዩነት ባሻገር የጋራ ማንነት ያላቸው ህዝቦች እንደሆኑ አበክሮ በሚገልፀው መልእክታቸው ላይ ደጋግመው እንዳስገነዘቡት፣ በምንም መልኩ ኢትዮጵያውያን አንዳቸው ያለ ሌላኛቸው ሊኖሩም፣ ሊያድጉም ሆነ ሊያሸንፉ አይችሉም።

«ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ሁሉም ሕዝቦች ሕዝቦቻችን ናቸው። ሁሉም ቋንቋዎች ቋንቋዎቻችን ናቸው። ሁሉም ባህሎች ባህሎቻችን ናቸው። ሁሉም በዓሎች በዓሎቻችን ናቸው። ሁሉም እምነቶች እምነቶቻችን ናቸው። ሁሉም ቅርሶች ቅርሶቻችን ናቸው። ሁሉም አካባቢዎች የሁላችን አካባቢዎች ናቸው። ሁሉም የተፈጥሮ ሀብቶች የሁላችንም ሀብቶች ናቸው። ለዚህም ነው በየትኛውም የሀገሪቱ ክፍል የጸጥታ ኃይሎቻችን ደማቸውን የሚያፈስሱት፤ አጥንታቸውንም የሚከሰክሱት» በማለት የኢትዮጵያውያንን ጠንካራ የጋራ እሴት በማጉላት አስረድተዋል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ያለ ዘላቂ ሰላም ዘላቂ ሰላምም ያለ ህብረ ብሄራዊ አንድነት ሊሳካ እንደማይችል አስገንዝበዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሌሎች ሀገሮች ዛሬ በሚያወጧቸው ህግች ሁሉን የሚያቅፍ ስርአት መገንባት ከቻሉ እኛ ከእነሱ በተሻለ በእሴት ጭምር የመገንባት ሀገራችንን ማጽነት እንችላለን፤ የባለ ጠንካራ መሰረት ህዝቦች መሆናችንን የመዘንጋት ጊዜያችንን ይብቃ፤ ልዩነታችንን ለሚና ካወልነው አንድነታችን በእሴታችን ላይ ባማረ መልኩ ይገነባል። አንድነት እና ልዩነት አይጣሉብን፤ ልዩነት ያልተዳፈነ ቀዳዳችንን የምንደፍንበት የስራ ስማችን ነው፤ አንድነት ደግሞ የእውቀት ጉዟችን ይሆናል፤ እናም በህብረት አንድ ላይ በመቆም ብቻ ሳይሆን በመደመር ሀይላችንን ከቁጥራችን እናብዛ» ሲሉም በጋራ የመቆምን ፋይዳ አስገንዝበዋል።

የብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች ቀን ለ17ኛ ጊዜ በሲዳማ ክልል በሃዋሳ ከተማ "ህብረ ብሄራዊ አንድነታችን ለዘላቂ ሰላማችን" በሚል መሪ ቃል በተከበረበት ወቅት የተገኙ ተሳታፊዎችም የጠቅላይ ሚኒስትሩን መልእክት የሚያጠናክር ሃሳብ ተናግረዋል። ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች ልክ በአንድ ቤት በሚኖሩ የቤተሰብ አባላት





እንደሚመሰሉ ነው የተናገሩት። የማንነት ልዩነቶች የውበት እንጂ የግጭት መንስኤ ሊሆኑ እንደማይገባም አስገንዝበዋል።

በስፍራው የተገኘው የዝግጅት ክፍላችን ዘጋቢ ካነጋገራቸው ተሳታፊዎች መካከል አንዱ የሆኑት የኦሮሞ ብሄር ተወካይዋ ወይዘሮ ከድጃ አዲይ ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ኦሮሞ፣ አማራ፣ ጉራጌ፣ ወላይታ፣ሲዳማን የመሳሰሉ ልዩ ልዩ ማንነቶች እንዳሉ ጠቅሰው፣ እነዚህ ማንነቶች የውበት የአንድነት መገለጫ መሆናቸውን ጠቅሰዋል፤ ልዩነቶች የግጭት ሰበብ ሊሆኑ አይገባም ሲሉም መልእክታቸውን አስተላልፈዋል። ሁሉንም ኢትዮጵያውያን የሚያስተሳስሩ አያሌ የጋራ ማንነቶች እንዳሉም ጠቅሰው፣ እነርሱን ለማጉላትና የአንድነቶቻችን መሰረት እንዲሆኑ መስራት ያስፈልጋል ይላሉ።

በአፋር ክልል አርጐባ ብሄረሰብ ወክለው የተገኙት አቶ ሙክታር ኡመር፣ እኛ ኢትዮጵያውያን በአንድ ቤት ውስጥ ባለ ቤተሰብ የምንመሰል፣የተለያዩ አስተሳሰቦች አሉን ሲሉ ይገልጻሉ። እነዚህ አስተሳቦች ውበት ናቸው። አንዱ ያለአንዱ ውበትና ጥንካሬ የለውም። ስለዚህ በብዝሃነታችን ውስጥ አንድነታችን አስጠብቀን ልንጓዝ ይገባል ነው ያሉት።

የወላይታ ብሄር ተወካይዋ ወይዘሮ ጸዳለ ዱሌም ይህን ሀሳብ ይጋራሉ። በኢትዮጵያ የተለያዩ የማንነት ጥያቄዎች እንዳሉ ጠቅሰው፣ እነዚህ የማንነት ጥያቄዎች በህገመንግስቱ በዲሞክራሲያዊ መንገድ እንጂ በግጭት ሊፈቱ እንደማይችሉ ይናገራሉ። "የሚያምርብን ኢትዮጵያዊ አንድነታችን ነው። የብሄር ብሄረሰቦች ቀን በአልን ሁሉም በመነፋፈቅ የሚጠብቁት ልዩ ቀን ነው" በማለትም አንድ እናት በሆነችን ኢትዮጵያ ውስጥ ተቻችለንና ተከባብረን ልንኖር ይገባል ብለዋል። ይህንን ለማድረግ የሚያስችሉ የጋራ ባህላዊና ማህበራዊ መሰረቶችም እንዳሉም ነው የሚገልፁት።

የብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦችን የጋራ ባህላዊ እሴቶች አሁን ካለውም በላይ በእጅጉ በላቀ ማጠናከርና ማጎልበት እንደሚያስፈልግ የዘርፉ ምሁራንም ያስገነዝባሉ። ለመሆኑ "ኢትዮጵያውያን የጋራ ባህላዊ እሴቶች አሏቸው። እነርሱን ማልማት፣ ማጠናከር፣ ለወንድማማችነትና አንድነት መሰረት እንዲሆኑ ማድረግ ላይ መስራት ያስፈልጋል" ሲባል ምን ማለት ይሆን?

ደስታ ሎሬንሶ በአንትሮፖሎጂ የትምህርት መስክ ሶስተኛ ዲግሪያቸውን እየሰሩ ያሉና በባህል ልማትና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ በርካታ የጥናት ውጤቶችን ይፋ ያደረጉ ምሁር ናቸው። እርሳቸው ኢትዮጵያውያን በአገር ላይ ጠላት ሲመጣ በጀግንነት የሚመክቱበት እሴት በሌላው ዓለም ላይ የሌለና ብቸኛው የማንነታቸው መሰረት መሆኑን ይገልፃሉ። ከዚህ ባለፈ ፍቅር፣ ብሄርን ሳይሆን ሰውነትን ያስቀደመ መተሳሰብና ትብብር የኢትዮጵያውያን መገለጫና የጋራ ባህላዊ እሴታቸው መሆኑንም ይናገራሉ። በነዚያ የድል ወቅቶች መላው ብሄረሰቦች ልዩነታቸውን ወደጎን ትተው ከሁሉም የአገሪቷ ክፍሎች በርካታ ኪሎ ሜትሮችን በማቋረጥ ሉአላዊነታቸውን ያስከበሩበት ዋንኛ ምክንያትም የጋራ እሴቶች ስላሏቸው እንደሆነ ነው አስረግጠው የሚናገሩት።

ይህንንም በወጣቱ ዘንድ ማስረጽ እንደሚገባ አስገንዝበው፣ በስርአተ ትምህርቱ ውስጥ በማካተት ማሳደግና እሴቶቹን ማጎልበት እንደሚያስፈልግ ነው የሚያስረዱት። መረዳዳት፣ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት እና ሌሎችም መሰል ማንነቶች የኢትዮጵያዊነት መገለጫና የጋራ እሴት መሆናቸውን ይጠቅሳሉ።

"ሁሉም ሰው ስለ ጋራ እሴት ሊያወራ ይችላል። ይሁን እንጂ ይህ ማንነት ተቋማዊ በሆነ መንገድ ተጠንቶና ታትሞ ለትውልድም ሆነ ለትምህርት ተቋማት እየተላለፈ አይደለም" የሚሉት ምሁሩ ፤ በተለይ በመንግስት ስር ያሉ በባህልና በብሄር ብሄረሰቦች ጉዳይ ላይ የሚሰሩ እንደ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴርና የፌዴሬሽን ምክር ቤትን የመሳሰሉ ተቋማት በተደራጀ መንገድ በስትራቴጂ ተደግፈው የጋራ እሴቶችን ለማጎልበት እየሰሩ እንዳልሆነ ነው የሚያምኑት።

ከዚህ በመነሳትም "የኢትዮጵያውያን የጋራ ባህላዊ እሴት ግንባታና ጥናትና ምርምር ተቋም ማቋቋም ያስፈልጋል" የሚል ጠንካራ አቋም ያራምዳሉ። ይህንን ሃላፊነት መንግስት ሊወጣና በፖሊሲ፣ ህግና በተግባር መሬት ላይ የሚተረጎምበት መንገድ መፈለግ እንዳለበትም ይናገራሉ። በተለይ በአሁኑ ወቅት በአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር የሚቀነቀኑ "መደመርን"ና "ወንድማማችነት" የመሰሉትን የጋራ እሴቶችን የሚያጎለብቱ ሃሳቦች ከቃላት ባለፈ መሬት ላይ ወርደው በጥናት፣ ፖሊሲ ተቀይረው ማህበረሰቡ ውስጥ ዘልቀው እንዲገቡ በማድረግ የባህል አብዮት ሊያመጡ በሚችሉበት መንገድ ላይ ሊሰራ ይገባል የሚል ጠንከር ያለ መልእክት ያስተላልፋሉ።

**እንደ መውጫ**

የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦች እና ህዝቦች የየራሳቸው ማንነት ፣ ባህል፣ ቋንቋና ታሪክ አላቸው። ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች ኢትዮጵያዊነት ናቸው። እነዚህን ማንነቶች በግል ወይም በተናጠል ማሳደግ ወይም በትይዩ (parallel) የጋራ ዕሴቶቻችን ማስተሳሰር፣ መገንባት እና ኢትዮጵያዊ ማንነትን ማጠናከር ያስፈልጋል። ኢትዮጵያዊ ማንነት ወይም ሀገራዊ አንድነት እና ሉዓላዊነት የወቅቱ ትልቁ የሀገሪቱ አጀንዳ ነው። በዚህ ሀገራዊ ማንነት ላይ መሰረት ጥለን የኢኮኖሚ ዕድገት እና ብልጽግናን እንዲሁም ዘላቂ ሰላምን በተባበሩ የኢትዮጵያ ህዝቦች ማረጋገጥ ይቻላል።

የጋራ ባህላዊ ትስስር የኢኮኖሚ ማህበራዊ ትስስር፣የፖለቲካ መረጋጋት፣ ሰላም እና ደህንነት ለማረጋገጥ ዋስትና ይሰጣል። ከዚህም በተጨማሪ የኢኮኖሚ መስተጋብር እና የንግድ ልውውጥ (shared values) ይፈጥራል። ጠንካራ ሀገር በጋራ እሴት ውስጥ እንደሚገነባም መገንዘብ ያስፈልጋል።

በዘርፉ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ሳይንሳዊ ምርምር ያደረጉ ምሁራን ህዝቦች ወንድማማችነትን የሚያጎለብቱት የጋራ እሴቶቻቸውን ለይተው ትኩረት ሰጥተው ሲሰሩ መሆኑን ነው የሚያምኑት። ማህበራዊ ትስስር እና የጋራ እሴቶች ሲላሉ ለእርስ በእርስ ግጭት (civil war) መነሻ እንደሚሆኑ እነዚህ ምሁራን ያስረዳሉ። ይህ እሴት የማይዳብር ከሆነ ህዝቦች ሀገርን አናውቅም፣ ትስስር የለንም ማለታቸው እንደማይቀርም ነው የሚያስረዱት። በዚህ ምክንያትም ጥላቻ ይሰፍናል፣ ለጠላቶቻቸውም መግቢያ ቀዳዳዎች ይፈጠራሉ፤ ኢኮኖሚ ይወድማል፣ የሀገር ጸጥታ ይናጋል፤ ገጽታ በእጅጉ ይበላሻል። ህዝቦች በስጋት ይኖራሉ፣ የህዝቦች ጥርጣሬ እና አለመተማመን ለልማትም አብሮ ለመኖርም ጸር ነው። ኢትዮጵያ አንድ ሀገር ደግሞም የብዙ ህዝቦች የጀግንነት እና ሉዓላዊነት ውጤት ነች። የጋራ ባህላዊ ዕሴት መገንባት ለሀገሪቷ ቀደምት ታሪክ፣ የጀግንነት፣ የሉዓላዊነት፣ የመተባበር፣የመረዳዳት ዕሴቶች ዕውቅና መስጠት ነው።

ሰሞኑን የተከበረው የብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች በዓልም አንድነትንና ወንድማማችነትን በሚያጠናክሩ እሴቶች ተሞልቶ ተከብሮ ማለፉን መረጃዎች ያመለክታሉ። ሁሉም ዜጎች እንደየ ባህላቸውና የእሴት መሰረታቸው ማንነታቸውን በሚገልፁ ተወዳጅ አለባበሶች፣ ባህላዊ ስርአቶች፣ አመጋገቦችና ሌሎች የሸምግልናና መሰል ሃብቶች ደምቀው ማሳለፋቸውም፣ ቀኑን የተመለከቱ መድረኮች መካሄዳቸውም እሴቶቹን ለማጠናከር ፋይዳቸው ከፍተኛ ነው።

እሴቶቹን ለማጎልበትና በህዝቡ ዘንድ እንዲሰርጹ ለማድረግ ከዚህም በላይ መሰራት ይኖርበታል። ከባህልና ከመሳሰሉት ጋር የሚሰሩ ተቋማት በእዚህ በኩል ከፍተኛ ኃላፊነት አለባቸው። የብሄሮች ብህረሰቦችና ህዝቦች ባህሎችና ሌሎች እሴቶች የመላ ኢትዮጵያውያን እሴቶች መሆናቸው ላይ አበክረው መስራት አለባቸው።

የአንትሮፖሎጂ ምሁሩ አቶ ደስታ ሌሬንሶ እንዳሉትም፤ ወንድማማችነትንና አንድነትን የሚያጠናክሩትን እነዚህን የጋራ እሴቶች/ ሀብቶች/ ዜጎች ይበልጥ እንዲገነዘቧቸውና የራሳቸው አድርገው እንዲመለከቷቸው አልፎም ተርፎ ለልማትና ለዴሞክራሲ ስርአት ግንባታው እንዲያውሏቸው ለማድረግ እሴቶቹን በተቋማዊ አሰራርና አደረጃጀት ማጎልበትና ማስረጽ ላይ በስፋት መስራት ያስፈልጋል። ይህን ማድረግ ሲቻል የሚነፍሰውን የጥፋት ነፋስ እና ወጀብ በራሳችን እሴቶች ከመቆጣጠርና የአንድነት መሰረትን ከማጠናከር ባሻገር ለትውልድ የሚሻገር ተግባር ማከናወን ይቻላል።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ሳምንቱን በታሪክ

## የወልወል ግጭት

ዋለልኝ አየለ

በዛሬው ሳምንቱን በታሪክ ዓምዳችን ሦስት ነገሮችን እናያለን፡፡ የወልወል ግጭት፣ የአምባላጌ ጦርነት እና የዓለም የኖቤል ሽልማት፡፡

ፋሺስት ኢጣሊያ፤ ኢትዮጵያን ለመውረር እንደሰበብ የተጠቀመችበት ታሪካዊው የወልወል ግጭት (Wal-Wal Incident) የተከሰተው ከ88 ዓመታት በፊት፣ በዚህ ሳምንት ኅዳር 26 ቀን 1927 ዓ.ም ነበር፡፡

ኢጣሊያ በ1888 ዓ.ም ዓድዋ ላይ የደረሰባትን ሽንፈት ለመበቀልና ኢትዮጵያን የኢጣሊያ ምስራቅ አፍሪካ ቅኝ ግዛት አካል ለማድረግ ለ40 ዓመታት ያህል ስትዘጋጅና ጊዜ ስትጠብቅ ቆየች፡፡ በአውሮፓውያኑ የዘመን አቆጣጠር በ1922 ወደ ሥልጣን የመጣው ቤኒቶ ሙሶሊኒ፣ ኢጣሊያ ዓድዋ ላይ የተከናነበችውን የውርደት ማቅ እንደሚበቀልና ኢትዮጵያ የኢጣሊያ ቅኝ ግዛት አካል እንደምትሆን መዛት የጀመረው ገና በጠዋቱ ነበር፡፡

ለዚህም እንዲያመቸው የኢጣሊያ መንግሥት ራስ ተፈሪ መኮንን ኢጣሊያን በጎበኙበት ወቅት «ቪቫ ኢትዮጵያ» እያለ ወዳጅ መስሎ ሸነገላቸው፡፡ እስከ አፍንጫው የታጠቀ በርካታ ጦር በኤርትራና በሌሎች የኢጣሊያ ምስራቅ አፍሪካ ቅኝ ግዛት አካባቢዎች ላይ ያከማች ጀመር፡፡ የጦሩን ውጤታማነት አስተማማኝ ለማድረግም ሀኪሞችን፣ ሰላዮችንና ሌሎች ሙያተኞችን አብሮ አጓጓዘ፡፡ «ኢትዮጵያውያን» የግዛት ባላባቶችን በጥቅም በመደለል ማስኮብለሉንና መረጃ መመንተፉንም ተያያዘው፤ በጨካኝነታቸው የታወቁትን እነ ኢሚሊዮ ዴ ቦኖ፣ ፒትሮ ባዶሊዮ፣ ሩዶልፎ ግራዚያኒና ሌሎች የጦር አለቆችን ወደ ምስራቅ አፍሪካ ላከ፡፡

ኢጣሊያ ይህንን ዝግጅት ካጠናቀቀች በኋላም ኢትዮጵያን የምትወርበት አጋጣሚ መጠባበቅ ጀመረች፡፡ ኅዳር 26 ቀን 1927 ዓ.ም የኢጣሊያ ወታደሮች በኢትዮጵያ እና በእንግሊዝ ሱማሌላንድ (British Somaliland) መካከል ያለውን ወሰን ለመከለል የተላኩትን ሰዎች ይጠብቁ በነበሩት የኢትዮጵያ ወታደሮች ላይ ጥቃት ከፈቱባቸው፡፡ (ኢጣሊያ በአካባቢው ያለው የኢጣሊያ ሱማሌላንድ ግዛቷ ስለሆነ ወታደሮቿ በአካባቢው ነበሩ) ውጊያ ተደረገና በሁለቱም ወገኖች በኩል ሰውነት ቆሰለ፣ አካል ጎደለ፣ የሰው ሕይወት ጠፋ፡፡

ኢትዮጵያም ስሞታዋን ለኢጣሊያ መንግሥት ስታቀርብ፤ የኢጣሊያ መንግሥት ይባስ ብሎ የተበደለ መሆኑን በመግለፅ የሚከተሉትን «የመደራደሪያ ጥያቄዎች» አቀረበ፡፡

አንደኛ፤ የወቅቱ የሐረርጌ ገዢ የነበሩት ደጃዝማች ገብረማርያም ወልወል ድረስ ሄደው እዚያ የሚገኘውን የኢጣሊያ የጦር መሪ በኢትዮጵያ መንግሥት ስም ይቅርታ እንዲጠይቁ፣ አንድ የኢትዮጵያ የጦር ጓድ ለኢጣሊያ ሰንደቅ ዓላማ ሰላምታ እንዲሰጥ፣ በኢትዮጵያ በኩል ለተደረገው የማጥቃት እርምጃ ኃላፊ የሆኑት ባለስልጣኖች ሁሉ ተይዘው የኢጣሊያን ሰንደቅ ዓላማ እጅ ነስተው እንዲሻሩና ተገቢውን ቅጣት በአስቸኳይ እንዲያገኙ፣

ሁለተኛ፤ የኢትዮጵያ መንግሥት ለቆሰሉት፣ አካላቸው ለጎደለውና ለሞቱት የኢጣሊያ ወታደሮች ካሣ የሚሆን 200 ሺህ ማርቴሬዛ (ጠገራ ብር) እንዲከፍል እንዲሁም በኢጣሊያ ወታደሮች ላይ ጥቃት ፈፅመው ከባድ ጥፋት ያደረሱት ደጃዝማች ዑመር ሰመተር ተይዘው ለኢጣሊያ መንግሥት እንዲሰጡ ... በማለት የለየለት የትዕቢት ጥያቄ አቀረበ፡፡

የኢትዮጵያ መንግሥትም የኢጣሊያን ሃሳብ ሳይቀበል ቀረ፤ ጉዳዩ በእርቅ እንዲያልቅ ለማድረግ ቢጥርም ሳይሳካ ቀረ፡፡ ፋሺስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን መውረሯ እንደማይቀር ሲታወቅ፣ ከዓድዋ ድል በኋላ ራሷን በኢኮኖሚ ሳታበለፅግ ለ40 ዓመታት ያህል ባለችበት የቆየችው ኢትዮጵያ መሳሪያ ለመግዛት እንቅስቃሴ ብታደርግም ቄሳራውያኑ ኃይሎች በመመሳጠር እንዳይሳካላት አደረጉ፡፡

ከዚህ በኋላ ፋሺስት ኢጣሊያ ለ40 ዓመታት ያህል ስትዘጋጅበት የቆየችውን እቅድ እውን ለማድረግ በሁሉም አቅጣጫዎች ኢትዮጵያን ወረረች፡፡ በዓለም አቀፍ ሕግጋት ፈፅሞ የተከለከሉ የጦር መሳሪያዎችን (የጦር አውሮፕላን፣ የመርዝ ጋዝ፣ ...) ጭምር በመጠቀም በኢትዮጵያውያን ላይ እጅግ በጣም ከባድ የሆነ የጦር ወንጀል ፈፀመች፡፡

> ከዓድዋ ጦርነት ሦስት ወራት ቀደም ብሎ የተከናወነው የአምባላጌ ጦርነት የተካሄደው ከ127 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ኅዳር 28 ቀን 1888 ዓ.ም ነበር

የፋሺስት ኢጣሊያ ጦር በኢትዮጵያውያን አርበኞች ትግልና በወዳጅ ሀገራት እገዛ ከኢትዮጵያ ተሸንፎ እስኪወጣ ድረስም ዘመን ተሻጋሪ ውጤት(ተፅዕኖ) ያላቸውን በርካታ ወንጀሎችን በኢትዮጵያውያን ላይ ፈፅሟል፡፡

የወልወል ግጭት ኢጣሊያ ለብዙ ዘመናት ሉዓላዊነቷን ጠብቃ የቆየችውን ኢትዮጵያን ለመውረር የነደፈችውን እቅዷን ለማሳካት እንደሽፋን የተጠቀመችበት ታሪካዊ ክስተት ነው፡፡

### የአምባላጌ ጦርነት

ከዓድዋ ጦርነት ሦስት ወራት ቀደም ብሎ የተከናወነው የአምባላጌ ጦርነት የተካሄደው ከ127 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ኅዳር 28 ቀን 1888 ዓ.ም ነበር፡፡

የአምባላጌውን ውጊያ የጀመሩት ፊታውራሪ ገበየሁ (አባ ጎራ) እና ራስ አሉላ እንግዳ (አሉላ አባ ነጋ) ናቸው፡፡ የኢትዮጵያ ጦር የበላይ አዛዥ ልዑል ራስ መኮንን ነበሩ፡፡

ጦርነቱም በኢትዮጵያ አሸናፊነት የተጠናቀቀ ሲሆን የወራሪው የኢጣሊያ ጦር በኢትዮጵያ መሸነፉ በመላው አውሮፓ በተለይም በተሸናፊዋ ኢጣሊያ ምድር ከፍተኛ ፍርሃት፣ ብስጭትና ቁጣ ፈጥሮ ነበር፡፡

በጦርነቱ ዕለት ንጉሰ ነገሥቱ ዳግማዊ አጤ ምኒልክ ለዓድዋ ጦርነት ዘመቻ ከአዲስ አበባ ተነስተው እየተጓዙና በመንገዳቸውም ላይ ሕዝቡን እያነጋገሩ ገና ወሎ ውስጥ ነበሩ፡፡ የድሉን ዜና ለዳግማዊ ምኒልክ የላኩላቸው ራስ መንገሻ ነበሩ፡፡

### የኖቤል ሽልማት 121ኛ ዓመት

ኖቤል ሲባል አስቀድሞ የሚታሰበን ገናና የሆነው ሽልማቱ ነው። ሽልማቱ በየዓመቱ የሚሰጥ ሲሆን፣ ከተጀመረም እነሆ 121 ዓመታትን አስቆጠረ።

የኖቤል ሽልማት መስጠት የተጀመረው በዚህ ሳምንት በአውሮፓውያኑ አቆጣጠር ደሴምበር 10 1901 ወይም በኢትዮጵያ አቆጣጠር ታኅሳስ 1 ቀን 1894 ዓ.ም ነው፡፡

ሽልማቱ የተጀመረው የአልፍሬድ ኖቤል አምስተኛው ሙት አመት በተዘከረበት ነው። የመጀመሪያዎቹ ሽልማቶችም የተሰጡት በስዊድን ስቶክሆልም ሲሆን፣ ሽልማቶቹ የተሰጡባቸው መስኮችም ፊዚክስ፣ ኬሚስትሪ፣ ህክምና፣ ስነ ጽሁፍ እና ሰላም ናቸው።

ቆይቶም ምጣኔ ሀብት ተጨምሮበታል። ኖቤል በ1895 ባረቀቀው መመሪያ መሠረት ሽልማቱ እየተሰጠ ይገኛል። በስማድናዊው አልፍሬድ ኖቤል ስም የተዘጋጀው ይህ ሽልማት ለሰው ልጅ ትልቅ ዋጋ ያላቸውን ተግባሮች ላከናወኑ እንዲሰጥ በሚል ኖቤል በተናዘዘው መሰረት የሚሰጥ ነው። ተሸላሚው የወርቅ ሜዳሊያ፣ ዲፕሎማ እና የገንዘብ ሽልማት ይሰጠዋል። ሎሬት በመባልም እንዲጠራ ይደረጋል። ኖቤል በምርምር ያገኛቸው የፈጠራ ስራዎች የሰው ልጅን የሚጎዱ በሚል በማህበረሰቡ ዘንድ ይሰነዘርበት የነበረው ነቀፌታ አሳስቦት ሽልማቱን ማዘጋጀቱን መረጃዎች ያመለክታሉ። ሽልማቱ እጅግ በጣም የተከበረ በሚል የሚታሰብና በዓለም ላይ ትልቅ ስኬታማ ሥራ በመሥራት ውጤታማ ለሆኑ ሰዎች ብቻ ይሰጣል። ኖቤል ከኢንቨስተመንቶቹ ከሚያገኘው ሀብት አብዛኛውም ለዚህ ሽልማት እንዲውልም ተናዟል። በቅድሚያ ለተለያዩ የግንባታ ስራዎች (ለሲቪል ስራ) የሚጠቅመውን ድማሚት የፈጠረው አልፍሬድ ኖቤል፣ ምርምሩ እየሰፋ ሄዶ ለጦር መሳሪያ የሚውሉ የተለያዩ አይነት ፈንጂዎችንና በርካታ የጦር መሳሪያ ተቀጣጣዮችን ፈጥሯል። 355 የፈጠራ ስራዎች የባለቤትነት ባለመብትም ነው። ኖቤል በዚህ ሽልማት ይበልጥ ቢታወቅም፣ ኬሚስት፣ ኢንጂነር፣ የፈጠራ ስራዎች ባለቤትና የንግድ እና ኢንቨስትመንት ሰው እንዲሁም በበጎ አድራጎት ስራውም ይታወቃል።

በእሱ ፈቃድ አራት የተለያዩ ተቋማት ተመስርተውም ነው ሽልማቱ እየተካሄደ ያለው። በዚህ መሠረት ሦስት ስዊድናውያንና አንድ ኖርዌያዊ ሽልማቱን ይሰጣሉ። ከስዊድን ዋና ከተማ ስቶክሆልም የስዊድን ዘውዳዊ ሳይንስ አካዳሚ ለፊዚክስ ፣ለኬሚስትሪ እና ምጣኔ ሀብት ሽልማት ለመስጠት ሲወስኑ፤ የካርሎኒስካ ኢንስቲትዩት በፊዚዮሎጂ ወይም በሕክምና ዘርፍ እና የስዊድን አካዳሚ በስነ ጽሑፍ ዘርፍ ሽልማት ለመስጠት ይወስናሉ።

በኦስሎ መቀመጫውን ያደረገው የኖርዌይ ኖቤል ኮሚቴ ደግሞ በሰላም ዘርፍ ለሚሰጠው ሽልማት ይወስናል። የኖቤል ፋውንዴሽን ሕጋዊ ባለመብትና የፈንዶቹ ተግባራዊ አስተዳዳሪ በመሆን በመሥራትና የሽልማት ሰጪው ተቋሞች የጋራ አስተዳደራዊ ሚናው በመወጣት ያገለግላል። በሽልማቱ ዙሪያ መመካከርና መወሰን ግን አይችልም። ሽልማቱ የሚገባቸውን ሰዎች የሚወስኑት አራቱ ተቋማት ናቸው።

አልፍሬድ በርንሀርድ ኖቤል የተወለደው እ.ኤ.አ በ1833 በስዊድን ዋና ከተማ ስቶክሆልም ነው። ኖቤል ከተወለደ ከአራት ዓመት በኋላ ቤተሰቦቹ ወደ ሩሲያ ሄዱ። አባቱ በሴንት ፒተስበርግ ከተማ የሚገኝ ፈንጂዎችን እና ሌሎች የጦር መሣሪዎችን የሚያመርት ስኬታማ ፋብሪካን ያስተዳድር ነበር። ይህም ሁኔታ ለኖቤል መልካም አጋጣሚ ሳይፈጥርለት እንዳልቀረ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

ኖቤል ፈጠራዎቹን በየጊዜው እያሻሻለ ያወጣም ነበር። የተሻሻለ ፈንጂን በምርምር ማግኘት ችሏል። ይህም በዘመናዊ መልኩ ከፍተኛ ፍንዳታዎችን ማድረግ የሚያስችል ሆነለት።

ፈጠራው በአንድ ጊዜ በርካታ ሰዎችን የሚጨርስና አካባቢዎችን የሚያወድም ጅምላ ጨራሽ መሣሪያ ነበር። ይህ የኖቤል ናይትሮግሎሲሪን ፋብሪካ እአአ በ1964 ፍንዳታ ይደርስበትና ታላቅ ወንድሙንና ሌሎች በርካታ ሰዎችን ይገድላል።

አልፍሬድ አሁንም ሌላ የተሻሻለ ፈንጂ ለማምረት ምርምሩን ቀጠለ። በአውሮፓውያኑ አቆጣጠር 1867 ለአያያዝና ለአጠቃቀም የማያስቸግር ከፍተኛ ፍንዳታ ማድረስ የሚችል «ኪሴልጉር» የተሰኘ ቅይጥ የፍንዳታ ፈጠራን እውን አደረገ። ይህ ለፈጠራ የተፈጠረ ሰው በቃኝ አላለም። በ1875 ትልቅ አቅም ያለው ጌላቲን የተሰኘ ድማሚት ፣ በ1887 ባሊሲታይትን አገኘ። በዚህ ወቅት ሌላ ወንድሙ ፈረንሳይ ውስጥ ይሞታል።

ጋዜጠኞች የሞተው አልፍሬድ ኖቤል ይመስላቸዋል። ጋዜጠኞቹ የኖቤልን ፈጠራ በጥሩ አይመለከቱትም ነበርና ይህን በሚመጥን መልኩም አንድ ጋዜጣ « የሞት ነጋዴው ኖቤል ከዚህ አለም በሞት ተለየ» በሚል ርዕስ ዘገባውን አቀረበ። ኖቤል ግን ይችን አለም የተሰናበተው በአውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ1896 ነው።

ዜናውን ያነበበው ሁሉ «የማታ የማታ እውነት ይረታ» እንደሚባለው ዘግይቶ ኖቤል አለመሞቱን ቢረዳውም ዜናውን ያነበበውን ኖቤል ግን ምቾትና ሰላም ነሳው። እውነትም ብሞት እንዲህ ተብሎ ነው የሚፃፍልኝ ብሎ ራሱን ጠየቀ። የኔ ብቸኛ ዝናዬ ሞትን ማከፋፈል ማለት ነው ሲል ተፀፀተ።

ያገኘውን ዝናና ዕውቅና በወንድሙ ሞት ወደ መልካም አጋጣሚ ለመቀየር ቆረጠ። በስሙ ፋውንዴሽን በመመሥረት በሥራው ከሚያገኘው ገቢ አብዛኛውን ለዚህ ሽልማት ድርጅት በመስጠት ተሸላሚዎች እንዲውል የወሰነውም ከዚህ በኋላ ነው።

ጥቁር አሜሪካዊው የሰብአዊ መብት ዋና ተሟጋችና ሰማዕት ማርቲን ሉተር ኪንግ እንዲሁም የደቡብ አፍሪካው ጳጳስ ዴዝሞንድ ቱቱ የኖቤል ሰላም ሽልማት ከተቀበሉት መካከል ይገኙበታል። የእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር ሜናኸም ቤጊን እና የግብጽ ፕሬዚዳንት አንዋር ሳዳት የኖቤል የሰላም ሽልማት ተካፋዮች ሽልማቱን ተቀብለዋል።

የፍልስጤም መሪ ያሲር አራፋት እና የእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር ይስሐቅ ራቢን እንዲሁም የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ሺሞን ፔሬዝ በጋራ የተሰጣቸውን የኖቤል የሰላም ሽልማት ከተቀበሉት መካከል ይገኙበታል።

የናይጄሪያው ወሌ ሶይንካ፣ የግብፁ ናጂብ ማህፉዝ እና የደቡብ አፍሪካው ናዲን ጎርዲመር በስነ ጽሑፍ ሽልማትን ተቀብለዋል። የኢትዮጵያው ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ከሦስት ዓመት በፊት የሰላም የኖቤል ተሸላሚ ሆነዋል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለዚህ ሽልማት የበቁት ወደ ስልጣን ከመጡበት ጊዜ ጀምሮ በአገራቸው ውስጥ ለውጥ ለማምጣት በወሰዱት እርምጃ በተለይ ከኤርትራ ጋር ሠላም ለማውረድ ባደረጉት ጥረት ነው። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ የኖቤል ሰላም ሽልማት 100ኛው አሸናፊ ናቸው።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በወቅቱ በትዊተር ገጻቸው « በኖርዌይ ኮሚቴ ውሳኔ ተደስቻለሁ፤ ለሰላም ለሚሰሩ እና ለሚተጉ በሙሉ የከበረ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፤ ይህ ሽልማት የኢትዮጵያና የአፍሪካ ነው» ሲሉ አስፍረዋል፡፡

# የዝነኞች ገጽ

## ስመ ገናናው ኢትዮጵያዊ የጥበብ ፈርጥ

**ቦጋለ አበበ**

ኢትዮጵያ የጥበብ ባህር ብቻ ሳትሆን የአያሌ ዘመን ተሻጋሪ የጥበብ ፈርጦችም መገኛ ናት። በተለያዩ ዘመናት በበርካታ የጥበብ ዘርፎች አለምን ያስደነቁ ታላላቅ የጥበብ ቀንዲሎች ከኢትዮጵያ ማህጸን ወጥተዋል። ከነዚህ ጥበበኞች ደግሞ አንዳንዶቹ በአለም እጅግ የተከበሩና የተፈሩ ከመሆናቸው ባሻገር ስማቸውን ቀለል አድርጎ እንኳን ለመጥራት አይቻልም። ለዚህ አንዱና ዋነኛው ቀለምን በብሩሻቸው ጠቅሰው ሸራ ላይ ብዙ ተአምራትን ለአለም አኑረው ያለፉትና በስእል ጥበባቸው ገናና ስም ያተረፉት እጅግ የተከበሩ የአለም ሎሬት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ በጉልህ ይጠቀሳሉ። እኛም በዛሬው የዝነኞች ገጽ አምዳችን ስለእኚህ በአለም ገናና ስም ያተረፉ የጥበብ ሰው በተለያዩ ጊዜዎች የተጻፉ መዛግብትንና ድረ ገፆችን አገላብጠን የሚከተለውን ጽሁፍ በማዘጋጀት ለንባብ አቅርበናል።

እጅግ የተከበሩ የዓለም ሎሬት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ በሰሜን ሸዋ በምትገኘው አንኮበር ጥቅምት 13 ቀን 1925 ዓ.ም ነው የተወለዱት። አባታቸው አቶ ተክሌ ማሞ እናታቸው ደግሞ ወይዘሮ ፈለቀች የማታወርቅ ይባላሉ።

ገና በጨቅላ ዕድሜያቸው ፋሺስት ጣልያን ኢትዮጵያን በግፍ ሲወራት ተመልክተው በቁጭት ነው ያደጉት። የልጅነት ትዝታቸውም ይሄው የግፍ ወረራ እና ጦርነት የሚያስከትለው የሰው፣ የንብረት እና የባህል ጥፋት ነበር። የጠላት የግፍ ወረራ እና እልቂት ያስከተለውን የሰው፣ የንብረት እና የባህል ጥፋት ገና በህጻንነት ዕድሜያቸው የተመለከቱት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ከነጻነት በኋላ ሃገራቸውን እንደገና እንዴት መገንባት እንደሚቻል ሲያወጡ እና ሲያወርዱ ከቆዩ በኋላ ዋናው እና ቀዳሚው ጉዳይ እውቀት መሸመት መሆኑን የተረዱት ገና በልጅነት እድሜያቸው እንደነበረ በብዙ መዛግብት ተጽፎ ይገኛል። ለዚህም ለሀገር ግንባታ አስፈላጊውን እውቀት መሸመት የፈለጉት በማዕድን ምሕንድስና ዘርፍ ነበር። ወላጆቻቸውና ዘመድ አዝማዶች ግን የኪነ ጥበብ ተሰጧቸውን በቤታቸውና በከተማው ዙሪያ በሚስሏቸው ስዕሎች ተገንዝበውት ነበር።

የመጀመሪያና መካከለኛ ትምህርታቸውን የት እና መቼ እንዳጠናቀቁ የተጻፈ መረጃ ባይገኝም፤ ገና በአሥራ አምስት ዓመታቸው በ1940 ዓ/ም ለከፍተኛ ትምህርት ተመርጠው የምሕንድስና ትምህርት ለመከታተል ወደ እንግሊዝ አገር መላካቸው ተዘግቧል ፡፡

ለትምህርት የተመረጡት ተማሪዎች ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ሲሰናበቱ የተሰጣቸውን ምክር ሁሌም እንደሚያስታውሱት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ ሲናገሩ ‹‹ንጉሠ ነገሥቱ ተግታችሁ አጥኑና ተማሩ፣ ጠንክራችሁ ለመስራትና ሀገራችሁ ኢትዮጵያን የምትገነቡበትን ዕውቀት ይዛችሁ ተመለሱ። ‹‹ ከናንተ የሚፈለገው አዕምሯችሁን ዝግጁ አድርጋችሁ ኢትዮጵያን ለመገንባት የሚያስችል እውቀትንና ጥበብን ሸምታችሁ እንድትመለሱ ነው እንጂ አውሮፓ ውስጥ ስላሉት ረዣዥም ፎቅ ቤቶች ወይም ስለመንገዶቻቸው ስፋት በአድናቆት እንድትነግሩን አይደለም›› ብለዋቸው እንደነበር ሁሌም ያስታውሱ ነበር፡፡

እጅግ የተከበሩ የዓለም ሎሬት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ በእንግሊዝ አገር በትምህርት ላይ ሳሉ የአዳሪ ትምህርት ቤትን ኑሮ በማስታወስ የባእድ ሃገር እንግዳ በዓላት እና የአየር ሁኔታው መለዋወጥ እንዳስቸገራቸው በተለያዩ ጊዜዎች ተናግረዋል።

በትምህርት አቀባበላቸውም በሒሣብ፣በኬሚስትሪ እና በታሪክ ትምህርቶች ጥሩ ውጤት በማምጣት ከመምህሮቻቸው ተደጋጋሚ አድናቆት ቢያገኙም የተፈጥሮ መክሊታቸው ኪነ ጥበብ እንደሆነ መምህሮቻቸው ለመገንዘብ ብዙ ጊዜም አልወሰደባቸውም።

በመምህራቸው አበረታችነት በዚህ ስጦታቸው ላይ የበለጠ ለማተኮር ወስነው በለንደን ማእከላዊ የኪነ ጥበብ ትምሕርት ቤት የገቡት አፈወርቅ ከዚህ ትምህርት ቤት ትምህርታቸውን በጥሩ ውጤት በማጠናቀቅ ለከፍተኛ ጥናት በስመ ጥሩው የለንደን ዩኒቨርሲቲ የስሌድ ኪነ ጥበብ ማዕከል የመጀመሪያው አፍሪካዊ ተማሪ ሆነዋል ፡፡

በዚህ ትምህርት ቤት ቆይታቸውም በቀለም ቅብ፣ በቅርጻ ቅርጽ እና በኪነ ህንጻ ጥናቶች ላይ በመስራት ተመርቀዋል። ትምህርታቸውን አጠናቀው ወደ ኢትዮጵያ እንደተመለሱ በተለያዩ ግዛቶች በመዘዋወር በአንዳንድ ቦታም እስከ ሦስት ወራት በመቀመጥ የኢትዮጵያን ታሪክ እና የብሔር ብሔረሰቦቿን ባህልና ወግ ሲያጠኑ ቆይተዋል።

በ1946 ዓ.ም ገና የ22 ዓመት ወጣት እያሉ የተለያዩ የስነ ጥበብ ሥራቸውን የሚያሳይ የመጀመሪያውን ኤግዚቢሽን በአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት አቅርበዋል። ከትርዒቱ ባገኙት ገቢ በድጋሚ ወደ አውሮፓ በመሄድ ለሁለት ዓመት በጣሊያን፣ በፈረንሳይ፣ በስፔን፣ በፖርቱጋል፣ በእንግሊዝና ግሪክ ጥልቅ የኪነ ጥበብ ጥናት አከናውነዋል።

በጦርነትና በሌሎች ምክንያቶች ተዘርፈው በነዚህ ሃገራት የሚገኙትን የኢትዮጵያ ጥንታዊ የሃይማኖትና የታሪክ የብራና መጻሕፍትን በጥልቅ አጥንተውና የመስታወት ላይ ስዕል ( የሞዛይክ አሠራር ጥበብን ) ቀስመው ወደ አገራቸው ተመልሰዋል።

እጅግ የተከበሩ የዓለም ሎሬት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ ወደ ሃገራቸው እንደተመለሱ ንጉሠ ነገሥቱ አዲስ አበባ በሚገኘው የመናገሻ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ግድግዳ፣ ጣሪያና መስኮቶችን በሃይማኖታዊ ምስሎች በቀለምና በመስታወት ስዕሎች እንዲያስውቡት ባዘዟቸው መሰረት የዳግም ምጽአት ፍርድ፣ የድንግል ማርያም ንግስና ፣ ኪዳነ ምሕረት፣ እና የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን የዘውድ ስርዓት የሚያሳዩ ሥራዎችን ሰርተዋል። በሐረር ከተማ የሚገኘውን የልዑል ራስ መኮንን ሀውልት የቀረጹትም እሳቸው ናቸው። ከዚህም በኋላ የአርቲስቱ የስዕል እና ሌላ የኪን ሥራዎቻቸው ወዲያው በ'ቴምብሮች'፣ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር የኪነ ጥበብ ትርዒት ላይ እጅግ በጣም እየታወቁና እየገነኑ መጡ።

እጅግ የተከበሩ የዓለም ሎሬት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ እንደ ኢትዮጵያዊ ምሁርና የጥበብ ሰው በጥንታዊት ኢትዮጵያ ታሪክ፣ ነጻነት፣ ባሕልና ሥልጣኔ እንዲሁም በግዕዝ ቋንቋ፣ በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖታዊ አስተምህሮቶች፣ ትውፊትን ጠንቅቀው የሚያውቁ የታሪክ ሰውና ቅርስ ጠባቂ ሰው እንደነበሩ በቅርብ የሚያውቋቸው ሁሉ ይመሰክሩላቸዋል።

ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ በሀገራቸውና በአውሮፓ ለረጅም ዓመታት የሥነ ጥበብ ሙያን የተማሩ ከመሆናቸው ባሻገር በሀገራቸውና በዓለም አቀፍ ደረጃም በተለያዩት ጊዜያት በርካታ የስዕል አውደ ርዕዮችን በማቅረብ ትልቅ አድናቆትንና ክብርን ለመጎናጸፍ ችለዋል። በዚህ ልዩ ተሰጥኦአቸውና ችሎታቸው የተነሳም በተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች ከሚገኙ ታላላቅ የጥብብ ሰዎች ጋር ለመገናኘትና ስራዎቻቸውንም ለሌሎች ለማሳወቅ ችለዋል። በስነ ጥበብ ስራዎቻቸውም ለዓለማችን ሰላምን፣ ለሰው ልጆች አንድነትና እኩልነትን በመስበካቸውም በዓለማችን ከሚገኙ ታላላቅ መሪዎችና ፖለቲከኞች፣ ታዋቂ ሰዎችና የሃይማኖት አባቶች ጋር ለመገናኘት የቻሉ ዓለማቀፋዊ ዝናን እና ክብርን ያተረፉ የሥነ ጥበብ ሰው ሆነዋል።

በዚህም ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የስነ ጥበብ ከፍተኛ ሽልማት ጀምሮ በሀገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ደረጃ ከ90 በላይ የሚሆኑ ሜዳሊያዎች፣ ሽልማቶችንና ዲኮራሲያኖችን እንዲሁም የክብር ዜግነት ያገኙ ሰው ሲሆኑ፤ ለአብነትም በሐምሌ ወር 1997 ዓ.ም በአየርላንድ ዋና ከተማ በዱብሊን በተደረገው በ30ኛው የኪነ ጥበብ የባሕልና የሳይንሶች ዓለማአቀፋዊ በዓል ላይ (The International Biographical Center of Cambridge) በስነ ሙያ ጥበብ የመጨረሻ ሽልማት የሆነውን (Davinci Diamond) የደቬንቺ አልማዝ የተባለውን ሽልማት ሰጥቷቸዋል። ይህንን ሽልማት በማግኘትም ብቸኛው አፍሪካዊ የሥነ ጥበብ ሰው ለመሆን በቅተዋል። በዚሁ በዓል ላይም "The United Cultural Convention of the United States of America" ለእኚሁ ታላቅ ሰው አለም አቀፍ የሰላም ሽልማት (International Peace Prize) ልዩ ሽልማትና፣ የክብር የሰላም አምባሳደርነትን ሰጥቷቸዋል። ይህም ሽልማትና የክብር ዲፕሎማ በዘር፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ፣ በባሕል በተከፋፈለች ዓለማችን ለዓለም ሰላምንና ፍትህን፣ ለሰው ልጆች እኩልነትንና አንድነትን ለማስፈን ለሚጥሩ ሰዎች የሚሰጥ ዓለምአቀፋዊ ሽልማት እንደሆነ የድርጅቱ ኃላፊዎች በሽልማቱ ወቅት ገልጸው ነበር። ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌም በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ካገኟቸው በርካታ ሽልማቶች መካከል እነዚህ ለሁለቱ ዓለም አቀፍ ሽልማቶች ልዩ ክብርና አድናቆት እንደላቸው ገልጸው ነበር። እጅግ የተከበሩ የዓለም ሎሬት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ የነገሥታት መናገሻና መዲና በነበረችው አንኮበር ተወልደው እንዴት ለእዚህ ዓይነት ዓለምአቀፋዊ እውቅና እና ዝና ሊደርሱ እንደቻሉ በተጠየቁበት በአንድ ወቅት ‹‹አገራችን በብዙ ነገሮች ቀደምት በመሆኗ እንደምትታውቅና እንደምትደነቅ ሁሉ እኔም በዚህ የሙያ መስክ የአገሬን ስም እንዳስጠራ የኢትዮጵያ አምላክ ፈቃድ የሆነ ይመስለኛል።›› በማለት ከፍተኛ ትህትና እና የሀገር ፍቅር ስሜት የተሞላበት መልስ ሰጥተዋል።

የእኚህ ታላቅ የጥበብ ሰው አጭር የሕይወት ታሪክ ከልጅነት ጀምሮ ጓደኛቸው በሆኑት በፕሮፌሰር ሪቻርድ ፓንክረስት በአማርኛና በእንግሊዘኛ ‹‹አፈወርቅ ተክሌ አጭር ሕይወት ታሪክና ምርጥ ስዕሎቹ›› በሚል ርዕስ ባቀረቡት መጽሐፍ መግቢያ ላይ አስተያየታቸውን ያሰፈሩት በደርግ ዘመነ መንግሥት የባሕልና የስፖርት ጉዳይ ሚ/ር የነበሩት ሻለቃ ግርማ ‹‹የሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ ምርጥ የሥዕል ሥራዎች በሺህ ዓመታት አንዴ ብቅ እንደሚሉ የፈጠራ ሰዎች ውድና ብርቅ የሥነ ጥበብ ውጤቶች ናቸው። አብዛኛዎቹ ሥዕሎቻቸው ጠንካራ የሀገር ፍቅር ስሜትና የተፈጥሮ ውበትን ሕያው በሆኑት ታዋቂ ሥራዎቻቸው አንጸባርቀዋል፤ በጥንታዊነቷና በታሪካዊነቷ በርካታ የምርምርና የጥናት ሰዎችን ለምትስበው እናት ኢትዮጵያ የሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ ምርጥ የሥነ ጥበበብ ሥራዎች ተጨማሪ ጌጥና ኩራት ናቸው።›› ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተው ነበር።

አፍሪካውያን ከቅኝ ግዛት ቀንበር ስር ለመውጣት በሚያደርጉት የሞት ሽረት ትግል የጥቁር ሕዝቦች ነጻነትና አይበገሬነት ልዩ መገለጫ በሆነችው ኢትዮጵያ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ሲቋቋም የአፍሪካውያንን ታላቅ ስልጣኔ፣ አኩሪ ባሕል፣ ታሪክና ነጻነት በበሩሻቸው ቀለም በድርጅቱ መሰብሰቢያ አዳራሽ እውን ያደረጉት እኚሁ ታላቅ የጥበብ ሰው ነበሩ። በድርቅ፣ በጦርነትና በረሃብ የተጎሳቆለችውን እናት ሀገራቸውን ኢትዮጵያን በብሩሻቸው የገለጹበት ‹‹ዋይ ዋይ የት ትሄዳለህ›› የሚለው የጥበብ ስራቸውም በሀገራችን በወቅቱ በደረሰው አስከፊ ድርቅና ረሃብ የደረሰባቸውን የልብ ስብራትና ጥልቅ ሐዘን የገለጹበት ስራቸው ነው።

ከታዋቂ ሥራዎቻቸው መካከል በከፊል

- በአዲስ አበባ በቀድሞው የአፍሪቃ አንድነት ድርጅት አዳራሽ መግቢያ የሚታየው በመቶ ሃምሳ ካሬ ሜትር ላይ የተሳለው ትልቅ የመስታወት ስዕል
- አዲስ አበባ በመናገሻ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን የውስጥ ስዕሎች፣ ሞዛይኮች
- አዲስ አበባ በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል የሚገኘውን የመጀመሪያውን የ'ዳግም ምጽዓት ፍርድ ስዕል
- በሐረር የልዑል ራስ መኮንን ሐውልት
- በአዲግራት የ'ዳግም ምጽዓት ፍርድ ስዕል
- በለንደን 'ታወር ኦፍ ለንደን' የቅዱስ ጊዮርጊስ ጸሎት ቤት ከብር እና ከእንጨት የተሠራ የመንበር መስቀል
- በሩሲያ፣ አሜሪካ እና በሴኔጋል ኤግዚቢሽን ላይ የቀረበው 'የመስቀል አበባ' ስዕል
- "እናት ኢትዮጵያ'
- የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ምስል እና
- 'ደመራ' ተጠቃሾች ናቸው ፡፡

እጅግ የተከበሩ የዓለም ሎሬት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ ማክሰኞ ሚያዝያ 2 ቀን 2004 ዓ/ም በተወለዱ በ79 ዓመታቸው ከዚህ አለም በሞት ተለይተው ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት ፣ወዳጅ ዘመዶቻቸውና አድናቂዎቻቸው በተገኙበት አዲስ አበባ በሚገኘው መንበረ ጸባኦት ቅድስት ስላሴ ካቴድራል ቀብራቸው ተፈጽሟል ፡፡



**የዓለም ሎሬት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ**

# ዓለም አቀፍ



## የሱዳን ፖለቲከኞች ከስምምነት ቢደርሱም ህዝባዊ ተቃውሞው ቀጥሏል

የሱዳን የፖለቲካ ፓርቲዎች እና ኃይሎች በሀገሪቱ አዲስ የፖለቲካ ሽግግር ለመጀመር ያስችላል የተባላውን የስምምነት ማዕቀፍ ቢፈራረሙም በሀገሪቱ የሚደረገው ተቃውሞ እንደቀጠለ ነው።ተቃዋሚዎቹ፤ “መፈንቅለ መንግስቱን እንዳፈረስን ሁሉ ስምምነቱን እናፈርሳለን” እያሉ ነው

በሺዎች የሚቆጠሩ ሱዳናውያን ወታደራዊ እና ሲቪል ፓርቲዎች ሰኞ እለት የሲቪል መንግስት ምስረታ ስምምነት ላይ የደረሱበት ፕሬዚዳንታዊ ቤተ መንግስት አቅራቢያን ጨምሮ በበርካታ የካርቱም አካባቢዎች የተቃውሞ ድምጾች ሲያሰሙ መታየታቸው የሮይተርስ ዘገባ ያመለክታል።

የሱዳን የጸጥታ ኃይሎች በዋና ከተማው የተበተኑ ህዝባዊ ተቃውሞዎችን ለመቆጣጠር ባደረጉት ጥረት አስለቃሽ ጭስ ተጠቅመው መንገዶችን እና ድልድዮችን መዝጋታቸውም ተገልጿል።በሱዳን ፖለቲከኞች መካካል ተደረሰው ስምምነት በዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ዘንድ ትልቅ ተቀባይነት ቢቸረውም፤ ሱዳናውያን በጉዳዩ ላይ ልዩነቶች እንዲያንጸባርቁ ምክንያት ሆኗል እየተባለ ነው።

አንዳንድ ሱዳናውያን ስምምነቱ መረጋጋት ሊያመጣ ይችላል ሲሉ ሌሎች ደግሞ የወታደራዊውን ኃይል ተሳትፎ ውድቅ ያደርጋሉ።በካርቱም በተደረገው ሰልፍ ተሳታፊ የሆነው የ22 ዓመቱ የዩኒቨርስቲ ተማሪ ሳፋ ሳሌህ “መፈንቅለ መንግስቱን እንዳፈረስን ሁሉ ስምምነቱን እናፈርሳለን” ሲል ለተደረሰው ስምምነት ያለውን ተቃውሞ ገልጿል።ፍትህ ለሰማዕታት እንሻለን ወታደርንም አንቀበልም ሲልም አክሏል የዩኒቨርስቲ ተማሪ ሳፋ ሳሌህ።

ባለፈው ሰኞ እለት በሱዳን የዴሞክራሲ አቀንቃኞች ጥምር ኃይል እና ወታደራዊ ኃይሉ መካካል የተፈረመው ስምምነት ሀገሪቱን ወደ ሲቪል አስተዳደር ለመመለስ የሚያስችል እንደሆነ ይታመናል።በስምምነቱ መሰረት ምርጫ እስከሚካሄድ ድረስ፣ ለሁለት ዓመታት የሚዘልቅ የሲቪል የሽግግር አስተዳደር እንደሚኖር ተገልጿል።የቀድሞው ፕሬዝዳንት ኦማር አልባሽር በህዝባዊ ተቃውሞ ከስልጣን ከተወገዱ በኋላ፣ ሱዳን ላለፉት አራት ዓመታት የፖለቲካ ቀውስ ውስጥ ተዘፍቃ እንደቆየች ይታወቃል።የአህጉሪቱ ተቋም የአፍሪካ ህብረት፣ የአረብ ሀገራት እንዲሁም ምዕራባውያን በሱዳን ወታደራዊ ኃይል እና በሲቪል አመራሩ መካከል ስምምነት ተደርሶ በሀገሪቱ ሰላም እና መረጋጋት እንዲሰፍን የተለያዩ ጥረቶች ሲያደርጉ መቆየታቸውን አል ዐይን ዘግቧል።

## በጆርጅ ፍሎይድ ግድያ የተባበረው የቀድሞ ፖሊስ ተጨማሪ እስራት ተፈረደበት



የቀድሞ የሚኒያ ፖሊስ ከተማ የፖሊስ ባልደረባ ጆርጅ ፍሎይድ ጀርባ ላይ በመቆም ለግድያው በመተባበሩ የሦስት ዓመት ተኩል እስር ተፈረደበት። ጄ አሌክሳንደር ኩንግ ጥፋተኛነቱን አምኗል። በጆርጅ ፍሎይድ ግድያ ከተያዙ አራት ፖሊሶች አንዱ ነው። ፍሎይድ እአአ በ2020 በፖሊሶች ተይዞ፣ አንደኛው ፖሊስ በጉልበቱ የፍሎይድን አንገት አፍኖ ነበር ሕይወቱ ያለፈው።

ሞቱ ዘረኝነት እና የፖሊስ ጭካኔን የሚቃወም ከፍተኛ ሕዝባዊ ቁጣን በአሜሪካ እና በመላው ዓለም ቀስቅሷል። የቀድሞው ፖሊስ ከዚህ በፊት የፍሎይድን ሰብአዊ መብት በመጣስ የተፈረደበት ሲሆን፣ የአሁኑ በቀደመው ላይ ተጨማሪ የእስር ጊዜ ተፈርዶበታል።በ2021 የቀድሞው የፖሊስ ባልደረባ ዴሬክ ሾቪን ፍሎይድ አንገት ላይ ለዘጠኝ ደቂቃ ተንበርክኮ በመግደል የ22 ዓመት ተኩል እስራት ተፈርዶበታል። ከዚህ ጎን ለጎን በሰብአዊ መብት ጥሰት የ20 ዓመት እስር ተፈርዶበታል።

ግድያው ጋር በተያያዘ ጄ አሌክሳንደር ኩንግ፣ ቶማስ ሌን እና ቶው ታዎ የተባሉ ሌሎች ፖሊሶችም በሰብአዊ መብት ጥሰት የፍርድ ውሳኔ ተላልፎባቸዋል።ፖሊሶቹ ፍሎይድን በቁጥጥር ስር ለማዋል ሲሞክሩ ለገጠመው የጤና እክል ተገቢውን ትኩረት ባለመስጠታቸው ነው ብይኑ የተላለፈው።

ኩንግ እና ሌን በጋራ ሆነው ሾቪን የተባለው የቀድሞ ፖሊስ በፍሎይድ አንገት ላይ ተንበርክኮ ሲያፍነው ተባብረዋል። ታዎ ደግሞ በአካባቢው የነበሩ እግረኞችን ሲያባርር ነበር። ሾቪንን ጨምሮ በግድያው የታሰሩት ፖሊሶች ከቀረቡባቸው ክሶች አንዱ፤ ኩንግ የተባለው የቀድሞ ፖሊስ ፍሎይድን ለማዳን ጣልቃ ባለመግባቱ የተፈረደበት የ36 ወራት እስራት ይገኝበታል።

በተጨማሪም ታዎ በተመሳሳይ ክስ የ42 ወራት እስራት የተፈረደበት ሲሆን፤ ቶማስ ሌን በግድያ የሁለት ዓመት ተኩል እና የሦስት ዓመት እስራት ተፈርዶበታል።የፍርድ ውሳኔው ሲተላለፍ ዐቃቤ ሕግ ማቲው ፍራንክ ኩንግ በግድያው ቀጥተኛ ተሳትፎ ነበረው። የጆርጅ ፍሎይድ ቤተሰብ ጠበቃ “ውሳኔው ለፍሎይድ ቤተሰብ ፍትሕን ያሰፈነ ነው” ።“ቤተሰቡ ያለ ፍሎይድ ሌላ ዓመት በዓል ሊያሳልፍ ነው። እንዲህ ያሉ ውሳኔዎች በመጠኑም ቢሆን መጽናናት ይሰጧቸዋል ብዬ አምናለሁ” ማለታቸውን የዘገበው ቢቢሲ ነው።

የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን
Ethiopian Intellectual Property Authority

ከኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን ጋር
በመተባበር በየአስራ አምስት ቀኑ የሚታተም

## የቴክኖሎጂና የኢኖቬሽን ድጋፍ ማዕከል ፕሮጀክት ያለው ሀገራዊ ፋይዳ

የበለፀጉት አገራት አሁን የደረሱበት የዕድገት ደረጃ ላይ የመድረሳቸው ዋነኛ ምክንያት ለሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ዘርፍ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠታቸውና ዘርፉን የዕድገት አንቀሳቃሽ መሳሪያ በማድረጋቸው ነው። በሀገራችንም የቴክኖሎጂ ፈጠራዎችን በመቅዳት፣ በማላመድ፣ ጥቅም ላይ በማዋል እንዲሁም ቀስ በቀስ ሀገር በቀል የፈጠራ ሥራዎችን በማጎልበት ብሔራዊ የቴክኖሎጂ አቅምን አስተማማኝ ደረጃ ላይ ለማድረስ ዕቅድ በመያዝ ለተግባራዊነቱም ያላሰለሰ ጥረት በማድረግ ላይ ትገኛለች። በዚህ ረገድ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲዎች፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት እና የተለያዩ ኢንዱስትሪዎች የማይተካ ድርሻ እንዳላቸው ይታመናል።

በአሁኑ ወቅት በዓለማችን ላይ የሚገኙት የፈጠራ ሥራዎች የሰውን ልጅ የዕለት ተዕለት ኑሮ ቀላል በማድረግና በማሻሻል ረገድ የሚኖራቸው ሚና ከፍተኛ በመሆኑ ሀገር በቀል የፈጠራ ሥራዎች እንዲበራከቱ የፈጠራ ባለሙያዎችን ማበረታታት ያስፈልጋል የሚሉት በኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን የቴክኖሎጂና የኢኖቬሽን ድጋፍ ማዕከል አስተባባሪ የሆኑት አቶ ጳውሎስ ዳዊት ናቸው።

ከዚህ አኳያ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ለዩኒቨርሲቲዎች፣ ለምርምርና ስርፀት ተቋማት በፓተንት ሰነዶች የታቀፉ የቴክኖሎጂ መረጃዎችን በማሰራጨት ተደራሽ ከማድረግ ባሻገር የቴክኖሎጂና የኢኖቬሽን ድጋፍ ማዕከል በየተቋማቱ በማቋቋም በትብብር በመሥራት ላይ እንደሚገኝ አቶ ጳውሎስ ይናገራሉ።

እርሳቸውም ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በቴክኖሎጂና የኢኖቬሽን ድጋፍ ማዕከል በኩል የቴክኖሎጂ ሽግግርን ለማፋጠንና የህብረተሰቡን የቴክኖሎጂ ፍላጎት ለማሟላት እያከናወኑ ያለውን ተግባራት በሚመለከት እንዳብራሩት፤




አቶ ጳውሉስ ዳዊት፤

ባለስልጣኑ መንግሥት በመረጣቸው ዘጠኝ የትኩረት መስኮች የሚገኙ የፓተንት መረጃዎችን ከአለም አእምሯዊ ንብረት ድርጅት ጋር በመተባበር ለዩኒቨርሲቲዎች፣ ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት አዳዲስ የቴክኖሎጂ መረጃዎችን እንዲጠቀሙ በማድረግ ላይ ይገኛል።

እንዲሁም ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ የቴክኖሎጂ መረጃ ተደራሽነት እንዲሰፍን ፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲሳለጥ እና የምርምር እና ስርጸት ድግግሞሽ እንዲቀነስ በማድረግ ሀገራዊ የኢኮኖሚ ዕድገት ሂደትን በላቀ ደረጃ ለመደገፍ ከአለም አእምሯዊ ንብረት ድርጅት (WIPO) ጋር በመተባበር የቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ድጋፍ ማዕከል (TISC) ፕሮጅክት ኢ.ኤ.አ ከ2013 ጀምሮ ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛል። የአለም አእምሯዊ ንብረት ድርጅቱ የበለጸጉ ሀገራት በክፍያ የሚያገኙትን በፓተንት የታቀፉ ቴክኖሎጂ መረጃ እና ሳይንሳዊ የህትመት ውጤቶችን በማደግ ላይ ላሉ አገራት በልዩ ሁኔታ በዝቅተኛ ክፍያ ወይም በነፃ ተጠቃሚ ያደርጋል።

በዚህ ረገድ ሀገራችን የዚህ ልዩ እድል ተጠቃሚ ብትሆንም መረጃውን ማግኘት የሚያስችለውን የይለፍ ቃል በመውሰድ በሚፈለገው መጠን ችግር ፈቺ የፈጠራ ሥራዎችን በማበልጸግ እና የቴክኖሎጂ ሽግግር በማድረግ ረገድ የተሠራው ሥራ ዝቅተኛ ነው ማለት ይቻላል። የቴክኖሎጂና የኢኖቬሽን ድጋፍ ማዕከል ፕሮጀክት በአሥር ዓመት ቆይታ ወቅት ከ36 ዩኒቨርሲቲዎች፣ 18 የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማትና አምስት የተለያዩ የምርምርና ስርጸት ተቋማት ጋር ማዕከሉን ለማቋቋም የመግባቢያ ሰነድ መፈራረም የተቻለ ቢሆንም፤ ስምምነቱን ከፈረሙ ተቋማት መካከል 14 ተቋማት ብቻ የይለፍ ቃል በመውሰድ የፓተንት ቴክኖሎጂ መረጃ እና ሳይንሳዊ የህትመት ውጤቶችን እንዲጠቀሙ ማድረግ ተችሏል።

ሆኖም ማዕከሉን ለማቋቋም የመግባቢያ ሰነድ ከተፈራረሙ ተቋማት አኳያ የይለፍ ቃል በመውሰድ የፓተንት ቴክኖሎጂ መረጃ እና ሳይንሳዊ የህትመት ውጤቶችን የሚጠቀሙ ተቋማት ቁጥር እጅግ አነስተኛ ነው። ስለዚህ በቀጣይ ሁሉም ማዕከሉን ለማቋቋም የመግባቢያ ሰነድ የተፈራረሙ እና አዲስ የሚፈርሙ ተቋማት የይለፍ ቃል በመውሰድ የፓተንት ቴክኖሎጂ መረጃ እና ሳይንሳዊ የህትመት ውጤቶችን እንዲጠቀሙ ድጋፍ በማድረግ እና ስልጠና በመስጠት ችግር ፈቺ የፈጠራ ሥራዎችን እንዲያበለጽጉ እና በሀገሪቱ የቴክኖሎጂ ሽግግርን እንዲያሳልጡ ባለስልጣን መስሪያቤቱ በቁርጠኝነት እንደሚሠራ አቶ ጳውሎስ ተናግረዋል።

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል። በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

# አወዛጋቢው ምናባዊ ገንዘብ(ክሪፕቶ ከረንሲ)

ስለ ምናባዊ ገንዘብ አሁናዊ ሁኔታ እና ምን ያህል ለማጭበርበር አደጋ የተጋለጠ እንደሆነ በተከታታይ ለንባብ በበቁት መጣጥፎቼ ለማሳየት ሞክሬያለሁ። በዛሬው መጣጥፍ ደግሞ ስለ ክሪፕቶ ከረንሲ ንግስቷ መጨረሻና የባለሙያ ምክር ተካቷል። ግንዛቤ ሊጨበጥበት የሚገባው የመጀመሪያው መርህ ፤ ገንዘብ ዋጋ የሚኖረው ሌላው ሰውም ዋጋ ሲሰጠው ነው። በታሪክ ባንክ ያተመው ገንዘብ ይሁን ሳንቲም አልያም የከበሩ ማዕድናት ወይም ዛጎል ለመገበያየት ይውሉ የነበሩት ብቸኛ ምክንያት በሁሉም ተጠቃሚዎች ዘንድ አመኔታ ስለተጣለባቸው ነው።

በርካቶች ለአመታት በመንግስታት ዘንድ ተቀባይነት እንዳገኙት መደበኛ መገበያያዎች ሁሉ ተቀባይነት ያለው ዲጂታል ከረንሲ ለመፍጠር ያደረጉት ጥረት ከንቱ ሆኖ የኖረው አመኔታን ሊያገኙ ስላልቻሉ ነው ይለናል ባርትሌት፤ ቢትኮይን ይሄን ሁሉ አልፎ በሕዝብና ተቋማት ዘንድ ተቀባይነትን እያገኘ የመጣው አመኔታን ያተረፈለትን አሰራር ተግባራዊ በማድረጉ ነው። ቢትኮይን ስራ ላይ ያዋለው ልዩ"የሒሳብ መዝገብ"ወይም የመረጃ ቋት "ብሎክቼይን" ይባላል። አንድ የቢትኮይን ባለቤት ራሱን የቻለ ግን ደግሞ ተመሳሳይ ቅጂዎች በተለያዩ ቦታዎች እንዲኖሩት ያደርጋል።

ቢትኮይን ለሆነ ሰው ባስተላለፍኩ ቁጥር የዚህ ልውውጥ ቅጂ ወደ ሁሉም መዝገቦች ይተላለፋል። ባንክ ይሁን መንግስት ሌላ ማንም አካል ፤ ራሱ የቢትኮይን ፈጣሪ እንኳ ይሄን ዝውውር ሊቀይረውና ለግል ጥቅሙ ሊያውለው አይችልም። ከዚህ ጀርባ ረቂቅ የሒሳብ ቀመር አለ። ለዚህ ነው ቢትኮይን የማይጭበረበረው፤ በመንታፊዎች የማይበረበረው ወይም ተመሳሳይ ቢትኮይን ሁለት ጊዜ መጠቀም የማይቻለው።

ተንቀሳቃሽ ስልክ ያለው ሁሉ ባንኮችን ወይም የሀገሩን ገንዘብ ወደጎን በማድረግ ወይም በማለፍ የባንክ አገልግሎትን ተክቶ ግብይቱን ወይም የገንዘብ ዝውውሩን ከመፈጸሙ ባሻገር ኢንቨስት ያደረገ ደግሞ ጠቀም ያለ ትርፍ ያገኛል። እንግዲህ ዶ/ር ሩጃ ስለክሪፕቶከረንሲ ያላትን ዕውቀት ነው ለማጭበርበርና በአቋራጭ ለመክበር የተጠቀመችበት። የክሪፕቶ ንግስቷ በዌምብሌ አሪና ተገኝታ ዋንኮይንን ካስተዋወቀች ከ4 ወር በኋላ በጥቅምት 2016 ዓ.ም መቀመጫውን በቡልጋሪያ ያደረገው ዋንኮይን ቴክኒካል ኦፊሰር ለመቅጠር በወኪሉ አማካኝነት ማስታወቂያ ያወጣል።

ከቤትና ከመኪና በተጨማሪ በአመት 250ሺህ ፓውንድ የሚያስከፍለው አጓጊ የስራ ማስታወቂያ ማርኳቸው ከአመለከቱት የብሎክቼይኑ ባለሙያ ቢዦርን ዠርኬ ይመረጥና በቀጣሪ ኤጀንሲው ለቃለ_መጠይቅ ይጠራል። ቃለ_መጠይቅ የሚያደርግለትን ሰው ኩባንያው ምን እንድሰራለትና እንዳሳካለት ነው የሚፈልገው ሲል ይጠይቀዋል። ብሎክቼይን ስለሌለው ትሰራለታለህ ሲል ይመልስለታል። ዠርኬ ክው ብሎ ደነገጠ ፤ ጆሮውን ማመን ስላቃተው ፤ ኩባንያው ክሪፕቶከረንሲ አይደለም እንዴ ሲል መልሶ ይጠይቀዋል።

ያለምንም ማቅማማት አዎ ክሪፕቶከረንሲ ነው ይለዋል። ከተመሠረተ የቆየ ቢሆንም ብሎክቼየን ግን የለውም። በሁኔታው ግራ የተጋባው ዠርኬ ለመሆኑ ክሪፕቶከረንሲው ማን ነው ሲል የቀጣሪ የኤጀንሲውን ሰው ይጠይቀዋል። "ዋንኮይን"ሲል ይመልስለታል። ዠርኬ የዚህን ጊዜ ችግር እንዳለ ስለጠረጠረ ቅጥሩን ተወው። ያለ ብሎክቼይን ክሪፕቶከረንሲ አይታሰብም። መስራቹ በቀላሉ የኢንቨስተሮችን ገንዘብ ለግሉ ጥቅሙ ያውለዋል። በዋንኮይን የሆነው ይሄው ነው። ዠርኬ ስራውን ካለመቀበል ባሻገር ሁኔታውን ለሚዲያ ወይም ለሚመለከተው አካል ቢጠቁም ኖሮ ብዙዎችን ያድን ነበር። ሆኖም ባልታወቀ ምክንያት ይሄን አላደረገም።

የእሷ አልበቃ ብሎ ቤተሰቦቿንና ጓደኞቿን አግባብታ ዋንኮይን ላይ ኢንቨስት እንዲያደርጉ ወትውታና ገፋፍታ ያስበላቻቸው ጄን ማክአዳምስ እንዴት እንደተሸወደች ትናንት የሆነ ያህል በቁጭት ታስታውሰዋለች። በዌቢናር ያገኘችው የዋንኮይን አወያይ ፤"በዚህ ሰዓት ይሄን ዌቢናር የምትመለከቱ እድለኞች ናችሁ። በአጭር ጊዜ ከቢትኮይን የሚበልጠው ዋንኮይን ላይ ኢንቨስት በማድረግ ዳጎስ ያለ ጥቅም ታገኛላችሁ። " አለ። አወያዩ በመቀጠል ስለ ዋንኮይን መስራች ዶ/ር ሩጃ ማንነት ገለጻ ማድረግ ጀመረ።

"የመጀመሪያና 2ኛ ዲግሪዋን በኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ እንደሰራች፤ ፒኤችዲዋን በሀገረ ጀርመን ከሚገኘው ኮንስታንዝ እንደተቀበለች በኩራት ገለጸ። የተጨበጨበላት አማካሪ/ኮንሰልታንት/መሆኗንም አስታወሰ። ታዋቂው ዘ ኢኮኖሚስት መጽሔት ባዘጋጀው አንድ ጉባኤ ያደረገችውን ንግግርም አባሪ አደረገ። ማክአዳም በዶ/ር ሩጃ ስኬት ተደመመች። ሴት በመሆኗ ኮራች። ዋንኮይን ላይ ኢንቨስት ለማድረግ ወሰነች። ወዲያው በ1000 ፓውንድ ዋንኮይን ገዛች። ጠቀም ያለ ትርፍ ለማግኘት ኢንቨስትመንቷን ወደ 10,000 ፓውንድ አሳደገች። ቤተሰቦቿንና ጓደኞችን አግባብታ 250,000 ፓውንድ ኢንቨስት አደረጉ።

ማክአዳም ነጋ ጠባ የዋንኮይንን ድረ ገጽ በጉጉት ትመለከታለች። በጥቂት ቀናት ኢንቨስትመንቷ በአስር እጥፍ አድጎ 100,000 ፓውንድ ደረሰ። ማክአዳም በደስታ ጮቤ ረገጠች። የት ሄዳ እንደምትዝናና ማሰብና ማቀድ ጀመረች። የሽመታ ዕቅድም አወጣች። ትርፏን እያሰላች እንደ ህጻን ፈነደቀች። ዳሩ ግን በአመቱ መገባደጃ አካባቢ ጄን ማክአዳም በበይነ መረብ ራሱን በፈቃዱ ሰውን የሚረዳ ሳምራዊ/good Samaritan/ብሎ ከሚጠራ ሰው ጋር ተዋወቀች።

በሉቃስ ወንጌል(10÷30_37) ላይ ከእየሩሳሌም ወደ እያሪኮ እየሄደ ሳለ ወንበዴዎች ደብድበውና ገፈው ከመንገድ የጣሉትን ሰው አላፊ አግዳሚው እንዳላየ ሲያልፈው ፤ አንድ ሳምራዊ ግን አይቶ ያዝንለታል ቁስሉ ላይ ዘይትና የወይን ጠጅ አፍስሶ ያስርለትና በአህያው ጭኖ ወደ እንግዳ ማረፊያ በመውሰድ ገንዘብ ከፍሎ እስኪያገግም እንክብካቤ እንዲደረግለት አደራ ብሎ ይሄዳል።

ጄን ማክአዳምን ራሱን ጉድ ሰማሪታን ብሎ የተዋወቃት እንደ መጽሐፉ ቅዱሱ ሳምራዊ በገዛ ፈቃዴ ሰዎችን የምረዳ ነኝ ለማለት ነው። በእርግጥ ይሄ ሰው እንደ ሉቃስ ወንጌሉ ሳምራዊ ይሆናል !? አብረን እናያለን። በዋንኮይን ላይ ሰፊ ጥናት ያደረገና ዋንኮይን ላይ ኢንቨስት ያደረጉትን በማነጋገር ላይ መሆኑን ሲገልጽላት ማክአዳም እያመነታች በስካይፕ ለማውራት ፈቃደኝነቷን ትገልጻለች። ሆኖም ውይይታቸው ወደ ክርክርና መጨጫህ ተቀየረ፤ ዳሩ ግን የማክአዳምን ህይወት ወደ አዲስ አቅጣጫ መውሰዱ አልቀረም።

ሳምራዊ ነኝ ብሎ የተዋወቃት ሰው ቲሞቲ ከሪ መሆኑን ነገራት። የክሪፕቶከረንሲ አቀንቃኝና የቢትኮይን አድናቂ እንደሆነ አስረዳት። ሆኖም ዋንኮይን ክሪፕቶከረንሲ እንዳልሆነና አጭበርባሪ መሆኑን አረዳት። ይሄንም ሊያረጋግጥላት እንደሚችል አስረዳት። ማክአዳም ምንድን ነው ማረጋገጫህ ስትል አፋጠጠችው። ከሪ እሺ አረጋግጥልሻለሁ ብሎ መረጃዎችን መላክ ጀመረ። ለተከታታይ ሳምንታት ስለ ክሪፕቶከረንሲ አሰራር የሚያብራሩ ሊንኮችን ፤ መጣጥፎችንና ተንቀሳቃሽ ምስሎችን ላከላት።

ዋንኮይን ብሎክቼይን እንደሌለው ካረጋገጠው ዠርኬ ጋርም አስተዋወቃት። ማክአዳም ይሄን ሀቅ አምኖ ለመቀበልና በዋንኮይን ላይ ጥያቄ ለማንሳት ሶስት ወር ወስዶባታል። ከሪ እንዳላት ዋንኮይን ብሎክቼይን ከሌለው ችግር አለበት ማለት ነው በማለት መፍራት ጀመረች። የዋንኮይን ቡድን አባላትን ነጋ ጠባ ክሪፕቶከረንሲው ብሎክቼይን አለው ወይስ የለውም እያለች ስትጨቀጭቃቸውና መቆሚያ መቀመጫ ስታሳጣቸው በሚያዚያ 2017 ዓ.ም ዋንኮይን ብሎክቼይን እንደሌለው አረዷት። ማክአዳም ተዝለፍልፋ ወለሉ ላይ ተዘረረች። እነ ማክአዳም ይይዙት ይጨብጡት አጥተው ግራ በተጋቡበት ፤ የክሪፕቶ ንግስት ዋንኮይንን ለማስተዋወቅ አለምን እየዞረች ነው። ከማካው እስከ ዱባይ ፣ ከኳላሉፓር እስከ ሲንጋፓር ፤ ዋንኮይን እድገቱን ቀጥሏል።

ወዲህ ንግስቷ የእነ ማክአዳምን ኢንቨስትመንት እንደ ግል ሀብቷ ትረጨው ይዛለች። በቡልጋሪያ መዲና ሶፊያና በጥቁር ባሕር ሶዞፓል ቅንጡ ሕንጻዎችንና ጀልባ ገዛች። ሲደብራት በቅንጡው ጀልባዋ እንደ ቤቤ ሬክሳ ያሉ የፓፕ ከዋክብትን በመጋበዝ ድል ያለ ፓርቲ ትደግሳለች። ወዲህ ዋንኮይን በገባው ቃል መሠረት ለኢንቨስተሮች ክፍያ መፈጸም አልቻለም። በዚህ የተነሳ በመላው አለም የሚገኙ የዋንኮይን ኢንቬስተሮች ግራ ተጋብተዋል። ገንዘባችንን ማለት ጀምረዋል።

ለእነዚህና ለሌሎች ኢንቨስተሮች ጥያቄ መልስ ለመስጠት በፓርቹጋል ሊዝበን በጥቅምት 2017 ዓ.ም ቀን ተቆጥሯል። ኢንቨስተሮችና የዋንኮይን አስተዋዋቂዎች፤ በቀጠሮ አክባሪነት የማትታማውን ዶ/ር ሩጃን በመጠበቅ በርበሩን ቢያዩም የክሪፕቶ ንግስቷ የውሃ ሽታ ሆነች። አንዴ ሶፊያ ወደ ሚገኘው የዋንኮይን ዋና መስሪያ ቤት ፤ ሌላ ጊዜ እጅ ስልኳ ላይ ቢደውል ፤ መልዕክት ቢላክ መልስ የለም። የበላት ጅብ አልጮህ አለ። ከሊዝበኑ ሁነት ከሁለት ሳምንት በኋላ ማለትም በወርሀ ጥቅምት መገባደጃ ላይ ከሶፊያ ወደ ግሪክ አቴንስ ከበረረች በኋላ አየሁም ሰማሁም ያለ ጠፋ። በኋላ ላይ ሲጣራ ዋንኮይን ሀሰተኛ ክሪፕቶከረንሲ ከመሆኑ ባሻገር ያረጀው ያፈጀው የፒራሚድ ንግድ መሆኑ ተደረሰበት።

በዚህ ማጭበርበር የስንቱ ቤት እንደፈረሰ ፤ የስንቱ ህልም እንደጨነገፈ ቤት ይቁጠረው። ለዚህ ነው "አዲስ ዘመን"ዜጎችን ከዚህ መጭበርበር ለማስጠንቀቅ ተደጋጋሚና ተከታታይ ግንዛቤ ማስጨበጫ ዜናዎችንና መጣጥፎችን እያዘጋጀ ያለው። ነገርን ነገር ያነሳዋል እንዲሉ ጋዜጣው በዚያ ሰሞን ያስነበበንን ምክርና ማስጠንቀቂያ እዚህ ላይ ላስታውስ። ክሪፕቶ ከረንሲ የተሰኘውን ዲጂታል መገበያያ ያላቸው ዜጎች ምናባዊው ገንዘብ ህጋዊ ፍቃድ እስኪያገኝ ድረስ የያዙትን ክሪፕቶ ከረንሲ ወደ ህጋዊ ገንዘብና ዕቃ ቢቀይሩት ይመከራል ሲሉ በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የሶፍትዌር ኢንጂነሪንግ መምህር ረዳት ፕሮፌሰር ሁሴን ሰይድ ይመክራሉ።

ረዳት ፕሮፌሰር ሁሴን ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር በነበራቸው ቆይታ፤ ህጋዊ ዕውቅና የሌለውን ክሪፕቶ ከረንሲ ወደ ዶላርና ወደብር እንዲሁም ወደ ዕቃ መቀየር ይኖርባቸዋል። ይህም በቅጽበት ምናባዊው ገንዘብ አሰራሩን ቢቀይር አሊያም አገራት ቢያስቆሙት ከሚደርሰው ኪሳራ እራስን ለመጠበቅ ይረዳል። እንደ አዲስ ቴክኖሎጂ ወደፊት በስፋት ጥቅም ላይ መዋሉ አይቀርም በሚል ተስፋ ብዙዎች ወደዚህ ክሪፕቶ ከረንሲ ግብይት እንደሚገቡ የገለጹት ረዳት ፕሮፌሰር ሁሴን ፤ ይሁንና ገንዘባችንን ስናወጣ በብዙ መልኩ ህጋዊ አካሄዱን ማሰብ ይገባናል ሲሉ ያስጠነቅቃሉ። ክሪፕቶ ከረንሲ ኢትዮጵያ ውስጥ እስካሁን ፍቃድ ያገኘ መገበያያ አይደለም። ይህ ዲጂታል ገንዘብ ጥቅምም እንዳለው ሁሉ አሉታዊ ተጽእኖው ስላለው ህጋዊ ማዕቀፍ ተዘጋጅቶለት እስኪወጣ ድረስ እራስን ከኪሳራ መጠበቅ ያስፈልጋል።

በተለይ አገራት የእራሳቸውን ስምምነት አድርገው እስካልተጠቀሙበት ድረስ በምናባዊው ገንዘብ ተማምኖ ለመቆየት አስቸጋሪ ነው። እንደ ረዳት ፕሮፌሰር ሁሴን ሃሳብ ከሆነ ፤ አንድ አገር የወረቀት ገንዘብ አትሞ ሲያሰራጭ በወርቅ ክምችት ተግባብቶ ነው ገንዘቡን ወደሥራ የሚያስገባው። ክሪፕቶ ከረንሲውን የሚያሰራጭ ሰው ግን ካለምንም ዓለም አቀፍ ስምምነት መገበያያ ብሎ የሚያከፋፍለው እራሱ ያዘጋጃቸውን የኮምፒዩተር ኮዶችን ነው።

ባለቤቱ የኮምፒዩተር ኮዶቹን ለተለያዩ ሰዎች እያከፋፈለ በአንጻሩ ደግሞ ህጋዊ ገንዘቦችን የሚሰበስብበትና ሃብትን በእጁ የሚያስገባበት መንገድ እየሰፋ መሄዱ ደግሞ አይቀርም። አንድ የኮምፒዩተር ባለሙያ ወይም ድርጅት አንድ የክሪፕቶ ከረንሲ መገበያያ ቢፈጥርና ያ ገንዘብ ገበያው ቢገባ ኮዶችን ብቻ እያከፋፈለ በቅጽበት የዓለም ሃብታም የሚሆንበትና በአንድ ጀንበር የዓለምን ኢኮኖሚ የሚቆጣጠርበት ዕድሉ ሰፊ መሆኑን ረዳት ፕሮፌሰሩ ጠቁመዋል።

በተጨማሪ አጨቃጫቂ የሚሆነው ጉዳይ ክሪፕቶ ከረንሲን ማን እንደሚያሰራጨውና ባለቤቱ ማን እንደሆነ እንኳን አይለይም። በመሆኑም ካለው ስጋት አኳያ አንድ ቀን አገራት በሙሉ ምናባዊውን ገንዘብ ሊያቋርጡበት የሚችልበት ዕድል እንዳለ ማሰብ ያስፈልጋል ሲሉ ምክረ ሃሳባቸውን አስቀምጠዋል።

አንድ ድርጅት ቢት ኮይን የተባለ ወይም ሌላ ስም ሰጥቶ ይህንን ምናባዊ ገንዘብ አስተዋውቄያለሁ ስላለ ብቻ ሰዎች ገንዘባቸውንም ንብረታቸውንም ሰጥተው ያንን ምናባዊ ገንዘብ ለማግኘት የሚሯሯጡ ከሆነ እጃቸው ላይ የሚቀራቸው ሃብት እንደማይኖር ሊያስቡ ይገባል ሲሉ አሳስበዋል። ስለዚህ ይህን ምናባዊ የኮምፒዩተር ኮዶች የገዙ ሰዎች በተቻለ መጠን እራሳቸውን ከአደጋ ለመጠበቅ የያዙትን ምናባዊ ገንዘብ ወደህጋዊ ንብረት አሊያም በባንክ መገበያየነት እያገለገሉ ወደሚገኙ ገንዘቦች ቢቀይሩ ሃብታቸውን በቅጽበት ከማጣት ስጋት መላቀቅ ይችላሉ።

እንደ አገርም ይህንን ምናባዊ ገንዘብ ተግባራዊ ለማድረግ ሰፊ ዝግጅት ይጠይቃል ያሉት መምህሩ፤ ብዙ ሕጎችም መውጣት አለባቸው። በተጨማሪም በአገራት መካከል ጭምር ድርድሮችና ማካሄድና ምናባዊው ገንዘብ ላይ ስምምነቶች ማካሄድ ይኖርባቸዋል። ያን ጊዜ በሙሉ ልብ ይህንን ክሪፕቶ ከረንሲ መጠቀም እንደሚቻል ዕምነታቸው መሆኑን ገልጸዋል። ዲጂታል መገበያያ ገንዘብ አለያም ምናባዊ ንብረትን ለግብይት መጠቀም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ዕውቅና ያልተሰጠው ድርጊት በመሆኑ ህብረተሰቡ ከእንደዚህ አይነት ሕገ-ወጥ ተግባር እራሱን እንዲጠብቅ ባንኩ ማሳሰቡ የሚታወስ ነው።

ፈጣሪ ሀገራችንን በቃ ይበላት !

አሜን።

# ስፖርት





# አንድሬስ ኤስኮባር- የዓለም ዋንጫ አሳዛኝ ክስተት

**ቦጋለ አበበ**

ተወዳጁና ትልቁ የእግር ኳስ መድረክ የአለም ዋንጫ አንድ ክፍለዘመን ሊሞላ ጥቂት አመታት በቀሩት እድሜው ውስጥ ተዘርዝረው የማያልቁ ታሪኮችን አስተናግዷል። እያንዳንዱ የአለም ዋንጫ በአራት አመት አንዴ መጥቶ ሲሄድ ልክ እንደ ትናንት የሚታወሱ የራሱን የሆነ ትውስታን ጥሎ ያልፋል። ከዚህ በፊት የተካሄዱት ሃያ አንድ የአለም ዋንጫዎች እያንዳንዳቸው የራሳቸው ጣእምና ትውስታ፣አዳዲስ ታሪክ፣ አስደሳችና አሳዛኝ ክስተቶችን ጥለው የኳታሩ 2022 የአለም ዋንጫ ላይ ደርሰናል። ካለፉት በርካታ የአለም ዋንጫዎች አሜሪካ ያስተናገደችው የ1994ቱ 15ኛው አለም ዋንጫ ግን በአንድ አሳዛኝና አስደንጋጭ እንዲሁም ለማመን የሚቸግር ክስተት ዛሬም ድረስ በስፖርት ቤተሰቡ ዘንድ ይታወሳል።

የዘንድሮውን የአለም ዋንጫ ያነሳሉ ተብለው ግምት ከተሰጣቸው አገራት ግንባር ቀደም የሆነችው ብራዚል ቻምፒዮን የነበረችበት የአሜሪካ የአለም ዋንጫ፣ በእግር ኳስ ታሪክ ከአሳዛኝ ክስተቶች አንዱና ሁሌም የማይረሳ የሆነውን የአንድሬስ ኤስኮባር የግፍ ግድያ ሰብዓዊነትንና የአለም እግር ኳስ ቤተሰብን ያስደነገጠ ታሪክ የተፈጸመበት ሆኖ ይበልጥ ይታወሳል። እኛም በስፖርት ማህደር አምዳችን ይህን አሳዛኝ ክስተት መለስ ብለን ልናስታውሰው ነው።

አሳዛኙ ክስተት ዛሬ ታሪክ ሆኖ እንዲታወስ ያደረገው አጋጣሚ እንዲህ ይጀምራል። በአሰልጣኝ ፍራንቿስኮ ማቱራና የሚመራው የኮሎምቢያ ብሔራዊ ቡድን ከጅምሩ ዓለም ዋንጫ ላይ ለመሳተፍ በላቲን አሜሪካ አህጉር በምድባቸው ባደረጉት የማጣሪያ ደርሶ መልስ ጨዋታ አስገራሚ ውጤት አግኝተዋል፣ በአለም ዋንጫውም ቢያንስ ለግማሽ ፍፃሜ እንደሚደርሱ ገምተዋል፡፡

ሰኔ 22/1994 አሜሪካ ከኮሎምቢያ። በአሜሪካ ምዕራብ ጠረፍ ካሊፎርኒያ ግዛት፣ ሎስ አንጀለስ ከተማ ፓሳዲና በሚገኘው ሮዝ ቦውል ስታዲየም ከ93 ሺህ በላይ ተመልካቾች የታደሙበት ወሳኝ ጨዋታ ነው። የኮሎምቢያ ተጫዋቾች ዝቅተኛ ግምት የተሰጣት አስተናጋጇ አሜሪካን እንደሚያሸንፉ ተማምነዋል፣ በጨዋታው 35ኛ ደቂቃ የአሜሪካ ብሔራዊ ቡድን ተጫዋች ጆን ሀርከስ የፍጹም ቅጣት ምት ሳጥን ውስጥ ለሚገኘው የቡድን አጋሩ ኤርኒ ስቴዋርት ለማቀበል ያሻገረውን ኳስ፣ የአትሌቲኮ ናሲዮናልና የኮሎምቢያ ብሔራዊ ቡድን ተከላካይ አንድሬስ ኤስኮባር በሸርታቴ ለማጨናገፍ ባደረገው ጥረት ግብ ጠባቂው አስካር ኮርዶባ ኳሷን ሊያድናት በሚችልበት አቋቋም ላይ አልነበረምና በስህተት በራሱ ቡድን ላይ ግብ አስቆጠረ።

ወቅቱ በኮሎምቢያ ስርዓት አልበኝነት፣ ቁማር፣ ግድያ፣ ዘረፋ፣ እገታ ፣ አንደንዛዥ ዕፅ ዝውውር ተንሰራፍቶ የተደራጁ ወሮበሎች ታጥቀው መንግሥትን በሚያዙበት ሁኔታ በተለይ ሜድይን (ሜድሊን) ከተማ የወንጀለኞች መዲና ነበረች፡፡ ውጤቱን ተከትሎም በቁማር ብዙ ሚሊየን የተበሉ የኮሎምቢያ ማፊያ ቡድኖችና አለቆቻቸው አንድሬስ ኤስኮባር ላይ ጥርሳቸውን ነክሰው ቀጣዩን ጨዋታ እየተጠባበቁ ነበር።

ሰኔ 26 ስዊዘርላንድ 0- 2 ኮሎምቢያ ብታሸንፍም በመጀመሪያዎቹ ሁለት ጨዋታዎች የተሸነፈችው ኮሎምቢያ በውድድሩ ለመቆየት የአሜሪካና ሮማንያን ጨዋታ ውጤት መጠበቅ ነበረባት፣ ኮሎምቢያ እንድታልፍ የአሜሪካ ማሸነፍ፣ የሮማንያ ደግሞ መሸነፍ የግድ ነበር፡፡ ሮማንያ አሸነፈች ኮሎምቢያ ከውድድሩ ተሰናበተች፡፡

አንድሬስ ኤስኮባር ወደ ሀገሩ ተመለሰ። ጥንቃቄ እንዲያደርግና ለተወሰነ ጊዜ ከእይታ ሸሽግ እንዲል ከወዳጆቹ የተሰጠውን ምክር ችላ ብሎ፣ ከቀናት በኋላ ምሽቱን ለመዝናናት ከጓደኛው ጋር ሜድይን ወደሚገኘው 'ኤል ኢንዲዮ' ባር አቀና፣ ትንሽ ቀማምሶ እየተጨዋወተ ሳለ ከመሀል የተወሰኑ ሰዎች ይሰድቡትና ያንጓጥጡት ጀመሩ። በሁኔታው በመከፋት መጠጥ ቤቱን ለቆም ወደ መኪናው አመራ። ሰዎቹ ተከትለውት መጡ፣ ከሶስቱ መሀል አንዱ ሁምቤርቶ ካስትሮ ሙኞዝ ሽጉጡን አውጥቶ አከታትሎ ስድስት ጥይት ኢስኮባር ላይ አርከፈከፈበት። ከአሜሪካ ጋር በነበረው ጨዋታ በቀጥታ ሲያስተላልፍ የነበረው የላቲን ኮሜንታተር ግቡ ሲቆጠር ይል እንደነበረው ገዳዩም ሲተኩስ በእያንዳንዱ ተኩስ "ጎልልልልል" "ጎልልልል".... እያለ እንደነበር እማኞች ገልፀዋል፡፡ ከመኪናው ወንበር ሆኖ በደም ጨቅይቶ ለሞት እያጣጣረ የነበረው አንድሬስ በአምቡላንስ ወደ ሆስፒታል ቢወሰድም ከ45 ደቂቃ በላይ ሊቆይ አልቻለም፣ ሐምሌ 2 ህይወቱ አለፈች፡፡

በማግስቱ ፖሊስ አንድሬስ ኤስኮባር ላይ ተኮሰ የተባለውን ሁምቤርቶ በቁጥጥር ስር አዋለው። ተጠርጣሪው ወንጀሉን "ፈፅሜያለሁ" ብሎ ቢያምንም ነገሩ ግን ሌላ ነው፡፡ ግድያው እንደተፈፀመ ተጠርጣሪዎቹ ከአካባቢው ለማምለጥ ከተጠቀሙባቸው መኪና የአንዱን ሰሌዳ ቁጥር እማኞች ለፖሊስ ሰጡ፣ ተሽከርካሪው ንብረትነቱ የተመዘገበው በሁለቱ ዝነኛ የአደገኛ ዕፅ አዘዋዋሪ ወንድማማቾች ፔድሮ ጋዮንና ዩዋን ጋዮን ነበር። ሁምቤርቶ ደግሞ የወንድማማቾቹ ሹፌርና ጠባቂ ነው። ስለዚህ ሁምቤርቶ ያለ አለቆቹ እውቅና የዚህ አይነቱን ትልቅ ወንጀል ቢፈፅም ሞቱን የሚያስናፍቅ ቅጣት እንደሚከተለው ጠንቅቆ ስለሚያውቅ አያደርገውም። ግድያውን ተከትሎ ወንድማማቾቹ ፔድሮና ዩዋን



ወዲያውኑ 3 ሚሊየን ዶላር ጉቦ በመስጠት አቃቤ ህግ ክሱ ሁምቤርቶ ላይ ብቻ እንዲያተኩርና ከጀርባ ያለውን ሀቅ እንዳይበረብር አፉን አዘጉት፡፡

በ1995 ፍርድ ቤት በቀረበለት ማስረጃ መሠረት ሁምቤርቶን ጥፋተኛ ነህ ሲል የ43 ዓመት እስራት ፈረደበት። በግድያው ወቅት የነበሩ ግብረአበሮችም ሆኑ ወንድማማቾቹ ከየትኛውም ክስ ነፃ ሆኑ፡፡ ሁምቤርቶ በእስር ቤት በሰራው የጉልበት ስራና ባሳየው መልካም ባህሪ በሚል (በቁጥጥር ስር ከዋለበት ጀምሮ) ከ11 ዓመት በኋላ ብቻ በ2005 ከእስር ተለቀቀ፡፡ ገና በ27 ዓመቱ ለተቀጨው አመለሸጋ ወጣት አንድሬስ ኤስኮባር የቀብር ስነ-ስርዓት ከመቶ ሃያ ሺ ህዝብ በላይ ተገኝቷል። በተወለደበትና በተገደለበት ሜድይን ከተማ በ2002 መታሰቢያ ሀውልት ቆሞለታል፡፡




# ሩሂና የአገር አቀፍ ፈተና ዝግጅቱ

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

ሰላም ልጆች እንዴት ናችሁ፣ ትምህርት ጥሩ እየሄደላችሁ ነው? በጣም ጥሩ ነው የሚል ምላሽ እንደሰጣችሁኝ አምናለሁ። ምክንያቱም ጎበዝ ተማሪ ሁልጊዜ መልካሙን ያያል፡፡ መልካሙን ያጎላል፡ ፡ በምንም መልኩ አያማርርም። ምስጋናን ሁልጊዜ ያስቀድማል። ለዚህ ሁሉ የሚያበቃው ደግሞ ሳይጨናነቅ ትምህርቱን ስለሚያጠና ነው፡፡ ትምህርት ቤት ውስጥም ሆነ ከትምህርት ቤት ውጪ ዋና ጉዳዩ ትምህርቱን ብቻ ያደርጋል፡፡ በአግባቡ ትምህርቱን የሚከታተልና የሚለፋ ደግሞ ሁልጊዜ ውጤታማ እንደሚሆን ይታወቃል፡ ፡ እናም እናንተም እንዲህ አይነት ልጅ ስለሆናችሁ ፈተናዎችን በድል እንደምታጠናቅቁ እርግጠኛ ነኝ።

ልጆች ዛሬ ከባለፈው ሳምንት የቀጠለ ግን ለየት ያለ ጉዳይ ይዤላችሁ ቀርቤያለሁ። ምንድነው እሱ? ካላችሁኝ የጎበዞቹና መልካሞቹ ልጆች ወንድም የሆነውን ተማሪ ሩሂ ማሙሸት ነው፡፡ እነርሱ ምን ለየት ያደርገዋል ካላችሁ ደግሞ የዘንድሮ አገር አቀፍ ፈተና ተፈታኝ መሆናቸው ነው፡፡ በዚህም ዝግጅቱን የጀመረው ገና ትምህርት ሳይጀመር ነው፡፡ ትምህርት ከተጀመረ በኋላ ደግሞ የአዲሱ ትምህርት መጻህፍትን በሶፍት ኮፒ ስለሚደርሰው እርሱን ከሚያግዙ መማሪያ መጸሐፍት ጋር በማጣመር ያነባል፡፡

እንደ ሩሂ አመለካከት ተፈታኝ መሆን ራስ ላይ ጫና መፍጠር አይደለም፡፡ ሸክምም ተደርጎ ሊወሰድ አይገባውም፡፡ ከዚያ ይልቅ ጥልቅ አንባቢና አስተዋይ መሆን ብቻ ነው የሚያስፈልገው፡፡ በተለይ ለእውቀት ብሎ መማርን መሰረት ማድረግ ከምንም በላይ የበለጠ




**ሩሂ ማሙሸት**

ውጤታማ ያደርጋል፡፡ ስለዚህም እርሱ ለፈተና ዝግጅት ሲያደርግ ፈተናውን ቀላል አድርጎ ሳይመለከትና ከባድ ነው ብሎም ራሱን ሳያጨናንቅ ነው፡፡ ልጆችም በተለይም ተፈታኝ ተማሪዎች ለአገር አቀፉ ፈተና ራሳቸውን ሲያዘጋጁ በሁለቱ መካከል ሆነው በቂ ዝግጅት በማድረግ ሊሆን ይገባል ሲል ይመክራል፡፡ ቻልተኛ ሳይሆኑ በቂ ንባብ አድርገው መዘጋጀት ይገባቸዋል፡፡

ልጆች ሩሂ ትምህርቱን ሲያጠና የተለያዩ ዘዴዎችን ይጠቀማል፡፡ አንደኛው ዘዴው የተማረውን ዳግመኛ በመከለስ ለራሱ በሚመች መልኩ አጫጭር ማስታወሻዎችን መያዝ ነው፡፡ ሌላኛው ዘዴው ደግሞ ከጓደኞቹ ጋር ክፍል ውስጥ በቡድን ማጥናት ሲሆን፣ በዚህ በጣም ውጤታማ እንደሆነ ያምናል፡፡ ምክንያቱም ከእያንዳንዳቸው አዳዲስ ሀሳቦችን ያገኛል፡፡ በዚህም ለተጨማሪ ንባብ ያዘጋጀዋል፡፡

ሩሂ አንዳንዴ ደግሞ ሲያጠና ተጨማሪ ማብራሪያ ሊሰጡት የሚችሉትን መጽሐፍት ያነባል፡፡ ትምህርታዊ የሆኑ ፊልሞችንም ያያል፡፡ ይህ ደግሞ አጠናኑን ይበልጥ ከፍ ያደርግለታል፡፡ በቂ እረፍትና መዝናናት እንዳለበትም ያምናል፡፡ ምክንያቱም ራስን በማንበብ ላይ ብቻ ማቆየት ጥናቱን ውጤታማ እንደማያደርገው ያስባል፡፡ ስለዚህም ዘና የሚያደርገውን ነገር መርጦ ያከናውናል፡፡

ሩሂ ትምህርቱን ሲያጠናቅቅ መሆን የሚፈልገው የእግር ኳስ ተጫዋች ነው፡፡ ቦታውም አጥቂነትን የሚይዝበት ቢሆን ይመቸዋል፡፡ ለዚህ ደግሞ ከአሁን ጀምሮ በርትቶ እየሰራ ይገኛል፡፡ በተለይም በቡድን አቅፎ የሚያሰራቸው አካል ስላለ ደስተኛ ነው፡፡ እንደውም አንዳንዴ ዘና የሚልበትን ሁኔታ ሲፈልግ ይህንን አማራጭ እንደሚጠቀም ነው የነገረን፡፡

ልጆች ሩሂ ሌላም ሊሆን የሚፈልገው ነገር አለ፡፡? ፔዳትሪሽያን መሆን ነው፡፡ ማለትም የመተንፈስ ችግርና ከዚህ ጋር የሚያያዙ በሽታዎችን ማከም ላይ መሥራትን ይመኛል፡፡ በተለይ ሕጻናት አካባቢ ምርጫው ነው። ምክንያቱ ደግሞ የትንሹ ወንድሙ ህመም ሲሆን ወንድሙ የአስም ችግር አለበት፡፡ በዚህም እንዴት እንደሚያደርገው በቤት ስለሚያይ ወንድሙ ብቻ ሳይሆን ቤተሰቡም አብሮ ይታመማል፣ ይሰቃያልም፡፡ ስለዚህ እኔ የመፍትሄ አካል መሆን አለብኝ ብሎ ስለሚያስብ ይህንን ትምህርት ማጥናት ይፈልጋል፡፡ ለዚህ ደግሞ ልዩ ትኩረቱን ሳይንስ ትምህርቶች ላይ አድርጓል፡፡

ሩሂ ሰውን መርዳት በጣም ከሚወደው ነገር አንዱ ነው፡፡ ስለዚህም በቻለው ሁሉ ማገዝን ያስቀድማል፡፡ በእርግጥ የእርሱ እምነት ሰውን መርዳት በገንዘብ አለያም በአልባሳት ብቻ አይደለም፡፡ ከዚያም ባሻገር ነው የሚል ሲሆን ለምሳሌ ለሰዎች ካለን ጊዜ ላይ ቀንሰን በመስጠት ችግራቸውን ማዳመጥ በራሱ ማገዝ ነው ይላል፡፡ እናም ጓደኞቹን ሲደግፋቸው በተለያየ መልኩ ነው፡፡ አንድም በትምህርታቸው ደከም ያሉትን በማገዝ፣ በሌላ በኩል ያለውን ማንኛውም ነገር በማካፈልና ሀሳባቸውን በማድመጥ ጭምር ነው፡፡

ልጆች ሩሂ ለእናንተ የሚያስተላልፈው መልክት አለው፡፡ ይህም ሁልጊዜ መልካም ነገር አድርጉ፣ ከአፋችሁ የሚወጣው የሚያበረታና ወደፊት የሚያስኬድ እንጂ ተስፋ የሚያስቆርጥ አይሁን፡፡ ምክንያቱም መጥፎ ንግግሮች የሰውን ፍላጎት ይገታሉ፣ ከአሰብንበት ቦታም ያስቀሩናል፡፡ እናም ለሌሎች መሰናክል እንዳትሆኑ መጠንቀቅ አለባችሁ፡፡ በተጨማሪ አስተዋይና ለትምህርታችሁ ቅድሚያ የምትሰጡ ልጆች መሆን ይገባችኋልም ብሏል፡፡ ስለዚህም ምክሩን ሰምታችሁ የምትተገብሩ ሁኑ፡፡ በሉ ለዛሬ በዚህ እንሰናበት በሚቀጥለው ጊዜ በሌላ ጉዳይና በሌላ እንግዳ እስክንገናኝ ቸር ሰንብቱ፡፡ መልካም ሰንበት !!